# አማርኛ

## እንደ መጀመሪያ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU



## ፯ኛ ክፍል

# አማርኛ

# እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# ፯ኛ(7) ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ


አዘጋጆች፡-

ማርዬ ጌትነት ስንቴ

ብርሃኑ ካሳ ረታ

አለማየሁ ደስታው ዳመና

ገምጋሚና አርታኢዎች፡-

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ኃይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

ጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ፡-

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

አስተባባሪ፡- ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

አቀማመጥ እና ስዕል፡-

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (TMS)

© የመጽሐፉ ህጋዊ ቅጂ ባለቤት2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ ላደረጉት ከፍተኛ ሙያዊናአስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉት ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ፣
እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት በሚያጋጥሙ ችግሮችመፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገምሁሌም ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮየማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ ፣ የትምህርትቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊአቶ ሳምሶን መለሰ ፣ ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ ፣ ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊአቶ ሲሳይ እንዳለ ፣ ለቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል።
በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ለአዘጋጅ መምህራንከዚህ በላይ ስራ የለም በማለት ፍቃድ በመስጠትና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንእናቀርባለን።

# ማውጫ

ገፅ

መግቢያ ------------------------------------------------------------------------I

ምዕራፍ አንድ፡- ተፈጥሮን ማድነቅ-------------------------------------1

ምዕራፍ ሁለት፡- የቤተሰብ እቅድ-------------------------------------15

ምዕራፍ ሦስት፡- በጎ ፍቃደኝነት-------------------------------------27

ምዕራፍ አራት፡- የታዋቂ ሰዎች የህይወት ታሪክ------------------39

ምዕራፍ አምስት፡- ውሃ እና ጥቅሙ--------------------------------55

ምዕራፍ ስድስት፡- የሰዎች ዝውውር---------------------------------72

ምዕራፍ ሰባት፡- ማህበራዊ ግንኙነት---------------------------------89

ምዕራፍ ስምንት፡- ሱስ-----------------------------------------------103

ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የሀገር ፍቅር--------------------------------------117

ምዕራፍ አስር፡- ቃላዊ ግጥም---------------------------------------130

ዋቢ መጽሐፍት፡- -----------------------------------------------------148

አባሪዎች፡- -------------------------------------------------------150

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ አማርኛን በመጀመሪያ ቋንቋነት የሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ መጻፍ እንዲችሉ፤ በተጨማሪም የቃላት እና የሰዋስው ዕውቀት እንዲያዳብሩ ለማድረግ የተዘጋጀ የሥርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ በዚህ የክፍል ደረጃ ስለሚሰጡ ትምህርቶች ሰፊ መረጃ ይሰጣል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርት ቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል፡፡

## መሰረታዊ መርሆዎች

- ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ፡፡
- ተማሪዎች በመጽሐፍ ውስጥ በቀረቡት ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በንግግር ሀሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡
- በቀጣይም በማሕበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ፡፡ ስለነዚህ የምንባብ ይዘቶች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡ በኋላ ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡
- አራቱን ክሂሎች ከላይ በተቀመጠው መሰረት ከተማሩ በኋላ በክፍል አምስትና ስድስት የቀረቡትን የቃላትና የሰዋስው ትምህርቶችን በየምዕራፉ በተገለጸው ዓላማ መሰረት ይማራሉ፡፡
- ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ተማሪዎች ጋር በመተባበር ይማራሉ፡፡

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር መማር

ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ:: ስለዚህ ወላጆች ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል::

1. የእለቱን የትምህርት ይዘት በተመለከተ ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድህረ-ገጽ ስለርዕሰ ጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ::
2. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለ መጠይቅ ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው::
3. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰ ጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ:: በትምህርት ቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ:: ይህንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ፤
4. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፤
5. ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሑፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ::
6. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ::
7. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የተለያዩ ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ::
8. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው፤ ለምሳሌ፣ የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ ተሰድረዋል ወይ? በዓረፍተ ነገሮች

ውስጥ /መካከል/ ያሉት ሥርዓተ ነጥቦች (አራት ነጥብ፣ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል ወይ? ወዘተ.

9. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ. እንዲጽፉ አበረታቷቸው።

# ምዕራፍ አንድ (፩)

## ተፈጥሮን ማድነቅ

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-

- የሌሎችን ሀሳብ ታዳምጣላችሁ።
- ስለ ተፈጥሮ ምንነት ትወያያላችሁ።
- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ጽሑፍ ታነባላችሁ።
- የተፈጥሮን የተለያዩ ገፅታ ታደንቃላችሁ።
- አንቀፅ ትመሰርታላችሁ።

## ክፍል አንድ ፡-ማዳመጥ

### “ አባይ”

❖ ቅድመ ማዳመጥ

1. ስለ ተፈጥሮ ምን ታውቃላችሁ?
2. ስለ ወንዞች አጠቃቀም የምታውቁትን በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ?
3. ከላይ ከቀረበው ምስል ምን ተረዳችሁ?

❖ የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር፡-

“አባይ” የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

ተግባር አንድ:-

"የአባይ ወንዝ እና የሕዳሴው ግድብ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. የሕዳሴው ግድብ በየትኛው ክልል ይገኛል?
   ሀ. ሶማሌ  ለ. አማራ  ሐ. ደቡብ  መ. ቤኒሻንጉል ጉሙዝ
2. የግድቡ ግርጌ ውፍረት ስንት ሜትር ነው?
   ሀ. 120 ሜትር  ሐ. 130 ሜትር
   ለ. 135 ሜትር  መ. 125 ሜትር
3. አባይን በተመለከተ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ከዓለማችን ረጃጅም ወንዞች አንዱ ነው።
   ለ. የአንድ ሀገር ብቻ ተፋሰስ ነው።
   ሐ. የግድቡ ከፍታ 145 ሜትር ነው።
   መ. አባይ 6696 ኪ.ሜትር ርዝመት አለው።
4. በአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የአባይ ወንዝ የተነፃፀረው ከየትኛው ወንዝ ጋር ነው?
   ሀ. ከአማዞን  ለ. ከአዋሽ  ሐ. ከተከዜ  መ. ከዛየር
5. የህዳሴው ግድብ ሲጠናቀቅ ስንት ሜጋ ዋት ያመነጫል?
   ሀ. 5200  ለ. 6450  ሐ. 5000  መ. 6000

ተግባር ሁለት:-

ካዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

1. የህዳሴው ግድብ ተገንብቶ ሲያልቅ ለሀገር እድገት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።
2. የመኖሪያ ቤታችን የኤሌክትሪክ ፍጆታ እየጨመረ ነው።
3. በትምህርቴ ጥሩ ውጤት የማምጣት ውጥን አለኝ።

4. ነገ ደመና እንደሚኖርና ዝናብ እንደሚጥል ተተንብይዋል፡፡
5. የአስፓልት መንገዱ እንዳይበላሽ የመንገድ ዳር ተፋሰስ ሊሰራለት ይገባል፡፡
6. የህዳሴው ግድብ ከፍታ 145 ሜትር ነው፡፡
7. የአባይ ወንዝ በዓለም ላይ ካሉ ረጃጅም ወንዞች በግንባር ቀደምነት ተጠቃሽ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ የንግግር መመሪያ መሰረት ታላቁ የህዳሴ ግድብ መገንባቱ ለሀገር ልማት ምን ጥቅም እንደሚሰጥ በቡድን ተወያዩ፡፡ ከውይይቱም በኋላ ከቡድናችሁ አንድ ሰው በመምረጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተገቢውን ቋንቋ በመጠቀም ንግግር አቅርቡ፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

በተግባር አንድ ባቀረባችሁት ንግግር መሰረት የእርስ በእርስ ግምገማ አድርጉ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

“የአፋር የተፈጥሮ ገፀ-በረከቶች”





## ❖ ቅድመ ንባብ

1. ተማሪዎች ለሽርሽር የተለያዩ ቦታዎች ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? ካወቃችሁ የትና መቼ?
2. አፋር ክልል በኢትዮጵያ በየት አካባቢ የሚገኝ ይመስላችኋል?
3. በአፋር ክልል ምን ምን አይነት የተፈጥሮ መስህቦች የሚገኙ ይመስላችኋል? ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ፡፡

## ❖ የንባብ ሂደት

ተግባር፡-

"የአፋር የተፈጥሮ ገፀ-በረከቶች" የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ በየመሀሉ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል እየሰጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

### "የአፋር የተፈጥሮ ገፀ-በረከቶች"

ሌሊቱ አልነጋ ብሎኝ እንዲሁ ስገላበጥ ነው ያደርኩት፤ ይህም የሆነው መስሪያ ቤታችን በሚያዘጋጀው ዓመታዊ የጉዞ መርሃ ግብር ለመሳተፍ ካለኝ ጉጉት የመነጨ ነው፡፡ ለጉዞ የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች በሻንጣ ከሸከፍኩ በኋላ ወፎች መጮህ ሳይጀምሩ ከቤቴ በመውጣት፤ የጠዋቱ ብርድ እያንዘፈዘፈኝ ከመስሪያ ቤታችን ቅጥር ግቢ ደረስኩ፡፡

ቦታው ላይ እንደደረስኩ የተፈጥሮ ገፀ-በረከት ወደ ሆነችው የአፋር ክልል ለመሄድ የስራ ባልደረቦቼ ግቢውን ሞልተውት ደረስኩ። ወዲያውም ወደ ተዘጋጀው አውቶብስ በመግባት ጉዞ ጀመርን። በጉዞ ወቅትም ሁሉም መንገደኛ በሀሳብ ተውጦ የአዲስ አበባን ከተማ የከበቡትን ትላልቅ ተራራዎች እየተመለከተ ባለበት ሰዓት አስጎብኛችን ስለ ክልሉ ገለፃውን ጀመረ።

"የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኘው በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ ሲሆን፣ 85,410 ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት አለው። ክልሉ በሰሜን ምዕራብ ከትግራይ፣ በደቡብ ምዕራብ ከአማራ፣ በደቡብ ከኦሮሚያ፣ በምስራቅ ከሱማሌ የኢትዮጵያ ክልሎች እና ከጅቡቲ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ ከኤርትራ ጋር ይዋሰናል። የክልሉ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከባህር ወለል በላይ እስከ 1500 ሜትር ከፍታ ካላቸው ኮረብታማ ስፍራዎች አንስቶ ከባህር ወለል በታች እስከ 116 ሜትር ዝቅታ ያላቸው ረባዳማ ስምጥ ስፍራዎችን ያካትታል። የአየር ንብረቱም ቆላማና በረሃማ ሲሆን፣የሙቀት መጠኑም ከ18 እስከ 45 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ይደርሳል።

የአፋር ክልል መስተዳደር በ5 ዞኖች እና በ29 ወረዳዎች የተከፋፈለ ሆኖ በውስጡ 28 ከተሞች እና 326 የቀበሌ ገበሬ ማህበራት አሉት። የህዝብ ብዛቱም በ1996 ዓ.ም 1.5 ሚሊዮን እንደሚደርስ እና ዓመታዊ የእድገት መጠኑም 2.4 በመቶ እንደሚሆን ተገምቶ ነበር። ከክልሉ ህዝብ የወንዶቹ መጠን ከሴቶቹ የላቀ ሲሆን፣ እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ 46.1 በመቶ የሚሆነውን ቁጥር ይሸፍናሉ። በክልሉ ከሚኖሩት ዋና ዋና ብሄረሰቦች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር ማለትም 92 በመቶውን የያዙት የአፋር ብሄር አባላት ናቸው። የአፋሮች ባህላዊ የቤት አሰራር ስርዓት <<አሪ>> ተብሎ ሲጠራ፣ መረጃ የሚቀባበሉበት ባህላዊ ስርዓት ደግሞ <<ዳጉ>> ይባላል።

አፋር ከፍተኛ የከብት ብዛት እና ሰፊ የእርሻ መሬት ከሚገኝባቸው፣ የውሃ እና የኢነርጂ ሀብት ካላቸው እንዲሁም በቱሪስት መስህብነታቸው ከሚታወቁት ክልሎች አንዱ ነው፡፡ ክልሉ ሙሉ በሙሉ በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ የዳሎል ረባዳ ስፍራ እና የኮባር ስምጥ ሸለቆ እሳተ ገሞራ ወለድ ተራራዎች እንዲሁም የህብረቀለም የጨው ኮረብታማዎች ለክልሉ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ተጨማሪ ውበት አጎናጽፈውታል፡፡" በማለት በዝርዝር አስረዳን፡፡

***ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት የተረዳችሁትን ዋና ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡ በቀጣዩ ክፍል ስለምን ሊነሳ የሚችል ይመስላችኋል?

በጉዟችንም ወቅት አዳማ፣ አዋሽ አርባ፣ አዋሽ ሰባት፣ ሚሌ፣ ሎጊያ ከተሞችን በማቋረጥ የክልሉ ዋና ከተማ ከሆነችው ሰመራ ገባን፡፡ አስጎብኛችንም "በክልሉ የሚገኙት የተፈጥሮ መስህቦች ክልሉን በጣም አስደናቂ ከሚባሉ አካባቢዎች ተርታ እንዲመዘገብ አድርገውታል" በማለት ነገረን፡፡ በመቀጠልም በአዋሽ ወንዝ ረግረጋማ አካባቢዎች ያለውን የተፈጥሮ ትዕይንት፤ በአካባቢው የሚገኙ እና የፈዋሽነት ሀይል አላቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን በርካታ የፍል ውሃ ምንጮች፣ ሀይቆች እና ወንዞች፣ የተለያዩ የዱር እንስሳትን ጎበኘን፡፡

በማግስቱም ከቀሪዎቹ የቱሪስት ሀብቶች መካከል ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ በ211 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን የአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ለመጎብኘት ቻልን፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ፓርኮች ውስጥ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሰው ይህ ፓርክ 827 ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት አለው፤ በውስጡ 86 አጥቢ እና 392 የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡ ፓርኩን አቋርጦ የሚፈሰው የአዋሽ

ወንዝ የሚፈጥረው ፏፏቴ እና በፓርኩ ክልል የሚታየው ውብ ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ጋር ተዳምሮ ቀልባችንን ገዛው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ፓርኩን የሚጎበኙ የቱሪስቶች ቁጥር እየጨመረ ቢመጣም፣ ገቢው የሚያረካ እንዳልሆነ አስጎብኛችን ነገረን። ለዚህም በዋንኛ ምክንያትነት የሚጠቀሰው በአካባቢው ለውጭ ቱሪስቶች አመቺ የሆኑ የሆቴል እና የመኝታ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ አለመኖር እና በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ቱሪዝምን ለማስተዋወቅ የሚደረገው ጥረት አናሳ መሆኑ እንደሆነ አብራራልን።

በአስጎብኛችን ገለፃ መሰረት የአፋር ክልል ዓለም አቀፋዊ እይታ እንዲገባ ካደረጉት ሌሎች ጉዳዮች መካከል በሃዳር፣ በጉና፣ በመልካ ወረር፣ በመካከለኛው አዋሽ እና በሌሎች ስፍራዎች የሚደረጉት የምርምር ስራዎች ይጠቀሳሉ። ስፍራዎቹ ኢትዮጵያ ትልቅ የታሪክ አሻራ እና የቅርስ ባለቤት መሆኗን አመላክተዋል። ይህም በሰው ዘር አዝጋሚ የእድገት ታሪክ ጥናት እና ምርምር ላይ በተሰማሩ ተመራማሪዎች ዘንድ እንደ በለፀገ የእንቁ ማዕድን የሚቆጠር አለማቀፋዊ ፋይዳ ያለው ግኝት በመሆኑ ኢትዮጵያ በአለም ህብረተሰብ ዘንድ እንድትታወቅ አድርጓታል። ከጊዜ ወደ ጊዜ የቱሪስቶችን ቀልብ እየሳበ የመጣው የኤርታኤሌ እሳተገሞራ ወለድ ተራራማ ተፈጥሮን ከማድነቅ ባሻገር፣ ለማመን እስከ ሚያዳግት ድረስ ህሊናን የሚገዛ የተፈጥሮ ክስተት ለማየት የሚያስችል በመሆኑ ብዙዎች የሚናፍቁት ሆኗል።

ክልሉ የአፍዴራ ሀይቅ፣ የዳሎል ረባዳማ ምድር፣ የዶቤ ባህላዊ የጨው ማምረቻ፣ የአፋምቦ እና የግመሬ ሀይቆች፣ የበርሀሌ ህብረ-ቀለም የጨው ተራራ እንዲሁም ያንጉዴራ የተሰኘው ብሔራዊ ፓርክ እና ሌሎች የውጭ እና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን ቀልብ የሚገዙ የተፈጥሮ መስህቦችም ይገኙበታል።

እኛም በአፋር ክልል የነበረንን ጣፋጭ ቆይታ አጠናቀን በሰላም ወደ አዲስ አበባ ተመለስን፡፡

ምንጭ፡- (በ1998 ዓ.ም ከታተመው የቀድሞው የ11ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪ መጽሀፍ፣ ከገጽ 19-22 ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የተሻሻለ፡፡)

❖ አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. በአዋሽ ፓርክ ውስጥ ስንት የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ?
2. ክልሉ በቱሪዝም ተገቢውን ያህል እንዳይጠቀም ያደረጉትን ምክንያቶች ዘርዝሩ፡፡
3. የአፋር ክልል ለምን የእምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤት ተባለ?
4. የአፋሮች ባህላዊ የቤት አሰራር ምን ተብሎ ይጠራል? የመረጃ መቀባበያ ዘዴስ ምን ይባላል?
5. በክልሉ ውስጥ የቱሪስቶችን ቀልብ እየሳበ የመጣው እሳተ ገሞራ ማን ይባላል?

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ቀልብ | ሀ. ስጦታ |
| 2. ገፀ-በረከት | ለ. ዝቅተኛ ቦታ |
| 3. ስርዓት | ሐ. ሁነት |
| 4. ረባዳ | መ. መነሳሳት |
| 5. ህብረ-ቀለም | ሠ. የቀለማት ውህደት |
| 6. ክስተት | ረ. ትኩረት |
| | ሰ. ደንብ |

ተግባር ሶስት፡-

“የአፋር የተፈጥሮ ገፀ በረከቶች” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ተራ በተራ ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ አንብቡ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

ማስታወሻ

አንቀፅ

የአንቀፅ ምንነት፡- አንቀፅ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ የሚተላለፍበት የድርሰት አነስተኛ አካል ነው፡፡ አንቀፅ የዓረፍተ ነገሮች ድምር ውጤት ነው፡፡ በአንድ አንቀፅ ውስጥ ሁለት ዓይነት ዓረፍተ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡-

1. ሀይለቃል (መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር) ፡-የአንቀፁን አጠቃላይ ሀሳብ ጠቅልሎ የሚይዝ የዓረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡
2. መዘርዝር፡- በሀይለ-ቃሉ ላይ የቀረበውን ሀሳብ በዝርዝር የሚያብራሩ የዓረፍተ ነገር አይነቶች ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-

<u>ብቸኝነት ጣጣው ብዙ ነው፡፡</u> ሰው ማህበራዊ ፍጡር በመሆኑ ከብቸኝነት መራቅ አለበት፡፡ አለበለዚያ የብቸኝነት ኑሮ ለሚያስከትላቸው ችግሮች ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ብቸኛ ሰው የሚያነጋግረውን ፍለጋ መዋተቱ አይቀሬ ነው፡፡ ብቸኝነትን ለመሸሽ ሲባል ወደ ተለያዩ ሱሶች ሊገባ ይችላል፡፡ ነጋ ጠባ መበሳጨትና ራስን መጣልም የብቸኝነት መዘዞች ናቸው፡፡


ከላይ በቀረበው አንቀፅ ውስጥ የተሰመረበት የአንቀፁ ሀይለቃል ሲሆን ሌሎቹ አምስት ዓረፍተ ነገሮች ሀይለ-ቃሉን የሚያብራሩ መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

የአንቀፅ ቅርፅ፡- የአንድ አንቀፅ ቅርፅ የሚወሰነው ሀይለ-ቃሉ

በሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ እነሱም፡-

1. ሀይለ-ቃሉ መጀመሪያ ሲመጣ፡- ሀይለ-ቃሉ መጀመሪያ ላይ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ ይሄን ይመስላል፡፡ 


2. ሀይለ-ቃሉ መሀል ላይ ሲመጣ ፡- ሀይለ-ቃሉ መሀል ላይ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ ይሄን ይመስላል፡፡ 

3. ሀይለ-ቃሉ መጨረሻ ላይ ሲመጣ፡- ሀይለ-ቃሉ መጨረሻ ላይ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ ይሄን ይመስላል፡፡ 

4. ሀይለ-ቃሉ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ ሲመጣ፡- ሀይለ-ቃሉ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ ይሄን ይመስላል፡፡ 


**ተግባር አንድ፡-**

ከላይ በቀረበው ማስታወሻ መሰረት ከታች የቀረበላችሁን ቢጋር በመከተል "ቱሪዝም" በሚለው ርዕስ ሁለት አንቀፅ ጻፉ፡፡




**ተግባር ሁለት፡-**

ተማሪዎች "ቱሪዝም" በሚል ርዕስ የፃፋችሁትን አንቀፅ በቡድን በመሆን እርስ በርስ ተገማገሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

ተዘውታሪ ቃላት

ማስታወሻ

ቃላት ማለት በስርዓት የተሰደሩ ፊደላት ስብስብ ነው፡፡ ቃላትን ተዘውታሪና ያልተዘወተሩ (አዳዲስ ቃላት) ብለን መክፈል እንችላለን፡፡

1. ተዘውታሪ ቃላት፡- በእለት ተዕለት ኑሯችን በተደጋጋሚ የምንጠቀማቸው ቃላት ናቸው፡፡
   ምሳሌ፡- በላ፣ ልብስ፣ ምግብ ... የመሳሰሉት ናቸው፡፡
2. ያልተዘወተሩ፡- በእለት ተዕለት ኑሯችን ውስጥ አልፎ አልፎ የምንጠቀማቸው እንግዳ የሆኑ ቃላት ናቸው፡፡
   ምሳሌ፡- ተግዳሮት፣ ጥቁር እንግዳ... የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### ተግባር አንድ፡-

ከዚህ በታች በቀረቡት ዓ.ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን በመለየት ፃፉ፡፡

1. የኤርምያስን ሙግት አልቻልኩትም፡፡
2. ለገና ዋዜማ እመጣለሁ ብሎኛል፡፡
3. አቶ ሙሳ ሰርክ ወደ መስጊድ ይመላለሳሉ፡፡
4. አዘቦት ቀን እመጣለሁ ብሎ እስካሁን የውሃ ሽታ ሆነ፡፡
5. ገመቹ ኳሷን ወደ ሰማይ አጎናት፡፡
6. ወደ ስራ ለመሄድ ስነሳ ጥቁር እንግዳ መጣብኝ፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ቢያንስ አምስት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡-

መምህራችሁ በሰጧችሁ ማስታወሻ መሰረት ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ በማለት ለዩ፡፡

1. የክረምቱ ዝናብ ከቤት አያስወጣም፡፡
2. አባቴ ከመጣ ሽርሽር ይወስደኛል፡፡
3. ሕፃናት ከአቅማቸው በላይ ሥራ መሥራት የለባቸውም፡፡
4. ፈተና ስለ ደረሰ ጥናታችንን እናጠናክር፡፡
5. የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር በፈተናው ዙሪያ ማብራሪያ ሰጡ፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

ከላይ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች መሰረት አምስት ነጠላ እና አምስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ የንግግር መመሪያ፣ የአንቀጽ ምንነት፣ ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት እንዲሁም ነጠላና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ተምረናል።
- ንግግር በቃል ወይም በጽሁፍ ሊቀርብ የሚችልና ሀሳብ አፍልቀን ለሌሎች የምናስተላልፍበት ክሂል ሲሆን ከዝግጅት እስከ አቀራረብ ጥንቃቄን የሚፈልግ ነው።
- አንቀፅ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ የሚተላለፍበት የድርሰት አነስተኛ አካል ነው። አንቀፅ የዓረፍተ ነገሮች ድምር ውጤት ሲሆን በአንድ አንቀፅ ውስጥ ሁለት ዓይነት ዓረፍተ ነገሮች ይገኛሉ። እነሱም፡- ሀይለቃልና መዘርዝር ዓረፍተ ነገር ናቸው።
- ቃል ማለት በስርዓት የተሰደሩ ፊደላት ስብስብ ሲሆን ቃላትን ተዘውታሪና ያልተዘወተሩ (አዳዲስ ቃላት) ብለን መክፈል እንችላለን።
- ዓረፍተ ነገሮች ከመዋቅር (ከቅርፅ) አንጻር ነጠላ እና ውስብስብ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ስለ ተፈጥሮ ማድነቅ ምን እንደተረዳችሁ ተናገሩ።
2. የአንድን አንቀፅ ቅርፅ የሚወስነው ምንድን ነው?
3. የኃይለ ቃል እና መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ልዩነት ተናገሩ።

# ምዕራፍ ሁለት (፪)

## የቤተሰብ እቅድ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፦**

- በጥሞና ታዳምጣላችሁ።
- በቤተሰብ እቅድ ምንነት ላይ ትወያያላችሁ።
- ቀላል ሁነቶችን ትተርካላችሁ።
- የቤተሰብ እቅድን መሰረት አድርገው በሚሰጡ አስተያየቶች ላይ ትከራከራላችሁ።
- ስዕሎችን ታብራራላችሁ።

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### “ ልጅ በእድሉ ያድጋል?”

❖ ቅድመ ማዳመጥ

1. የቤተሰብ ምጣኔ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ማለት ነው?
2. <<ልጅ በእድሉ ያድጋል>> በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ?
3. ከላይ ከቀረበው ስዕል ምን ተረዳችሁ?

❖ የማዳመጥ ሂደት

ተግባር፡-

“ልጅ በእድሉ ያድጋል” የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስታወሻ በመያዝ በንቃት አዳምጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

**ተግባር አንድ፡-**

“ልጅ በእድሉ ያድጋል” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. የነህብስት ቤተሰብ ብዛት ስንት ነው?
2. “የሚላስ የሚቀመስ” ከቤት ጠፋ በሚል የቀረበው ሀሳብ ምንን ይገልፃል?
3. የህብስት ትዳር ሰላም ያጣው በምን ምክንያት ነው?
4. የእነዘምዘም ቤተሰብ በሰላም እና በፍቅር የተሞላው በምን ምክንያት ነው?
5. <<የጥሩ ጓደኝነት ተምሳሌት ናቸው>>፡፡ ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ምን ጠቀሜታ አለው?

**ተግባር ሁለት፡-**

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ቁልፍ ቃላት እና ሀረጋት ከታች በቀረቡት ያልተሟሉ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢው ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ደፋ ቀና | የዕለት ጉርስ | ዶሮ ሳይጮህ |
| የበኩር | ባልደረባ | ባልንጀራ |

1. አልማዝ የበቀለ ----------- ልጅ ናት፡፡
2. መገርሳ የዕለት ኑሮውን ለማሻሻል ---------------ይላል፡፡
3. ------------------ከቤት የወጣ ጀምበር እስክትጠልቅ አልተመለሰም፡፡
4. የመስሪያ ቤቱ የስራ --------------- የሆነው አቶ ሀሰን ከመኪና አደጋ ለጥቂት ተረፈ፡፡
5. ለተሰንበት የዘቢባ ------------- ናት፡፡


## ክፍል ሁለት፡- መናገር

ተግባር፡-

1. ከታች የቀረበውን ቢጋር መሰረት በማድረግ የሁነቶችን ቅደም ተከተል በመጠበቅ አጭር ንግግር አድርጉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| የቤተሰብ እቅድ አለመጠቀም → | በቤተሰብ ውስጥ ሰላምና ፍቅር መጥፋት → | የትዳር መፍረስ → | የልጆች መበተን |

2. የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ "ልጅ በእድሉ ያድጋል" የሚለውን ሀሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ክርክር አድርጉ፡፡



## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### "የቤተሰብ እቅድ"



❖ ቅድመ ንባብ

1.የስነ-ተዋልዶ አገልግሎት ምንድን ነው?
2."ልጅ ሀብት ነው" በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ?
ምክንያታችሁን በቃል ግለፁ ፡፡
3.በአካባቢያችሁ የስነ-ተዋልዶ አገልግሎት ይሰጣል?ከተሰጠ የት?

❖ የማንበብ ሂደት

ተግባር አንድ፡-

“የቤተሰብ እቅድ” የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ምላሽ እየሠጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

## “የቤተሰብ እቅድ”

የሴቶችን መብት ማረጋገጥ ለልማት ያለው አበርክቶ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ እ.ኤ.አ በ1994 በካይሮ ላይ የተደረገው ዓለም አቀፍ የስነ-ህዝብ እና ልማት ጉባኤ ከፍተኛ መነቃቃትን ፈጥሯል፡፡ በወቅቱ የስነ-ተዋልዶ ጤናን ማስፋፋት እና የፆታ እኩልነትን ማስፈን የአንድ ሀገር የልማት እምብርት ተደርጎ መወሰዱ የጉባኤው ስኬት ነበር፡፡ ከጉባኤው ሩብ ምዕተ ዓመት በኋላ ዓለም ፈጣን እድገት ያስመዘገበች ሲሆን በዓለም ደረጃ የእርግዝና መከላከያ አቅርቦት በሃያ በመቶ እድገት አሳይቷል፡፡ የእናቶች እና የህጻናት ሞትም በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን የተባበሩት መንግስታት የስነ-ህዝብ መረጃ ያመለክታል፡፡ እ.ኤ.አ በ2019 በዓለም ዙሪያ 1.9 ቢሊዮን እድሜያቸው ከ15-49 ዓመት በመውለድ እድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ሴቶች መካከል 1.1 ቢሊዮን የሚሆኑት ሴቶች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የመጠቀም ፍላጎት አላቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ 842 ሚሊዮን የሚሆኑት የእርግዝና መከላከያዎችን እየተጠቀሙ ሲሆን 270 ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ የእርግዝና መከላከያ እየፈለጉ አገልግሎቱን ያላገኙ ናቸው፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከተነበበው ምን ተረዳችሁ? በሀገራችን ያለው የስነ-ተዋልዶ አገልግሎት ምን ይመስላችኋል?

በሀገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ እ.ኤ.አ በ2019 በተጠና ጥናት መሰረት ማንኛውንም አይነት ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን የመጠቀም ምጣኔ እ.ኤ.አ በ2005 ከነበረበት 14% በ2019 ወደ 41% አድጓል፡፡

ሆኖም ባለፉት 5 ዓመታት በወቅቱ ከነበሩት እርግዝናዎች መካከል 17% የሚሆኑት ያልታቀዱ ነበሩ፡፡ ይባስ ብሎ እድሜያቸው ከ18-19 ከሆኑ አፍላ ወጣት ሴቶች መካከል 10% የሚሆኑት በለጋነት እድሜያቸው የልጅ እናት ሲሆኑ 2% የሚሆኑት ደግሞ በጥናቱ ወቅት የመጀመሪያ ልጃቸውን አርግዘው ተገኝተዋል፡፡

የሀገራችን የስነ-ህዝብ ፖሊሲ እና የስነ-ተዋልዶ ጤና እስትራቴጂ ሁሉም ሰዎች በተለይ እናቶች እና አፍላ ወጣቶች የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ በርካታ የሰብዊ መብቶችን፣ የአመለካከት እና ሀሳብን የመግለፅ እንዲሁም የመስራት እና የመማር መብትን ብሎም ከፍተኛ የጤና እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ያትታል፡፡ የእርግዝና መከላከያ መጠቀም ከእርግዝና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የጤና አደጋዎችን በሴቶች በተለይም በአፍላ ወጣት ሴት ልጆች ላይ እንዳይከሰት ይከላከላል፡፡

በልጆች መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት ከሁለት አመት በታች ከሆነ የህጻናት ሞት መጠን የዕድሜ ልዩነታቸው ከ2-3 ዓመት ከሆኑት ጋር ሲነፃፀር በ45 ከመቶ ከፍ ያለ ሲሆን በአራት ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ከሚለያዩት ጋር ሲነጻፀር ደግሞ በ60 በመቶ ከፍ ይላል፡፡ የትምህርት እድሎችን ለማስፋፋት እና ለሴቶች አቅም መጎልበት እንዲሁም ለሀገራችን ዘላቂ የህዝብ እድገት እና ኢኮኖሚያዊ ልማት የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ፍቱን መድሀኒት ሲሆን በርካታ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡
የስነ-ተዋልዶ ጤና ከቤተሰብ እቅድ አገልግሎት በተጨማሪ የተሟላ የዕናቶች እና የሕጻናት ጤና አገልግሎትን ማዳረስን፣ የአፍላ ወጣቶችን ጤና፣ ኤች አይቪን ጨምሮ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን መከላከል እና ማከምን፣የመካንነት ችግርን መለየት እና ማከምን፣ የማህፀን ጫፍ ካንሰር ልየታ እና ህክምናን፣ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከልን እና ተጎጅዎችን ማከምን ብሎም ሌሎች ወሳኝ አገልግቶችን የሚያጠቃልል የጤና አገልግሎት

ቢሆንም ስር የሰደዱ የተዛቡ አመለካከቶች እና መሰረተ ቢስ አሉቧልታዎች ህዝባችን አገልግሎቶቹን በአግባቡ እንዳይጠቀም ማነቆ ሆነውበታል፡፡

ምንጭ፡- (ወይ አዲስ አበባ መፅሄት፣ቅፅ 1፣ቁጥር 8፣2013 ዓ.ም)

❖ አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. እ.ኤ.አ በ2019 በዓለም ዙሪያ የእርግዝና መከላከያ እየፈለጉ አገልግሎቱን ያላገኙ ሴቶች ምን ያህል ናቸው?
2. በስነ-ተዋልዶ ውስጥ ምን ምን አገልግሎት ይሰጣል?
3. በሀገራችን ኢትዮጵያ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን የመጠቀም ምጣኔ እ.ኤ.አ በ2019 በስንት በመቶ ከፍ አለ?
4. እ.ኤ.አ በ2019 በዓለም ዙሪያ እድሜያቸው ከ15-49 ዓመት የሆኑ ሴቶች ብዛት ስንት ነበር?
5. የምንባቡን ዋና መልዕክት አጠር አድርጋችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ?

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት በምንባቡ አውድ መሰረት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ፍቱን | ሀ. ያልተረጋገጠ መረጃ |
| 2. አሉባልታ | ለ. የተስፋፋ |
| 3. ማነቆ | ሐ. ችግር |
| 4. እምብርት | መ. ማሳደግ |
| 5. ስር የሰደደ | ሠ. ወጥመድ |
| 6. ማጎልበት | ረ. ሃያ አምስት ዓመት |
| 7. ሩብ ምዕተ-ዓመት | ሰ. ወሳኝ |
| | ሸ. መሰረት |

ተግባር ሶስት፡-

ከላይ የቀረበውን ምንባብ በየተራ እየወጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

ተግባር አራት፡-

ተማሪዎች ከታች የቀረበውን ስዕል መሰረት በማድረግ የተመልዕክት የሀሳብ ፍሰቱን ጠብቃችሁ አንቀፅ ፃፉ፡፡



## ክፍል አራት፡- ጽህፈት

ማስታወሻ

ኢ-መደበኛ ፅሁፍ

ፅሁፍ በአጠቃቀም ጊዜ ሁለት መልኮች አሉት፡፡ እነሱም፡-መደበኛና ኢ-መደበኛ ፅሁፍ ናቸው፡፡

1. መደበኛ ፅሁፍ፡- ይህ የፅሁፍ አይነት በመስሪያ ቤቶች፣ በመጽሄቶች፣ በጋዜጦች ፣ በሬድዮ ዝግጅቶች ፣በትምህርት ቤቶች እና በሌሎችም ማህበራዊ መስኮች የምንጠቀምበት የጽሁፍ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- አባቴ ትናንት ማታ ደውሎልኝ በጣም ተገርሜ ነበር፡፡ ወዲያው ወደ ክፍል እንደገባሁ የክፍል ጓደኞቼ ዛሬኮ ልደትሽ ነው ብለው ይበልጥ አስገረሙኝ፡፡ ምን አይነት ተዓምር ነው!

2. ኢ-መደበኛ ፅሁፍ ለሀሳብ ቅደም ተከተሉ፣ ለድምፀቱ መለዋወጥ፣ ለሰዋስዋዊ ቅንብሩ፣ ለቃላት መረጣው፣ ... እምብዛም ጥንቃቄ የማያደርግ የጽሁፍ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ፋዘር ትናንት ደውሎልኝ በጣም ሰርፕራይዝ አድርጎኝ ነበር፡፡ ወዲያው ወደ ክላስ እንደገባሁ ክላስ ሚቶቹ ዛሬኮ <<በርዝደይሽ ነው>> ብለው ይበልጥ ሰርፕራይዝ አደረጉኝ፡፡ አሜዚነግ ነው!

ለ. ባኤላ ለመግዛት ተገበያ ሄጄ፣ ጀምበሪቱ አናት አናቴን ወቅታኝ የራስ ህመሜን ቀሰቀሰችብኝ፡፡ እንዲሁ ስደናበር ተቤቴ ልደርስ ጥኢት ሲኽረኝ ዝናቡ መዓቱን ለኽኽብኝ፡፡

ሐ. አባቴ ከች ሲል ሀርድ ሊበጥስብኝ መስሎኝ ከቤታችን ጓዳ አንድ ጥግ ላይ ሻግ አልኩኝ፡፡ ሲስተር ልታስፎግረኝ መስሎኝ አረ ሙድ የለውም አልኳት፡፡

ተግባር አንድ፡-

ከላይ በቀረበው ማስታወሻ ውስጥ ያሉትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ባለ ሶስት አንቀፅ ኢ-መደበኛ ፅሁፍ ጻፉ፡፡

ተግባር ሁለት፡-

የፃፋችሁትን አንቀፅ መሰረት በማድረግ ከጓደኞቻችሁ ጋር የእርስ በርስ እርማት ተሰጣጡ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

**አዳዲስ ቃላት**

ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን አንቀጽ በማንበብ ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀይሉ ከስኬት ይደርስበታል የተባለው ስራ ውጤት አልባ ሆኗል፡፡ ይህ ክፉ አጋጣሚ ደግሞ ለቤተሰቦቹ እና ለእርሱ ተስፋ የሚያስቆርጥ መሆኑ አልቀረም፡፡ ውሎ አድሮ አብረውት ይሰሩ የነበሩ ጓደኞቹ ከጥሩ ደረጃ ደረሱ፡፡ ሀይሉ ግን ስራውን የማሻሻል እድል ሳያገኝ ቀረ፡፡

ሀ. ስኬት --------------------- መ. ደረጃ --------------------

ለ. አልባ ---------------------- ሠ. እድል ------------------

ሐ. ውሎ አድሮ ---------------

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

> **ማስታወሻ**
>
> **የአሁን ጊዜ**
>
> ጊዜ የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት (የወደፊት) ተብሎ በሶስት ይከፈላል፡፡ የአሁን ጊዜ የሚባለው አንድ በአሁን ሰዓት የሚፈፀም ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ድርጊትን የሚገልጽ የጊዜ አይነት ነው፡፡ አሁን የሚባለው አንድ ሰው ስለአንድ ድርጊት ንግግር የሚያደርግበት ጊዜ ነው፡፡ የአሁን ጊዜ ግስ <<እየ->>የሚል ምዕላድ ሊያስቀድምና <<ነው>> የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ምሳሌ፡- ቅድስት ምሳዋን እየበላች ነው፡፡

### ተግባር አንድ፦

ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች የአሁን ጊዜ ከሆኑ አዎ ካልሆኑ አይደለም በማለት መልሱ፡፡

1. መሳፍንት ትናንት ወደ ጎንደር ሄደ፡፡
2. ሙሉዓለም ነገ ወደ ዩኒቨርሲቲ ይጓዛል፡፡
3. ሳሙኤል ፈተና ስለደረሰበት እያጠና ነው፡፡
4. ትናንት መምህራችን የቤት ስራችንን አርመው መለሱልን፡፡
5. እናቴ ገበያ ሄዳ ነበር፡፡
6. የስፖርት ክፍለ ጊዜ በመሆኑ ተማሪዎቹ ኳስ እየተጫወቱ ነው፡፡

### ተግባር ሁለት፦

ከታች በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት የአሁን ጊዜን የሚያመለክቱ አምስት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፦ ሀ. ሀና ወደ ገጠር እየሄደች ነው፡፡

ለ. ፍራኦል ፈተና በመፈተን ላይ ነው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ክርክር፣ ኢ- መደበኛ ጽሁፍና የአሁን ጊዜ የሚሉ ይዘቶችን ተምረናል፡፡

ክርክር ሁለት ሰዎች ወይም ሁለት ቡድኖች ዳኞችን በመሰየም የሚያደርጉት ስርዓት ያለው ሙግት ነው፡፡

- ኢ-መደበኛ ፅሁፍ ለሀሳብ ቅደም ተከተሉ፣ ለድምፀቱ መለዋወጥ፣ ለሰዋስዋዊ ቅንብሩ፣ ለቃላት መረጣው፣ ... እምብዛም ጥንቃቄ የማያደርግ የጽሁፍ አይነት ነው፡፡
- የአሁን ጊዜ የሚባለው አንድ በአሁን ሰዓት የሚፈፀም ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ድርጊትን የሚገልጽ የጊዜ አይነት ነው፡ ፡ አሁን የሚባለው አንድ ሰው ስለአንድ ድርጊት ንግግር የሚያደርግበት ጊዜ ነው፡፡ የአሁን ጊዜ የሆነ ግስ እየ- የሚል ምዕላድ ሊያስቀድምና ነው የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የልጆችን ቁጥር መመጠን ምን ጠቀሜታ እንዳለው ዘርዝሩ፡፡
2. ባለ አንድ አንቀፅ ኢ-መደበኛ ፅሁፍ ፃፉ፡፡
3. ሶስት የአሁን ጊዜን የሚያመለክቱ ዐረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት (፫)

## በጎ ፍቃደኝነት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-**

- ያዳመጣችሁትን ታንፀባርቃላችሁ፡፡
- ስለበጎ ፍቃደኝነት ፅንሰ ሀሳብ ትገልፃላችሁ፡፡
- የፅሁፉን ዋና ሀሳብ መልሳችሁ ትገልፃላችሁ፡፡
- በጎ ፍቃደኞች በምን በምን ዙሪያ እንደተሰማሩ ትለያላችሁ፡፡
- ከፅሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ታወጣላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### “የበጎ ፍቃደኝነት ተምሳሌት”



❖ ቅድመ ማዳመጥ

1. ከላይ በቀረበው ስዕል ላይ የምትመለከቷቸውን ሴት ታውቋቸዋላችሁ?
   ካወቃችዋቸው በሬድዮ ወይም በቴሌቪዥን ስእሳቸው ምን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. “ኦቲዝም” ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

❖ የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር

“የበጎ ፍቃደኝነት ተምሳሌት” የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

❖ አዳምጦ መረዳት

**ተግባር አንድ፡-**

“የበጎ ፍቃደኝነት ተምሳሌት” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ዘሚ የኑስ የተወለዱት መቼ እና የት ነው?
2. <<ለራሴ በገባሁት ቃል ኪዳን መሰረት>> ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው?
3. ዘሚ የኑስ ለወጣት ልጆች ካስተላለፉቸው መልዕክቶች መካከል ቢያንስ ሶስቱን ተናገሩ።
4. ባለታሪኳ ጆይ የኦቲዝም ማዕከልን ለመመስረት ያነሳሳቸው ምክንያት ምንድን ነው?
5. ከበጎ ፍቃደኝነት ውጭ ባለታሪኳ በምን ስራ ላይ ተሰማርተው ነበር?
6. የታሪኩን ዋና መልዕክት ባጭሩ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ተግባር ሁለት፡-**

በ “ሀ” ስር ለቀረቡት ቃላት በ “ለ” ስር ከተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ደጃፍ | ሀ. ተጎናፀፉ |
| 2. ክህሎት | ለ. ውጤት |
| 3. እርግማን | ሐ. ችሎታ |
| 4. በቅጡ | መ. በር |
| 5. በርካታ | ሠ. ፍርጃ |
| 6. ስኬት | ረ. በደንብ |

7. ተቀዳጁ
8. አሻራ

ሰ. ብዙ
ሸ. ውድቀት
ቀ. አስተዋፅኦ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

ከጓደኞቻችሁ ጋር ጥንድ ጥንድ በመሆን እርስ በርስ ስለመረዳዳት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ንግግር አድርጉ፡፡





## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### "በጎ ፍቃደኝነት ምንድን ነው?"

❖ ቅድመ ንባብ

"በጎ ፍቃደኝነት ምንድን ነው?" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ የሰንጠረዡን ሁለት ረድፎች በደብተራችሁ ላይ በትክክል ሙሉ፡፡ ምንባቡ ካለቀ በኋላ ተመልሳችሁ ያወቅሁት የሚለውን በትክክል ሙሉ፡፡

| የበጎ ፍቃደኝነት | | |
|---|---|---|
| ስለ በጎ ፍቃደኝነት የማውቀው | ስለ በጎ ፍቃደኝነት ማወቅ የምፈልገው | ስለ በጎ ፍቃደኝነት ያወቅሁት |
| - <br> - <br> - <br> - | - <br> - <br> - <br> - | - <br> - <br> - <br> - |

❖ የማንበብ ሂደት

ተግባር

"በጎ ፍቃደኝነት ምንድን ነው?" የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ምላሽ እየሠጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

## "በጎ ፍቃደኝነት ምንድን ነው?"

በጎ ፍቃደኝነት ማለት በግለሰብ ወይም በቡድን የሚከናወን ግለሰብን፣ ቡድንን ወይም ድርጅትን ለማጎልበትና ለማሳደግ ያለምንም የገንዘብ ድጎማ አገልግሎቶችን የምንሰጥበት ሂደት ነው፡፡ በጎ ፍቃደኝነት ለበጎ ፍቃደኛው እና ለማህበረሰቡ በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ በጎ ፍቃደኝነት የክህሎት ልህቀት ከማጎልበቱም ባሻገር ብዙውን ጊዜ በበጎነት ለመራመድ እና የሰዎችን ሰብዓዊ ህይወት ለማሻሻል ይጥራሉ፡፡ ብዙ በጎ ፍቃደኞች በሰለጠኑበት ወይም በተካኑት ሙያ ለምሳሌ፡- እንደ ህክምና፣ ትምህርት ወይም ድንገተኛ እርዳታ የመሳሰሉ ዘርፎች የሚያገለግሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት እንደ አስፈላጊነቱ አገልግሎት ይሠጣሉ፡፡

እ.ኤ.አ ታህሳስ 5 ቀን 2011 ዓ.ም በዓለም ዙሪያ 80 ያህል ሀገሮችን ያቀፈ የመጀመሪያው የዓለም የበጎ ፍቃደኞች መርሀ ግብር በተባበሩት መንግስታት ስር በአሜሪካ ኒዮርክ ተቋቁሟል፡፡ የዚህ መርሀ ግብር

ዋና ዓላማው በበጎ ፍቃደኝነት ላይ የተሻለ ግንዛቤን ከማስፋቱም ባሻገር የ21ኛውን ክፍለ ዘመን አዳዲስ እሳቤዎችን ከበጎ ፍቃደኝነት ዓለም አቀፍ ወሰን እና ተመጣጣኝነት ጋር የተዋሀደ ዓላማ ይዞ ነበር የተነሳው፡፡

በመላው ዓለም ባሉ አብዛኛው ህብረተሰብ ውስጥ በጎ ፍቃደኞች በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች በፍቃደኝነት በልዩ ልዩ ተግባራት በመሳተፍ የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ለማሟላት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ከማበርከታቸው ባሻገር ለወገኖቻቸው በእውቀታቸው እና በጉልበታቸው እያገለገሉ የመንፈስ እርካታን በሰፊው እየሸመቱ ይገኛሉ፡፡

*ተማሪዎች ስለ በጎ ፍቃደኝነት ምን ተገነዘባችሁ? በቀጣዩ ምንባብ በሀገራችን ስላለው የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት ምን የሚወራ ይመስላችኋል?

በሀገራችን በጎ ፍቃደኝነት የማህበረሰቡ የእለት ተእለት የህይወት መገለጫ ነው፡፡ ለችግረኞች፣ ለአረጋዊያን እና ለወላጅ አልባ ህፃናት ተሰብስቦ በደቦ በማረስ፣ በመውቃትና ሰብስቦ ጎተራ በመክተት የበጎ ፍቃድ ስራዎችን ለበርካታ ዘመናት ሲያከናውን ኖሯል፡፡ ከዚህም ባሻገር ካመረተው እህል ከፍሎ ከመስጠት ጀምሮ በጉልበቱና በሙያው ለችግረኞች መድረስን የሚያውቅ ህዝብ ነው፡፡

ኢትዮጵያዊያን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡት በችግር ወቅት ብቻ አይደለም፡፡ በደስታ ጊዜም ማህበረሰቡ እርስ በእርስ ይረዳዳል ለዚህም ማሳያነት የደቦ ወይም የወንፈል ባህልን መጥቀስ ይቻላል ይህን ለረጅም ጊዜ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣውን መልካም የማህበረሰብ ልማድ በተጠናከረ መልኩ በማስቀጠል በሀገራችን

ባሉ አንገብጋቢ ጉዳዮች እና ትኩረት በሚገባቸው ተግባራት ዙሪያ ወጣቱን የማህበረሰብ አካል በማንቃትና በማሳተፍ የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎትን ማስቀጠልና ማስፋፋት ለሀገር እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ምንጭ፡- (ኤ.ሲ.ፒ.ኤሲ. የትምህርት ቦርድ የት/ቤት የበጎ ፍቃደኞች መመሪያ ማኑዋል)

## ❖ አንብቦ መረዳት

### ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. የዓለም የበጎ ፍቃደኞች መርሀ ግብር በተባበሩት መንግስታት የተቋቋመው መቼ ነው?
2. በዓለም ላይ ምን ያህል ሰዎች በበጎ ፍቃደኝነት ተግባራት ላይ ተሰማርተዋል ተብሎ ይገመታል?
3. በመጨረሻው አንቀፅ ላይ ይህን ለረጅም ጊዜ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ የማህበረሰብ ልማድ የተባለው ምንድን ነው?
4. በጎ ፍቃደኝነት ማለት ምን ማለት ነው? ምንስ ጥቅም አለው?
5. በጎ ፍቃደኝነት ለሀገራችን አዲስ ጉዳይ ነው፡፡ በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? መልሳችሁን በምክንያት በማስደገፍ መልሱ፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

ከታች በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት እና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የዓለም የበጎ ፍቃደኞች <u>መርሀ ግብር</u> በኒዮርክ ተቋቋመ፡፡
2. ለረጅም ጊዜ <u>ሲወርድ ሲወራረድ</u> የመጣ የማህበረሰቡ ልማድ ነው፡፡
3. እህሉን <u>ከጎተራ</u> ከተቱት፡፡
4. የመንፈስ እርካታን በሰፊው <u>እየሸመቱ</u> ነው፡፡
5. ያለምንም የገንዘብ <u>ድጎማ</u> ይሰራሉ፡፡
6. በጎ ፍቃደኝነት የክህሎትን <u>ልህቀት</u> ይጨምራል፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

**ማስታወሻ**

**የማግባቢያ ፅሁፍ**

የማግባቢያ ፅሁፍ አይነት ሰዎችን ለአንድ ዓለማ ወይም ተግባት ለመቀስቀስ እና ለማሳመን የሚረዳ የጽሁፍ ዐይነት ነው፡፡ አግባቢ ጽሁፍ በአንባቢው አስተሳሰብ ላይ ጫናን በመፍጠር አመለካከቱን ለመቀየር ጥረት ያደርጋል፡፡

ምሳሌ፡-

አረጋሽ ዘለቃ እባላለሁ፤ በዚህ ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን በዘንድሮው ዓመት በሚካሄደው የተማሪዎች ፓርላማ እጩ ተወዳዳሪ ነኝ፡፡ እኔን ብትመርጡ እናንተን በመወከል በርካታ ስራዎችን በትጋት እሰራለሁ፡፡ ከዚህም ውስጥ፤ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር እና ወተመህ አባላት ጋር በመነጋገር ወቅታዊና አዳዲስ መፃህፍት ተገዝተው በትምህርት ቤታችን ቤተ-መፃህፍት ውስጥ እንዲገቡ አደርጋለሁ፡፡ እዲሁም የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ለመማር ማስተማሩ ምቹ ይሆን ዘንድ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በመመካከር እንዲሻሻል አደርጋለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የስነ-ምግባር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ አደርጋለሁ፡፡ በመጨረሻም በትምህርት ቤቱ በሚከናወኑ ወቅታዊ እና አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ በግንባር ቀደምነት በመሳተፍ ማንኛውንም ጥቅማጥቅም አስከብርላችኋለሁ፡፡ በመሆኑም በመጭው ምርጫ የእናንተን ድምጽ እንደማገኝ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

ተግባር አንድ፦

ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ መምህራችሁ የሚያዟችሁን መመሪያ በመከተል ባለ ሶስት አንቀፅ የማግባቢያ ጽሁፍ ፃፉ።

ተግባር ሁለት፦

የፃፋችሁትን አንቀፅ መሰረት በማድረግ ከጓደኞቻችሁ ጋር የእርስ በርስ እርማት ተሰጣጡ።

## ክፍል አምስት፦ ቃላት

### ድርብ ቃላት

| ማስታወሻ |
| --- |
| **ድርብ ቃላት**<br>ድርብ ቃላት ማለት ሁለት የተለያዩ ፍቺ ያላቸው ቃላት አንድ ላይ በመምጣት ለሌላ ሶስተኛ ነገር መጠሪያ እና የተለያየ ትርጉም ሲሰጡ ነው።<br>ምሳሌ፦ <<ትምህርት ቤት>> የሚለው ድርብ ቃል <<ትምህርት>> እና <<ቤት>> ከሚሉ ሁለት ቃላት የተመሰረተ ነው። እንደዚሁ ሁሉ ብረት ድስት፣ ሀኪም ቤት፣ ብረት ምጣድ፣ አየር መንገድ፣ ፖሊስ ጣቢያ ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው። |

ተግባር አንድ፦

ከላይ በማስታወሻው በቀረበው ምሳሌ መሰረት የምታውቋቸውን ስድስት ድርብ ቃላት ፃፉ።

ተግባር ሁለት፦

"በጎ ፍቃደኝነት ምንድን ነው?" ከሚለው ምንባብ ውስጥ ከአንደኛው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አስር ተዘውታሪ ቃላትን በማውጣት ፃፉ።

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

**ነጠላ እና ብዙ ቁጥር**

ነጠላ ቁጥር የሚባለው ንጥል ወይም አንድ ነገርን ብቻ የሚገልፅ ነው፡፡ ብዙ ቁጥር የሚባለው ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን የሚገልፅ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

| ነጠላ ቁጥር | ብዙ ቁጥር |
|---|---|
| ቤት | ቤቶች |
| ቃል | ቃላት/ቃሎች |
| ተማሪ | ተማሪዎች |

ተግባር፡-

ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ነጠላ እና ብዙ ቁጥር በማለት ከለያችሁ በኋላ ዐረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ካህን | ታሪክ | ጥሬ |
| ሰማያት | አልባሳት | ግጥም |
| ቀን | በሬዎች | መጻሕፍት |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ ማዳመጥ መመሪያ፣ የማግባቢያ ፅሁፍ፣ ድርብ ቃላትና ነጠላ ቁጥር ተምረናል፡፡
- ማዳመጥ የሚከናወነው በንቃት በመሆኑ ንቃትን ከማይጠይቀው ከመስማት እጅግ ይለያል፡፡ በማዳመጥ ሂደት ውስጥ ሁልጊዜም መረዳትና ማገናዘብ ይኖራል፡፡ ማዳመጥ የሰው ልጅ ተግባቦታዊ ሂደት መሰረት ነው፡፡ ከመናማገር፣ ከመጻፍና ከማንበብ በበለጠ ብዙ ጊዜ የምናጠፋው በማዳመጥ ነው፡፡ የማዳመጥን ችሎታ ለማሳደግና ለማዳበርም ንቁ ተሳታፊ መሆን፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ትኩረት ማድረግ ወዘተ. ተገቢ ነው፡፡
- የማግባቢያ ፅሁፍ ሰዎችን ለአንድ ዓላማ ወይም ተግባር ለመቀስቀስ እና ለማሳመን የሚረዳ የጽሁፍ ዓይነት ነው፡፡ አግባቢ ጽሁፍ በአንባቢው አስተሳሰብ ላይ ጫናን በመፍጠር አመለካከቱን ለመቀየር ጥረት ያደርጋል፡፡
- ድርብ ቃላት የምንለው ሁለት የተለያዩ ፍቺ ያላቸው ቃላት አንድ ላይ በመምጣት ለሌላ ሶስተኛ ነገር መጠሪያ በመሆን ሲያገለግሉ ነው፡፡
- ነጠላ ቁጥር የሚባለው ንጥል ወይም አንድ ነገርን ብቻ የሚገልፅ ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. የተሰጣችሁን ቃላት በመጠቀም ድርብ ቃላት መስርቱ።

ሀ. አልጋ
ለ. አየር
ሐ. ዳቦ
መ. ጦር
ሠ. ሰርግ
ረ. ሰማይ

2. የሚከተሉትን ነጠላ ቁጥሮች ወደ ብዙ ቁጥር ቀይሩ

ሀ. ፍየል
ለ. ገዳም
ሐ. መስጊድ
መ. መምህር
ሠ. ወፍ

# ምዕራፍ አራት (፬)

## የታዋቂ ሰዎች የህይወት ታሪክ

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-

- በማዳመጥ ታብራራላችሁ፡፡
- የህይወት ታሪክን ምንነት ትገልፃላችሁ፡፡
- ከፅሁፉ ውስጥ የምክንያት እና የውጤት ግንኙነትን ትለያላችሁ፡፡
- ሰው የህይወት ታሪክ ትፅፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### "ዓለምፀሐይ፤ የሀገር ፀሐይ"



❖ ቅድመ ማዳመጥ

1. ከርዕሱ እና ከምስሉ ምን እንደተረዳችሁ ግለፁ፡፡
2. የአንድን ሰው የህይወት ታሪክ ስንፅፍ ምን ምን ነገሮች መካተት ያለባቸው ይመስላችኋል?
3. በምስሉ ላይ ያሉት ባለታሪክ በምን ስራ ላይ የተሰማሩ ይመስላችኋል?

❖ የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር

"ዓለምፀሐይ፤ የሀገር ፀሐይ" የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ቁልፍ ቃላትን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

“ዓለምፀሐይ፤ የሀገር ፀሐይ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. አለምፀሀይ ወዳጆ እንደተወለዱ አባታቸው ለትምህርት የሄዱት የት ሀገር ነበር?
2. ባለታሪኳ የሙዚቃ አስተማሪዬ ነው ያሉት ማንን ነው?
3. አለምፀሀይ ለህፃናት የኪነ-ጥበብ መርሃ ግብር ያዘጋጁ የነበረው የት በሚገኘው የህፃናት አምባ ነው?
4. በምንባቡ ውስጥ አስደማሚው ባለቅኔ የተባሉት ማን ነው?
5. <<እኔን ለሌሎች ምሳሌ አድርገው >>ስትል ምን ማለታቸው ነው?
6. ባለታሪኳ ለወጣቶች ካስተላለፉት መልዕክት መካከል ቢያንስ ሶስቱን ጥቀሱ፡፡
7. አለምፀሀይ የሐገር ፀሀይ የተባሉት ለምንድን ነው?

ተግባር ሁለት፡-

ካዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ የተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ወንድሜ የበርካታ ተሰጥኦዎች ባለቤት ነው፡፡
2. የኮተቤ ሜትሮፖሊታን መምህራን ዩኒቨርሲቲ ባሁን ሰዓት ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት እጩ መምህራንን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡
3. አባቶቻችን አድዋ ላይ የፈፀሙት ጀግንነት ዘመን አይሽሬ ነው፡፡
4. በጦርነት ውስጥ በአብዛኛው ጊዜ የጉዳት ሰለባ የሚሆኑት

ህጻናት፣ ሴቶችና አረጋዊያን ናቸው፡፡

5. አርቲስቷ በመድረክ ላይ በመተወን ከፍተኛ አድናቆትን አትርፋለች፡፡
6. ለአካባቢያችን ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ በርካታ ግለሰቦች ሽልማት ተሰጠ፡፡
7. ናትናኤል በትንሽ በትልቁ መሚገት ይወዳል፡፡
8. ሲፈን በትምህርቷ ከፍተኛ ውጤት ስላመጣች ጮቤ ረገጠች፡፡
9. አስተዋይነት ታላቅ ጥበብ ነው፡፡
10. የላይ አምባ ልጆች የገና ጨዋታ ውድድሩን አሸነፉ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ማስታወሻ

### የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ

በፅሁፍ ወይም በንባብ የቀረበ የአንድ ግለሰብ ታሪክ የሕይወት ታሪክ ይባላል፡፡ የሕይወት ታሪክ በአብዛኛው የሚዘጋጀው በታላላቅ ሰዎች ሕይወት ዙሪያ ነው፡፡ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ በሁለት ይከፈላል፡፡

እነሱም፡- የራስ የህይወት ታሪክ እና የግለሰብ የህይወት ታሪክ በመባል ይታወቃሉ፡፡

1. የራስ የህይወት ታሪክ፡- የራስ የህይወት ታሪክ ሲፃፍ
   - የትውልድ ስፍራን እና ዘመንን መግለፅ
   - ስለ አስተዳደግ ሁኔታ መፃፍ
   - የትምህርት ደረጃን መግለፅ
   - ያበረከትነውን አስተዋፅኦ በቅደም ተከተል መፃፍ
   - ታሪካችንን ቀላል እና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ማቅረብ

2. <u>የግለሰብ የህይወት ታሪክ</u>:-

- ታሪኩ ስለሚፃፍለት ግለሰብ መረጃ መሰብሰብ፣ ማደራጀት እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
- የትውልድ ቦታና ዘመንን፣ የሞተ ከሆነ የሞተበትን ዘመን መግለፅ
- ስለአስተዳደጉ ሁኔታ መግለፅ
- ስለፈፀማቸው ተግባሮች እና ስላበረከታቸው አስተዋጽኦዎች ማተት
- ታሪኩን ቀላል እና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ማቅረብ ይኖርብናል

ተግባር አንድ:-

ከላይ የቀረበውን መመሪያ ካነበባችሁ በኂላ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩበት::

ተግባር ሁለት:-

ከታች የቀረበውን ሰንጠረዥ መሰረት በማድረግ የዶክተር ሀዲስ አለማየሁን የሕይወት ታሪክ በማቀናጀት አጠር አድርጋችሁ በንግግር አቅርቡ::

| | |
|---|---|
| የባለታሪኩ ስም | ክቡር ዶክተርሀዲስ አለማየሁ |
| የአባት ስም | ቄስ አለማየሁ ሰለሞን |
| የእናት ስም | ወይዘሮ ደስታ አለሙ |
| የትውልድ ቦታ | ደብረ ማርቆስ አውራጃ ጎዛምን ወረዳ |
| የትውልድ ዘመን | ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ. ም |
| የተሰማሩበት የስራ መስክ | ደራሲ፣ አምባሳደር (1935-1966 በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለሀገራቸው አገልግለዋል |

| | |
|---|---|
| የፃፏቸው መፃህፉት በጥቂቱ | ፍቅር እስከ- መቃብር፣ተረት ተርት የመሰረት፣ወንጀለኛው ዳኛ ወዘተ. |
| ለሌሎች አርዓያ የሆኑበት ተግባር | ለኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ በጣሊያን ወረራ ወቅት ለሀገራቸው በአርበኝነት አገልግለዋል፡፡ |
| ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩበት ቀን | ህዳር 26 1996 ዓ. ም |

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### “አንጋፋው የአትሌቲክስ አባት”


❖ ቅድመ ንባብ

1. ፈሊጣዊ ንግግር ሲባል ምን ማለት ነው? ከምታውቋቸው ፈሊጣዊ ንግግሮች ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡
2. በዓለም አደባባይ ኢትዮጵያን አትሌቶች ታዋቂ የሆኑት በየትኛው ርቀት ይመስላችኋል?
3. ከታች በምስሉ የምትመለከቱት አትሌት ማን ይባላሉ?

❖ የማንበብ ሂደት

ተግባር አንድ፡-

“አንጋፋው የአትሌቲክስ አባት” የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ ድምፅ እያሰማችሁ በየመሀሉ ለምትጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ እየሰጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡





## “አንጋፋው የአትሌቲክስ አባት”

“ለኢትዮጵያ ህዝብ እና ለሀገሬ በገባሁት ቃል ኪዳን መሰረት ሬሳዬ የሚወጣው ከሩጫው ሜዳ ነው፡፡” የሚሉት አትሌት ዋሚ ቢራቱ የተወለዱት ጥር 11 ቀን 1907 ዓ.ም ነው፡፡ የአቶ ቢራቱ በራቄ እና የወይዘሮ ወርቄ አያና ልጅ የሆኑት ዋሚ፣ የትውልድ ስፍራቸው ከአዲስ አበባ ከተማ 21 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ሱሉልታ ወረዳ አካኮና መነ አብቹ በተባለው ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው፡፡

ዋሚ የስድስት ወንዶች እና የአምስት ሴት ልጆች አባት፣ የሃያ አንድ ልጆች አያት እና የአስራ አንድ ልጆች ቅድመ አያት ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ስፖርት ፈር ቀዳጅ ከሆኑት መካከል አንዱ አትሌት ሻለቃ ዋሚ ቢራቱ በ93 ዓመት እድሜያቸው የካቲት 18 ቀን 1999 ዓ.ም በጃን ሜዳ በተካሄደው ሃያ አራተኛው ሀገር አቋራጭ ውድድር በአዋቂዎች ምድብ ከነስለሺ ስህን እና ታደሰ ቶላ እንዲሁም ከሌሎች አትሌቶች ጋር ተሰልፈው ሲሮጡ ታይተዋል፡፡

የልጅነት ዘመን ትዝታቸውን ከጊዜው መርዘም አኳያ እጅግ በጣም ሩቅ እና አውስተው የማይጨርሱት መሆኑን ቢናገሩም፣ በአጭሩ "እኔ በወጣትነትና በልጅነት ዘመኔ እኩዮቼን እና የበላዮቼን ከአስር እስከ አስራ ሁለት ጊዜ በላይ በሩጫ ደርቤ አልፋቸው ነበር፡፡ ወላጆቼ ያሳደጉኝ በማር እና በወተት በጨጨብሳ እና በጭኮ ነው፡፡ ከእረኝነት ወደ ግብርናው ሞያ የተሸጋገርኩት እንደ ሰንጋ ፈረስ እየተቀለብኩ ሲሆን የጎደለብኝ ነገር አልነበረም፡፡ አፍላ ወጣት ሳለሁ እናቴ ከገበያ ቡና ጠቅልላ ያመጣችበትን የጋዜጣ ቅዳጅ ተመለከትኩ፡፡ በጋዜጣው ላይ አንድ ፀጉረ ልውጥ ሰው ሲሮጥ ይታያል፤ ያ ጋዜጣ ስለ ሰውየው አሸናፊነት እና ጥንካሬ የሚገልጽ ሀሳብ አስፍረዋል፡፡ እሱን ከተመለከትኩ በኋላ ለአራት ዓመታት ያህል በአእምሮዬ ሳወጣ ሳወርድ ቆየሁ፡፡"

*ተማሪዎች አትሌት ዋሚ ቢራቱ የት አካባቢ ተወለዱ? በቀጣዩ የታሪክ ክፍል ምን የሚያጋጥማቸው ይመስላችኋል?

አትሌት ዋሚ ወደ አትሌቲክስ ስፖርት የመጡት መስከረም 5 ቀን 1945 ዓ.ም ወደ ውትድርናው ዓለም ከገቡ በኋላ ነው፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ ግዛት በነበረችው አስመራ ውስጥ በነባር እና በአዲስ ወታደሮች መካከል በተደረገው የሩጫ ውድድር አንደኛ ወጡ፡፡ በዚህ አይነት መንገድ የአትሌቲክሱን ህይወት "ሀ" ብለው ጀመሩ፤ በሀገር ውስጥ የማራቶን ውድድር ሲኖር የሚቀናቀኗቸው ጠፉ፡፡ "በባዶ እግሬ በመሮጥ እና አበበ ቢቂላን ወደ ውድድሩ ዓለም በመሳብ፣ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፋና ወጊ ነኝ" የሚሉት ዋሚ ቢራቱ በ1953 ዓ.ም በጃፓን ቶኪዮ ላይ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የማራቶን ውድድር ሻምበል አበበ ቢቂላን ተከትለው ሁለተኛ ወጥተዋል፡፡

ሀገራችንን በመወከል በምስራቅ አፍሪካ፣ በጃፓን በቼክ ሪፐብሊክ እና በቀድሞዋ ሰው ቤት ህብረት ተወዳድረው አመርቂ ውጤት

አስመዝግበዋል፡፡ ዋሚ በሀገር፣ በአህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በተካሄዱ ውድድሮች ሃምሳ አንድ ወርቅ፣ አርባ አራት የብር እና ሰላሳ የነሀስ ሜዳሊያዎችን ለመሸለም በቅተዋል፡፡ በተለይም በመስከረም 1996 ዓ.ም ቱሪዝም ኮሚሽን ባዘጋጀው ውድድር የሃያ አንድ ኪሎ ሜትሩን እሩጫ በ 2:05 ደቂቃ በመፈፀም አድናቆትን ያተረፉ አንጋፋ አትሌት ናቸው፡፡ የሻለቃ ዋሚ ቢራቱ ታሪክ እጅግ ረጅም፣ ሰፊና ጥልቅ ነው፤ ደማቁ ዋሚ በቀጣይ የአትሌቲክስ ታሪክ ሲወሱ የሚኖሩ አንጋፋ አትሌት ናቸው፡፡

ምንጭ፡- (ደማቆቹ፣ 2000ዓ.ም የአንዳንድ ኢትዮጵያውያን የሕይወት ውልብታ)

❖ አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. አትሌት ዋሚ ቢራቱ ወደ አትሌቲክሱ ዓለም የገቡት በቀጥታ ነበር፡፡
2. የባለታሪኩ ወታደራዊ ማዕረግ ሻምበል ነበር፡፡
3. ዋሚ ቢራቱ ወደ አትሌቲክስ ዓለም የተሳቡት በአንድ ብጣሽ ጋዜጣ ላይ ባዩት ምስል ነበር፡፡
4. የዋሚ ቢራቱ ልጆች ቁጥር ከልጅ ልጆቻቸው ቁጥር ይበልጣል፡፡
5. ዋሚ ቢራቱ በተለያዩ ውድድሮች ሃምሳ አንድ የወርቅ ሜዳሊያዎችን አግኝተዋል፡፡
6. አትሌቱ በ1953 ዓ.ም ቶኪዮ ላይ በተደረገው ውድድር ሻምበል አበበ ቢቂላን በማስከተል አንደኛ ወጥተዋል፡፡

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ከምንባቡ የወጡት ቃላት በ "ለ" ስር ካለው ተቃራኒ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. አመርቂ | ሀ. እድሜ ጠገብ |
| 2. አንጋፋ | ለ. ርቀት |
| 3. ያተረፉ | ሐ. የማይታወቁ |
| 4. አፍላ | መ. አጥጋቢ ያልሆነ |
| 5. ደማቅ | ሠ. ያላገኙ |
| | ረ. ደብዛዛ |

## ተግባር ሶስት፡-ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ማስታዎሻ

ማስታዎሻ በግል በማንበብ በጥንድ በመወያየት ከምንባቡ የወጡ ፈሊጣዊው ከምንባቡ በማውጣት ምሳሌያዊውን ከቤተሰቦቻችሁ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ ከመምህራችሁ ጋር ስለፍቻቸቸው ተወያዩበት

ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገር ከቋንቋ የአነጋገር ስልቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን የሚፈጠረውም በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ ቃላትን በልዩ ልዩ ዘዴ በመጠቀም ነው፡፡ ፈሊጣዊ አነጋገር እያንዳንዱ ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር በሚቀናጁበት ጊዜ መጀመሪያ የነበረውን ፍቺ ሙሉ በመሉ በመቀየር አዲስ ፍቺ የሚሰጥበት መንገድ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ “ሁለት ልብ” የሚለውን የሁለት ቃላት ቅንጅት ብንመለከት ወላዋይ (ለመወሰን የተቸገረ) የሚል ፍቺ ይሰጣል፡፡

ለ <<አመድ አፋሽ>> የሚለው ፍቺ ደግሞ ምስጋና ቢስ (የማይመሰገን) የሚል ፍቺ ይሰጣል፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታወሻ

**አያያዥ ቃላትና ሀረጋት**

አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት ለብቻቸው ትርጉም አይሰጡም፡፡ ነገር ግን ተግባር አላቸው፡፡

ይሄውም፡-

- -ከአንድ ሀሳብ ወደሌላ ሀሳብ ለመሸጋገሪያነት
- -የቀደመውን ሀሳብ ከሚቀጥለው ማጠናከሪያ ጋር ለማቆራኘት
- -አፍራሽ ወይም ተቃራኒ ሀሳቦችን ለማገናኘት
- -ለቀደመው ሀሳብ ምክንያት ሰጪ ሀሳብን ለማስከተል
- -የጊዜ ቅደም ተከተል ያላቸውን ሀሳቦች ለማያያዝ ወዘተ. ያገለግላሉ፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. ተጨማሪ ሀሳቦችን የሚያያይዙ፡- በተጨማሪም፣ እንዲሁም፣ ቀጥሎም…

ለ. ተቃራኒ ሀሳቦችን የሚያያይዙ፡- ይሁን እንጂ፣ የሆነው ሆኖ፣ ነገር ግን ፣ ዳሩ ግን…

ሐ. ምክንያት ሰጪ ሀሳብን ለማስከተል፡- በዚህ የተነሳ፣ ምክንያቱም፣ ስለዚህ…

መ. የጊዜ ቅደም ተከተል የሚጠብቁ ሀሳቦችን ለማያያዝ፡- ከዚህ በኋላ፣ ቀጥሎም፣ ወዲያው፣ በተመሳሳይ ጊዜ…

**ተግባር አንድ፡-**

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን አያያዥ ቃላት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው አስቀምጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ይሁን እንጂ | አለበለዚያ | እና |
| ወይም | ስለሆነም | በተጨማሪም |

1. በጣም ሀይለኛ ዝናብ ጣለ፤ -------------- ምንም ጉዳት አላደረሰም፡፡
2. ወደ ሀረር የሚሄደው በመኪና ------------ በባቡር ነው፡፡
3. የወባ በሽታ እየተስፋፋ መጥቷል፤ ------------ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡
4. መምህራችን ትዕግስትን -------- ከድጃን ቢሮ እንዲመጡ ነገረቻቸው፡፡
5. ጥሩ ውጤት ለማምጣት በርትተን ማጥናት ይኖርብናል፤ --------------- የወላጅና የመምህር ክትትል ያስፈልገናል፡፡
6. ገንዘቤን በሰላም መልስልኝ፤ ------------ፍርድ ቤት እገትርሃለሁ፡፡

**ተግባር ሁለት፡-**

አያያዥ ቃላትና ሀረጋት የሚለውን ማስታወሻ አንብባችሁ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ስድስት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

**ተግባር ሶስት፡-**

የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያን በመከተል የራሳችሁን ወይም አንድ የቅርብ ቤተሰባችሁን ሰው የህይወት ታሪክ ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተዘውታሪና ፈሊጣዊ ቃላት

#### ተግባር አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ተዘውታሪ ቃላት በመጠቀም ስድስት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. እንቅፋት
2. ለበሰ
3. ሰዓት
4. ቁርስ
5. ተከዘች
6. ቅንነት

#### ተግባር ሁለት፡-

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቂም አረገዘች | የሞቀ ቤት | ልብ አቁስል |
| አመድ አፋሽ | ሀሞቱ ፈሰሰ | ውሃ በላው |
| አፈ ቅቤ | አይኑ ቀላ | ስራ ፈት |
| ገፀ በረከት | ሰማይ ቅርቡ | ቅስሙ ተሰበረ |

1. ስንት የለፋሁበትን ስራ ---------------------፡፡
2. ---------------------ስለሆነ ጊዜውን ባልባሌ ቦታ ያጠፋል፡፡
3. በሰማው ዜና ---------------------፡፡
4. ለበርካታ ዓመታት ለሰራችው መልካም ስራ------------ ተበረከተላት፡፡
5. የነገሩትን የማይሰማ --------------- ነው፡፡
6. --------------------- እያለው ወደ ጎዳና ወጣ፡፡
7. ያልተፈጠረ ነገር የተፈጠረ አስመስላ የምታቀርብ ----------- ናት፡፡

8. ስራውን መስራት ሳይጀምር -------------------::
9. ከሉባባ ጋር በማይረባ ጉዳይ ስለተጣላች ----------------------::
10. ምንም እንኳን ለሰዎች መልካም ስራ ብትሰራም የማትመሰገን------------ ናት::

ተግባር ሶስት፡-

አስር ፈሊጣዊ ንግግሮችን ከነፍቻቸው በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

ተግባር አንድ፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማስታወሻና መመሪያ መሰረት ከታች ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ስማዊ ሀረጎች አውጡ::

1. ወንድሜ የስንዴ ዳቦ ሰጠኝ::
2. የታመመው ልጅ ወደ ሀኪም ቤት ሄደ::
3. ወይንሸት ጎበዝ ተማሪ ናት::
4. ሰሚራ ጥቁር እስክርቢቶ ገዛች::
5. ከድጃ የሀር ሹራብ ገዛች::

ተግባር ሁለት፡-

ከታች በቀረቡት ስማዊ ሀረጎች ዓረፍተ ነገር መስርቱ::

1. የገብስ ቆሎ
2. የቆዳ ጫማ
3. ቀይ ወጥ
4. አሮጌ መኪና
5. የላም ወተት
6. የስዕል ደብተር

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ ሕይወት ታሪክ፣ ፈሊጣዊ አነጋገር፣ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት እንዲሁም የሀረግ አይነቶችን ተምረናል፡፡
- በፅሁፍ ወይም በንባብ የቀረበ የአንድ ግለሰብ ታሪክ የሕይወት ታሪክ ይባላል፡፡ የሕይወት ታሪክ በአብዛኛው የሚዘጋጀው በታላላቅ ሰዎች ሕይወት ዙሪያ ነው፡፡ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም፡- የራስ የህይወት ታሪክ እና የግለሰብ የህይወት ታሪክ በመባል ይታወቃሉ፡፡
- ፈሊጣዊ ንግግር ከቋንቋ የአነጋገር ስልቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን የሚፈጠረውም በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ ቃላትን በልዩ ልዩ ዘዴ በመጠቀም ነው፡፡
- አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት ለብቻቸው ትርጉም አይሰጡም፡፡ ነገር ግን ተግባር አላቸው፡፡
- ሀረግ ትርጉም ያላቸው ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው፡፡ የሀረጉም ዓይነት በሀረጉ ውስጥ ዋና ሆኖ በሚገባው ቃል ዓይነት ይወሰናል፡፡ ዋናው ቃል ሆኖ የሚገባው ቃል የሀረጉ መሪ ይባላል፡፡ በዚህም መሰረት ስማዊ ሀረግ፣ ቅጽላዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሀረግ፣ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ እና መስተዋድዳዊ ሀረግ ተብለው በአምስት ይከፈላሉ፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ከታች ለቀረቡት ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡
   ሀ. ቃል አጠረው
   ለ. አመለቢስ
   ሐ. ሰማይ ጠቀስ
   መ. በሬ ወለደ
2. ከታች የቀረቡትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም የምክንያትና ውጤት ትስስርን የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡
   ሀ. ይሁን እንጂ
   ለ. እንዲሁም
   ሐ. በዚህ የተነሳ
3. ቀጥሎ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም ስማዊ ሀረግ መስርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቦርሳ | ኳስ | ሳጥን |
| ምንጣፍ | ሰው | አስክርቢቶ |

4. የሕይወት ታሪክ ሲጻፍ የሚካተቱ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡

# ምዕራፍ አምስት (፭)

## ውሃና ጥቅሙ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-

- ከሚደመጡ ንግግሮች ውስጥ ማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- ስለውሃ ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡
- የራሳችሁን አመለካከትና ፍላጎት ትገልፃላችሁ፡፡
- በርካታ ቃላትን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የውሃ አይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### "ውሃና የውሃ ጥቅም"







### ❖ ቅድመ ማዳመጥ

"ውሃና የውሃ ጥቅም" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ የሰንጠረዡን ሁለት ረድፎች በደብተራችሁ ላይ በትክክል ሙሉ። ምንባቡ ካለቀ በኋላ ተመልሳችሁ ያወቃችሁት የሚለውን ክፍል በትክክል ሙሉ።

| ውሃና የውሃ ጥቅም | | |
|---|---|---|
| ስለውሃና የውሃ ጥቅም የማውቀው | ስለውሃና የውሃ ጥቅም ማወቅ የምፈልገው | ስለውሃና የውሃ ጥቅም ተጨማሪ ያወቅሁት |
| -<br>-<br>-<br>- | -<br>-<br>-<br>- | -<br>-<br>-<br>- |

❖ የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር ፡-

“ውሃና የውሃ ጥቅም” የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስታወሻ በመያዝና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. ከሰውነታችን ውስጥ ምን ያህል በመቶው ውሃ ነው?
   ሀ. ሶስት አራተኛው ሐ. አንድ አራተኛው
   ለ. አንድ ሶስተኛው መ. ሁለት ሶስተኛው
2. ለውሃ መበከል ምክንያት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ከፋብሪካ የሚወጡ ጽዳጆች ሐ. የአረምና የተባይ ማጥፊያዎች
   ለ. ከመኖሪያ ቤት የሚወጡ ጽዳጆች መ. ሁሉም
3. የውሃ ብክለት በምን በምን ላይ ጉዳት ያደርሳል?
   ሀ. በጤና ለ. በኢኮኖሚ ሐ. በአካባቢ መ. ሁሉም
4. ከሚከተሉት ውስጥ የውሃ ወለድ በሽታ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ታይፎይድ ለ. ኮሌራ ሐ. ጉንፋን መ. ጃርዲያ
5. አንጎላችን ምን ያህል በመቶው ውሃ ነው?
   ሀ. ሰባ በመቶው ሐ. ሃያ ሰባት በመቶው
   ለ. ሰባ ሁለት በመቶው መ. ሰማንያ ሁለት በመቶው
6. በሁለተኛው አንቀፅ “ይህ ፈሳሽ” የተባለው ማን ነው?
   ሀ. ውሃ ለ. ደም ሐ. ምራቅ መ. ዘይት

### ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ዝውውር | ሀ. ውጤት |
| 2. ምቹ | ለ. ጎጂ |
| 3. ባግባቡ | ሐ. መንስኤ |
| 4. ምክንያት | መ. ተስማሚ |
| 5. ትስስር | ሠ. እንቅስቃሴ |
| 6. መርዛማ | ረ. መተግበር |
| 7. ማከናወን | ሰ. ጠቃሚ |
| | ሸ. ቁርኝት |
| | ቀ. በስርዓት |

### ተግባር ሶስት፡-

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የተሰጡትን ቃላት በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ብሂል | ያሳያሉ | ተዋህሲያን |
| አንፃር | አልሚ | መዛመት |

1. በሽታ የሚያስተላልፉትን----------------------ለማስወገድ እጃችንን በተደጋጋሚ መታጠብ አለብን፡፡
2. -------------------- ምግቦችን መመገብ ለጤንነት አስፈላጊ ነው፡፡
3. የኮሮና ቫይረስ --------------- አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡
4. ወጣቶች ያሰቡበት ደረጃ ላይ እንዳይደርሱ እንቅፋት ከሆኑት ነገሮች አደንዛዥ እጽ አንዱ እንደሆነ ጥናቶች ----------------
5. "የውሃና የእናት መጥፎ የለውም" የሚል----------- በሀገራችን አለ፡፡
6. ውሃ ከጥቅሙ --------------- ተገቢው ትኩረት አልተሰጠውም፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፡-

ውሃና ጥቅሙ በሚል ርዕስ ካዳመጣችሁት ምንባብ የወሰዳችሁትን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ስለውሃ አይነቶች እና ጠቀሜታ ውይይት አድርጉ፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ያላችሁን አመለካከትና ፍላጎት በምክንያትና ውጤት በማስደገፍ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### "ለውሃ ስም አነሰው"



❖ ቅድመ ንባብ

1. ለውሃ ብክነትና መበከል ምክንያቶቹ ምን ምን ይመስላችኋል?
2. የውሃ ብክለት የሚያስከትለውን ጉዳት ዘርዝሩ፡፡
3. ከላይ ከቀረበው ምስል ምን ተረዳችሁ?

❖ የማንበብ ሂደት

ተግባር፦

‹ለውሃ ስም አነሰው› የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ፡፡ በየመሀሉ በመምህራችሁ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡፡

## "ለውሃ ስም አነሰው"

ከማልና መቅደስ የጥበብ ዕድገት ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በምሳ ሰዓት ምሳቸውን ከተመገቡ በኂላ መምህራቸው በሰጧቸው የቤት ስራ ዙሪያ በትምህርት ቤታቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኘው ትልቅ ዛፍ ስር አረፍ ብለው "ለውሃ ስም አነሰው" በተባለው ርዕስ ዙሪያ ስለሚፅፉት አንቀጽ እየተወያዩ ነው፡፡

- ከማል፦ "ዛሬ የአማርኛ መምህር የሰጡን የቤት ስራ ግራ ገብቶኛል" ፡፡
- መቅደስ፦ "እንዴት ከማል?"
- ከማል፦ ‹ለውሃ ስም አነሰው› በሚለው ርዕስ ዙሪያ ሶስት አንቀጽ ጻፉ ያሉት፡፡"
- መቅደስ፦ "ታዲያ ምን ችግር አለው? ውሃኮ ከእለት ተእለት ህይወታችን ጋር ጥብቅ ግንኙነት አለው፤ ስለዚህ ሊከብድህ አይገባም፡፡"
- ከማል፦ "መፃፍማ ቀላል ነው፤ ነገር ግን እንዴት አድርጌ ሶስት አንቀጽ ላሟላ?"
- መቅደስ፦ "ለመሆኑ ስንት አይነት ውሃ አይነቶች እንዳሉ ታውቃለህ?፡፡"
- ከማል፦ "እሱማ አውቃለሁ አምስተኛ ክፍል የተቀናጀ ሳይንስ ላይ ተምረናል፡፡ እነሱም፦ ለመጠጥ አገልግሎት

የሚውል ለምሳሌ የምንጭ እና የቧንቧ ውሃ፤ እንዲሁም ለመጠጥ አገልግሎት የማይውል በተለያዩ ንጥረ ነገሮች የተበከለ የውሃ አይነት አለ፡፡ ለምሳሌ የውቅያኖስ፣ የባህር እና የወንዝ ውሃ ይጠቀሳሉ፡፡"

- መቅደስ፡- "ልክ ነህ እኔም አስታወስኩኝ፤ በመጀመሪያ ግን ህይወት ያለው ነገር ለመኖር ውሃ እንደሚያስፈልገው በዝርዝር እንጽፋለን፤ የምድራችንም 70 በመቶው በውሃ የተሸፈነ ነው፡፡"

*ተማሪዎች የከማልና የመቅደስ ውይይት መነሻ ምክንያቱ ምንድን ነው? በቀጣዩ የውይይት ክፍልስ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

- ከማል፡- "ጥሩ ብለሻል መቅደስ፣ ጥሩ ውሃን ግን በምን እንለየዋለን?"
- መቅደስ፡- "ጥሩ ውሃ የሚባለው በተፈጥሮ ንጥረ ነገሮች የበለፀገ ነው፡፡ እነሱም፡- ማግኒዥየም፣ ካልሲየም፣ ፖታሺየም፣ ሶዲየም ወዘተ. የያዘ ነው፡፡"
- ከማል፡- "እንዴ መቅዲ በጣም ልክ ነሽ፤ ትዝ አለኝ ውሃኮ ሌሎችም ጥቅሞች አሉት፡፡ ለምሳሌ ለሃይል ማመንጫነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፤ የተለያዩ ወንዞች ተገድበው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ በመሆን የሚያገለግሉት ውሃ ሲኖር ብቻ ነው፡፡"
- መቅደስ፡- "ልክ ነህ ከማል ከዚህ በተጨማሪ በመስኖ የተለያዩ አዝርዕርት ለማብቀል ውሀ ከፍተኛ ጥቅም አለው፤ በዚህ ደግሞ ድህነትና ርሀብን መዋጋት እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ውሃማ አካላት ውስጥ የተለያዩ የአሳ ዝርያዎች ስለሚገኙ አሳ አስጋሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡"

- ከማል፡- “ከዚህ በተጨማሪ የሰው ልጆች አዕምሯቸውን ለማደስና የእረፍት ጊዜያቸውን ለማሳለፍ የውሃ ዳርና የውሃ ላይ መዝናኛዎችን ይመርጣሉ፡፡”
- መቅደስ፡- “ውሃ የዚህን ያክል ጥቅም ካለው ለምንድን ነው? በአግባቡ የማንጠቀመው?”
- ከማል፡- “እውነትሽን ነው፤ ይህ ለረጅም ጊዜ ሲከነክነኝ የነበረ ጉዳይ ነው፤ ግን እንዴት ነው? ከብክነት መከላከል የምንችለው?”
- መቅደስ፡- “ውሃን ስንጠቀም ብዙ ባለማፍሰስ፣ እንዲሁም ቧንቧዎችን ከፍቶ ባለመተው፣ ከዚህም በተጨማሪ ውሃን በድጋሚ በመጠቀም፣ ለምሳሌ ልብስ ባጠብንበት ውሃ ቤትና መጸዳጃ ቤቶችን በመወልወል ወዘተ. የመሳሰሉትን ተግባራት በመፈጸም ነው፡፡”
- ከማል፡- “እስካሁን ብዙ ነገር አንስተናል፤ ነገር ግን ስለ ውሃ ብክለት አላወራንም፡፡”
- መቅደስ ፡- “አዎ በጣም ልክ ነህ! ውሃን የሚበክሉ ንጥረ ነገሮች በውሃ ውስጥ መገኘት ውሃን ተበከለ ያሰኘዋል፡፡”
- ከማል፡- “በርካታ ሰዎች ለውሃ ብክለት ተጠያቂዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የሚጸዳዱትና ቆሻሻ የሚጥሉት በውሃማ አካላት ላይ ነው፡፡”
- መቅደስ፡- “አንተ ካልከው በተጨማሪ ከፋብሪካ የሚለቀቁ ፅዳጆች (ቆሻሻዎች)፣ በወንዞች ዳርቻ ልብስ ማጠብና መፀዳዳት፣ ከመፀዳጃ ቤት አላግባብ ወደ ወንዝ የሚለቀቁ ፍሳሾች ለውሃ ብክለት መንስኤዎች ናቸው፡፡”
- ከማል፡- “ታዲያ ከኛ ምን ይጠበቃል?”
- መቅደስ፡- “ከኛማ የሚጠበቀው ውሃ እንዳይባክን እና እንዳይበከል ባገኘነው አጋጣሚ ለክፍል ጓደኞቻችን እና ለቤተሰቦቻችን ማስተማር ነው፡፡”

- ከማል፡- “በጣም ትክክል ነሽ፤ ለካ ይህ ሁሉ ጥቅም አለው፡፡ ይህን ስላልተረዳን ነው በአግባቡ የማንይዘው፡፡

መምህራችን ትክክል ናቸው <<ለውሃ ስም አነሰው በሚል ርዕስ አንቀጽ ጻፉ ያሉን፤ በይ ሰዓቱ ስለደረሰ ወደ ክፍላችን እንሂድ፡፡>> ብለው ውይይታቸውን ጨርሰው ወደ ክፍላቸው ገቡ፡፡

❖ አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

<<ለውሃ ስም አነሰው>> በሚል ርዕስ ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. ውሃ ተበከለ የሚባለው ምን ሲሆን ነው?
2. የምድራችን ምን ያህል በመቶው በውሃ የተሸፈነ ነው?
3. በተፈጥሮ ማዕድን የበለፀገ ውሃ ምን ምን ንጥረ-ነገሮችን ይይዛል?
4. ለውሃ መበከል በምክንያትነት የተጠቀሱት ምን ምን ናቸው?
5. ሁላችንም ለውሃ ብክለት ተጠያቂዎች ነን ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. “ለውሃ ስም አነሰው” የሚለውን ሀሰብ አብራርታችሁ ፃፉ፡፡
7. የውሃ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

ተግባር ሁለት፡-

ከታች ለቀረቡት ካነበባችሁት ምንባብ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. የበለፀገ | 5. ሲከነክነኝ |
| 2. ማመንጨት | 6. ጽዳጀች |
| 3. አዝዕርት | 7. መበከል |
| 4. አሳ አስጋሪዎች | 8. መባከን |

ተግባር ሶስት፦

መምህራችሁ በሰጧችሁ ማስታወሻ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በማንበብ ምክንያትና ውጤታቸውን ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፦ ሀ. አበባው ውሃ ባለመጠጣቱ ጠውልጓል።

ምክንያት = ውሃ ባለመጠጣቱ

ውጤት = ጠውልጓል

ለ. የተደሰተው አዲስ ልብስ ስለተገዛለት ነው።

ምክንያት = አዲስ ልብስ ስለተገዛለት

ውጤት = የተደሰተው

1. በሙስና ስለተጠረጠረ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋለ።
   ምክንያት =
   ውጤት =
2. ሀይለኛ ራስ ምታት ስላመመኝ ከትምህርት ቤት ቀረሁ።
   ምክንያት =
   ውጤት =
3. ውሃን በአግባቡ አለመያዝ ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል።
   ምክንያት =
   ውጤት =
4. ትምህርቱን ያቋረጠው ቤተሰብ አልባ በመሆኑ ነው።
   ምክንያት =
   ውጤት =
5. ጥሩ ውጤት ያስመዘገበው ጠንክሮ በመስራቱ ነው።
   ምክንያት =
   ውጤት =
6. በርካታ ሰዎች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው የኮሮና ቫይረስ በጣም ተስፋፋ።
   ምክንያት =
   ውጤት =

7. ህይወቷ ሊያልፍ የቻለው ቶሎ ወደ ሆስፒታል ባለመሄዷ ነው።

ምክንያት =

ውጤት =

8. የትራፊክ አደጋ የተስፋፋው በአሽከርካሪዎች እና በእግረኞች ቸልተኝነት ነው።

ምክንያት =

ውጤት =

### ተግባር አራት፡-

በውሃ ወለድ ስለሚተላለፉ በሽታዎች ምንነትና ስለሚያስከትሉት ጉዳት ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከአካባቢያችሁ ወይም ከቤተ መፃህፍት መረጃ ሰብስባችሁ በመምጣት በክፍል ውስጥ ተወያዩ።

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

**ማስታወሻ**

**ተራኪ ፅሁፍ**

ይህ የፅሁፍ ዓይነት ተከታታይነት ያላቸውን ድርጊቶች እና ሁነቶች መሰረት አድርጎ ከመነሻው እስከ መድረሻው ድረስ የሚሆነውን ነገር እየተረከ ለአንባቢ በማድረስ ላይ ያተኩራል። በተራኪ ጽሁፍ ውስጥ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል ጠብቆ እንዲህ ሆነ፣ ከዚያም እንዲህ ተደረገ በሚል አቀራረብ የነገሮችን አከናወንና አፈፃፀም በትረካ ያቀርባል። በዚህም አንባቢው የሁነቶችን፣ የክስተቶችን እና የድርጊቶችን ትስስር በቅርበት መከታተል የሚችልበት መንገድ ያመቻቻል። ተራኪ ጽሁፍ ልቦለዳዊ ወይም ኢ-ልቦለዳዊ ሊሆን ይችላል። የበለጠ ግልጽ እንዲሆንላችሁ ከታች የቀረቡትን ምሳሌዎች ተመልከቱ።

ምሳሌ አንድ፡- ልቦለዳዊ ተራኪ ጽሁፍ

… የዚያኑ እለት ማታ የባቡር ትኬት አስቆረጥኩና ጓዜን ጠቅልዬ ጉዞ ወደ ሀረርጌ ጀመርኩ፤ ሲነጋጋ ድሬድዋ ከተማ ደረስኩ፡፡ አልጋ ተከራይቼ አጎቴ ቤት ጎራ አልኩና ብጠይቅ ለስራ ጉዳይ ወደ ሌላ ቦታ መሄዱን ባለቤቱ ነግራኝ ወደ ቤት እንድገባ ጠየቀችኝ፡፡ ያለሁበትን ማወቅ ተሳነኝ፤ መላው አለም በተቃውሞ የተነሳብኝ መሰለኝ፡፡ የአጎቴን ባለቤት ጥያቄ ምላሽ ሳልሰጥ እንዳበደ ሰው ከንፌ ወደ ተከራየሁት ቤርጎ ተጓዝኩ፡፡ ቤርጎ ቤቱ ጋር እንደደረስኩ ወደ ቡና ቤት ገባሁ፡፡ መላ ህዋሳቴ ዝሏል፡፡ አሳላፊው እስኪደንቀው ድረስ ሶስት ቡና አከታትዬ ጠጥቼ ወጣሁ፡፡…

ምሳሌ ሁለት፡- ኢ-ልበለዳዊ ተራኪ ጽሁፍ

ቀኑ እለተ አርብ መጋቢት አራት 2012 ዓ.ም ነው፤ ገና በማለዳ ነበር ወደ ትምህርት ቤት ያቀናሁት፡፡ ወዲያው ወደ ትምህርት ቤቱ የሚኒ ሚዲያ ቢሮ ገባሁ፡፡ አስታውሳለሁ "ሀገሬን አልረሳም" የሚለውን የንዋይ ደበበን ሙዚቃ ድምፁን ከፍ አድርጌ ከፈትኩት፡፡ ተማሪዎች ሰዓት እየደረሰ ስለነበር እየተንጠባጠቡም ቢሆን ወደ ሰልፍ ቦታው እየተጠጉ ነበር፡፡ ሙዚቃው እንዳለቀ የሀገራችንን ብሔራዊ መዝሙር ተማሪዎች ድምጻቸውን ከአድርገው ዘመሩ፡፡ በመቀጠልም የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር በተማሪዎች ስነ-ምግባር ዙሪያ ጠንከር ያለ መልዕክት አስተላለፉ፡፡እኔም ተማሪዎቹን ወደ ክፍላቸው እንዲገቡ ካዘዝኩ በኋላ የማስተምርበት ክፍለጊዜ እስኪደርስ ቁርስ ለመብላት በትምህርት ቤታችን የመምህራን ምግብ ቤት ጎራ አልኩኝ፡፡

ቁርሴን ተመግቤ ሻይ እየጠጣሁ እያለ ድንገት ዓይኔ በግድግዳው የተሰቀለው ቴሌቪዥን ላይ አረፈ፡፡ ጋዜጠኛው የሶስት ሰዓቱን ዜና እየተናገረ ነበር፡፡ ድንገት የአድማጭን ቀልብ የሳበው ሰበር ዜና በጋዜጠኛው አንደበት ሲስተጋባ ሁሉም ሰው በድንጋጤ

ተዋጠ፡፡ “የመጀመሪያው የኮሮና ተጠቂ ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኘ” ሲል ቤቱ ባንዴ በድንጋጤ ድባብ ተሞላ፡፡ የጀመርኩትን ሻይ እንኳን ሳልጨርስ በሀዘን ስሜት ከምግብ ቤት ስወጣ ተማሪዎች ከግቢ እየወጡ ነበር፡፡ መምህራንም በየፊናቸው በድንጋጤ ተውጠው ይሯሯጣሉ፡፡ በግቢው ውስጥ የነበረው ትዕይንት በሕይወት ዘመኔ ከማልረሳቸው ትዝታዎች ውስጥ አንዱ ነበር፡፡

ተግባር አንድ፡-

የማትረሱትን ገጠመኝ መሰረት በማድረግ ባለ ሁለት አንቀጽ ተራኪ ጽሁፍ ፃፉ፡፡

ተግባር ሁለት፡-

በተግባር አንድ የፃፋችሁትን ጽሁፍ በመቀያየር እርስ በርስ ተራረሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### እማሬያዊ ቃላት

ተግባር አንድ፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማስታወሻና ማብራሪያ መሰረት ከታች ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ሚጥሚጣ
2. ቀፎ
3. ንብ
4. ሚዛን
5. ፍየል
6. መሬት
7. ጨለማ
8. ቆቅ
9. ባህር
10. ወንበር

ተግባር ሁለት፡-

ከላይ ፍቺ በሰጣችሁባቸው እማሬያዊ ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

ምሳሌ፡- ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ግልብጥ ብሎ ወጣ፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

**ገቢር እና ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች**

ዓረፍተ ነገሮችን ገቢርና ተገብሮ ብለን በሁለት መክፈል ይቻላል።

ሀ. ገቢር ዓረፍተ ነገሮች፡- ትኩረት የሚያደርጉት ተግባሩን የፈጸመው ባለቤት (ድርጊት ፈፃሚው ) ላይ ነው።

ምሳሌ፡-

-ሙሉጌታ አበባ ተከለ።

-ሌባው ገንዘቤን ሰረቀኝ።

-ልጆቻችንን ወደ መናፈሻ እንወስዳለን።

ለ. ተገብሮ ዓረፍተ ነገር፡- ትኩረት የሚያደርጉት በተሳቢ (ድርጊት ተቀባይ) ላይ ነው።

ምሳሌ፡-

-አበባው በሙሉጌታ ተተከለ።

-ገንዘቤ በሌባው ተሰረቀ።

-ልጆቻችን ወደ መናፈሻ ይወሰዳሉ።

### ተግባር አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ገቢርና ተገብሮ በማለት ለይታችሁ ፃፉ።

1. አልማዝ ብርጭቆውን ሰበረችው።
2. መኪናው የተገዛው በአባቴ ነው።
3. መስታወቱ በልጆች ተሰበረ።

4. አቤል ኳሷን ለጋት።
5. ነቢያት ለስርዓተ ፆታ ክበብ ሰብሳቢነት ተመረጠች።
6. ሱልጣን ከኤች አይቪ ኤድስ ራሱን ይጠብቃል።
7. ውሻው የታሰረበትን ሰንሰለት በጠሰው።
8. ህፃናቱ በአሰሪዎቻቸው የጉልበት ብዝበዛ ደረሰባቸው።
9. ዙቤይዳ ባህሏን የሚያንፀባርቅ ልብስ ለበሰች።
10. እንስሳቱ ግጦሽ ቦታ ተሰማሩ።

ተግባር ሁለት፡-

አምስት ገቢር ዓረፍተ ነገር ከመሰረታችሁ በኋላ ወደ ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች ለውጡ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ ተራኪ ፅሁፍ፣ እማሬያዊ ቃላት፣ ገቢርና ተገብሮ ዓረፍተ ነገር እንዲሁም የምክንያትና ውጤት ተዛምዶ ተምረናል፡፡
- ተራኪ ጽሁፍ ተከታታይነት ያላቸውን ድርጊቶች እና ሁነቶች መሰረት አድርጎ ከመነሻው እስከ መድረሻው ድረስ የሚሆነውን ነገር እየተረከ ለአንባቢ በማድረስ ላይ የሚያተኩር የጽሁፍ አይነት ነው፡፡ ተራኪ ጽሁፍ ልቦለዳዊ ወይም ኢልቦለድ ሊሆን ይችላል፡፡
- እማሬያዊ ፍቺ ማለት የአንድ ቃል ጥሬ ትርጉም ወይም የመዝገበ ቃላት ፍቺው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ እማሬያዊ ፍቺ የቃሉ ቀጥተኛ ፍቺ ነው እየተባለ ይገለፃል፡፡
- ዓረፍተ ነገሮችን ገቢርና ተገብሮ ብለን በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡ ገቢር ዓረፍተ ነገሮች ትኩረት የሚያደርጉት ተግባሩን የፈጸመው ባለቤት (ድርጊት ፈፃሚው) ላይ ሲሆን ተገብሮ ዓረፍተ ነገር ትኩረት የሚያደርጉት በተሳቢ (ድርጊት ተቀባዩ) ላይ ነው፡፡
- ምክንያትና ውጤት፡- ምክንያት የምንለው አንድ ነገር ለመከሰቱ መንስኤ ወይም ሰበብ የሆነው ነገር ሲሆን፣ በክስተቱ ሳቢያ የሚገኘው ግብ ደግሞ ውጤት ይባላል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ተራኪ ጽሁፍ ምን አይነት የጽሁፍ አይነት ነው?

2. ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ገቢርና ተገብሮ በማለት ለዩ፡፡

ሀ. ፍቅርተ መፅሀፍ ገዛች፡፡

ለ. ደርቤ በሬውን ተሰረቀ፡፡

ሐ. ልጆቹ በወንድማቸው ተመሰገኑ፡፡

መ. ድመቶቹ ወተቱን ጠጡት፡፡

3. ለሚከተሉት ቃላት እማሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. እባብ

ለ. እስስት

ሐ. አሳማ

መ. ወንፊት

# ምዕራፍ ስድስት (፮)

## የሰዎች ዝውውር

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-

- ካዳመጣችሁት ነገር በመነሳት ዋናውን ሀሳብ ትገልፃላችሁ፡፡
- የሰዎችን ዝውውር ጽንሰ ሀሳብ ትገልፃላችሁ፡፡
- ከጓደኞቻችሁ ጋር በራስ በመተማመን ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- በትክክል ታነባላችሁ፡፡
- የሰዎች ዝውውር የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ታብራራላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### "የሰዎች ዝውውር"

❖ ቅድመ ማዳመጥ

1. ስለሰዎች ዝውውር ምን ታውቃላችሁ?
2. ለምን ሰዎች በህገወጥ መንገድ ከሀገር የሚወጡ ይመስላችኋል?
3. ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምን ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ግምታችሁን ተናገሩ፡፡

❖ የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር፡-

"የሰዎች ዝውውር" የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

**ተግባር አንድ፡-**

ከታች ለቀረቡት ከማዳመጥ ምንባብ ለወጡ ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሁፍ አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ህጋዊ የሰዎች ዝውውር ከህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በምን ይለያል?
2. ለህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት እነማን ናቸው?
3. መዳረሻ ሀገራት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?
4. በህገ-ወጥ ዝውውር ወቅት ሀሰተኛ መረጃና ተስፋ የሚሰጡት እነማን ናቸው?
5. የህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያቶችን ዘርዝሩ፡፡
6. ከህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እንዴት ራሳችንን መጠበቅ ይቻላል?
7. ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና መልዕክት በአጭሩ ግለፁ፡፡

**ተግባር ሁለት፡-**

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ወንጀል | ሀ. ሰለባ |
| 2. መመልመል | ለ. ምክንያት |
| 3. ምንጭ | ሐ. ድንገት |
| 4. ተጎጂ | መ. ማባበያ |
| 5. በር ከፋች | ሠ. አለማስተዋል |
| 6. መደለያ | ረ. የሚተላለፉባቸው |
| 7. የሚያቋርጧቸው | ሰ. ማጨት |
| 8. ግዳጅ | ሸ. ህገ-ወጥ ተግባር |
| 9. በጭፍን | ቀ. ያለፍቃድ |
| | በ. መነሻ |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

ተግባር ፡-

ስለሰዎች ዝውውር ጥቅምና ጉዳት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን የቡድናችሁን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### የሶስቱ እንስት የስደት ታሪክ”



❖ ቅድመ ንባብ

ከታች ለቀረቡት ቃላት በፍቻቸው ዙሪያ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

| | |
|---|---|
| ህገ ወጥ | እንግልት |
| ዳግም | ራዕይ |
| ቋጥሮ | ጫና |

❖ የማንበብ ሂደት

ተግባር፡-

“የሶስቱ እንስት የስደት ታሪክ” የሚለውን ምንባብ በየግል እያነበባችሁ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ምላሽ እየሰጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

## “የሶስቱ እንስት የስደት ታሪክ”

ሶስቱንም የተዋወቅኳቸው በአንድ የሙያ ስልጠና ላይ ነው፡፡ አንድ የሚያደርጋቸው ሶስቱም ከስደት ተመላሽ መሆናቸውና የሙያ ስልጠና መውሰዳቸው ነው፡፡ በመጀመሪያ ገጠመኟን አሐዱ ብላ ያወጋችን በምኖርበት አካባቢ የቤት እቃ መሸጫ ሱቅ ከፍታ ከምትሰራ ወይንሸት ረጋሳ የምትባል ወጣት ናት፡፡ ይህች ወጣት በሕጋዊ መንገድ ወደ ተባበሩት ዓረብ ኤምሬት ለስራ ፍለጋ በመሄድ ሰርታ የተመለሰች ነበረች፡፡ የመጀመሪያ ጉዞዋን አድርጋ ሁለት ዓመት ያህል እንደሰራች አሰሪዎቿ የተወሰነ ጊዜ ያህል እረፍት ሰጥተዋት ወደ ኢትዮጵያ መጣች፡፡ እንደመጣች ግን ቤተሰቦቿ ወደሚገኙባት ደሴ ከተማ አላመራችም ነበር፡፡ እረፍቷን ጨርሳ እስክትሄድ ድረስም ከአዲስ አበባ ውልፍት አላለችም፡፡

ከተማ ውስጥም ስትዘዋወር በአግባቡ ተሸፋፍና ነበር፡፡ ነገር ግን ከውጭ ሀገር የተላከ በማስመሰል እቃዎችን እዚሁ ገዝታ ለቤተሰቦቿ ልካ እንደነበረ ታስታውሳለች፡፡ ይህን ያደረገችበትን ምክንያት ስታብራራም ቤተሰቦቿ እና ዘመዶቿ ከሷ ብዙ ስለሚጠብቁ ሀገር ቤት ብትሔድ እያንዳንዱን ቤተሰብ በስጦታ እቃና በገንዘብ ማንበሽበሽ ባለመቻሏ ነበር፡፡ እናም እረፍቷን እስክትጨርስ ቤት ተከራይታ ወደ ተባበሩት አረብ ኢምሬት ተመለሰች፡፡

አሁንም ጠቅልላ ወደ ሀገሯ ብትመለስም ቤተሰቦቿ ጋር ያስገባኛል ብላ የምታስበውን ያህል ገንዘብ ስላልያዘች በያዘቻት ጥሪት የራሷን የእቃ መሸጫ ሱቅ ከፍታ እዛው እያደረች ኑሮዋን ተያይዛዋለች፡፡ እንደ እሷ አይነት መጠነኛ ጥሪት ቋጥረው በሀገር ላይ ለመሥራት ቢያልሙም የዘመዶቻቸውን ፍላጎት ባለማሟላታቸው ብቻ ለዳግም ስደት የሚዳረጉ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በርካታ ናቸው፡፡ ከነዚህም አብዛኞቹ ሕጋዊ የጉዞ እና የሥራ ፈቃድ ሰነዶች ሳይኖሯቸው በሕገ ወጥነት በሰው ሀገር የኖሩ እና በብዙ የስደተኝነት ቀውስ ውስጥ እያለፉ ያሉ ናቸው፡፡

ሁለተኛዋ ወጣት አዲስ አበባ ሳሪስ አቦ አካባቢ ተወልዳ ያደገችው ነጃት ሱሌይማን ሌላዋ ታሪኳን ያካፈለችን ስትሆን እሷም የስደት ህይወትን ቀምሳ በቃኝ ብላ ወደ ሀገሯ የተመለሰች ሰልጣኝ ናት፡፡ ወጣቷ በሱዳን አንድ ባለ ሀብት ቤት ተቀጥራ ትሰራ የነበረ ሲሆን በስደት ህይወት ብዙ የተለያዩ መከራዎችን ብታሳልፍም አብረን ወደ ጣልያን እንሻገራለን ካለችው የፍቅር ጓደኛዋ አንድ ሴት ልጅን አግኝታለች፡፡ ልክ መፀነሷን እንዳወቀች ትሰራበት የነበረውን ቤት ለቃ በኢትዮጵያ ኢምባሲ በኩል በትራንስፖርት ሀገሯ እንደገባች የምትናገረው ነጃት የልጇ አባት ተሳክቶለት ካሰበበት ጣሊያን መግባቱን ትናገራለች፡፡

ትዳር እዛና እዚህ እንዲሆን የፈረደባት ስደትን የምትረግመው ነጃት ጓደኞቿ ጠንክረው ሰርተው፣ የተወሰነ ጥሪት አግኝተው፣ ቤተሰብ አፍርተው ስትመለከት አራት የባከኑ ዓመታትን እንዳሳለፈች ትናገራለች፡፡ “አሁንም አልረፈደም” የምትለው ነጃት በምግብ ስራ ስልጠና ወስዳ የእለት ጉርሷን የምታገኝበት የስራ መስክ ላይ በመሰማራት ስደት ያበረከተላትን ፀጋ (ልጇን) ማሳደግ እንደምታስብ ተናግራ ሌሎችም ወደ ውጭ ለመውጣት ከመጓጓታቸው በፊት ቆም ብለው እዚህ ያሉ አማራጮችን ማጤን የሚገባቸው መሆኑን

ታስረዳለች፡፡ ህይወት በስደት ከባድ ነው፡፡ ሰው ተሰዶ ጥሪት ካልያዘ ለምን ይሰደዳል? በተቻለ መጠን ያቅሙን ያህል በሀገሩ ከሰራ ከሰው ሀገር የማይሻል ምንም የለም ትላለች፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከቀረበው ታሪክ ምን ተረዳችሁ? ሶስተኛዋ ባለታሪክስ ምን የሚገጥማት ይመስላችኋል?

“እንደ ዝምታ መካሪ እንደ ስደት ኑሮ አስተማሪ የለም” በማለት ስለስደት ህይወቷ ስጠይቃት ምላሽ መስጠት የጀመረችው ሶስተኛዋ ወጣት ብርቱካን ኪሮስ ናት፤ በአርሲ ነገሌ ተወልዳ እንዳደገች ትናገራለች፡፡ እስከ አስረኛ ክፍል ድረስ ከተማረች በኋላ ለመሰናዶ ትምህርት መግቢያ ውጤት እንዳላመጣች የተረዳችው ወጣት የተወሰነ ዓመት በአረብ ሀገር ሰርታ የራሷ የምትለውን ድርጅት ለመክፈት ባላት ህልም የተነሳ በህጋዊ መንገድ ወደ ኩዌት አቀናች፡፡ በቤት ሰራተኝነት የተቀጠረችው ይች ወጣት ቀንና ሌሊት ተሰርቶ የማያልቀው የአረብ ሀገር ስራ የወገብ በሽተኛ እንዳደረጋት ትናገራለች፡፡

በወር የምታገኘውን ገንዘብ በሙሉ ለቤተሰቦቿ በመላክ እጇ ላይ ምንም ገንዘብ ባለመኖሩ እስኪሞላ ቆይ ዛሬ ቆይ ነገ ስትል ለአምስት ዓመታት በከባድ የስራ ጫና ውስጥ ሰውነቷ ላይ ያለው ስጋ አልቆ በአጥንቷ የምትሄድ ሲመስል አሁን በቃኝ በማለት የያዘቻትን ይዛ ወደ ሀገሯ ተመለሰች፡፡ ለማገገም ከዓመት በላይ እንደ ፈጀባት የምትናገረው ብርቱካን ሰውነቷ ተመልሶ መንፈሷ ሲረጋጋ ትዳር ይዛ አንድ ልጅ ለማፍራት በቅታለች፡፡ አሁንም በምግብ ዝግጅት ሙያ ሰልጥና የራሷን ትንሽ ምግብ ቤት ለመክፈት ማቀዷን የተናገረች ሲሆን “ብልህ ከሰው ስህተት ይማራል” የሚባለውን ብሂል ከግንዛቤ በማስገባት ከኛ ህይወት በመማር ራሳችሁን አድኑ በማለት ጉዳቱ ላልደረሰባቸው፤ ግን ደግሞ ስደትን ላሰቡ ወገኖች ታሳስባለች፡፡

ለአብነት ያህል እነሱን አነሳን እንጂ የሀገራቸው መሬት እየናፈቃቸው በበረሃ ወድቀው የቀሩ፤ ከነሙሉ አካላቸው ተሰደው አካል ጉዳተኛ ሆነው የተመለሱ፤ በአቅም በጉልበታችን ሰርተን እንለወጣለን ብለው ከሀገራቸው ከወጡ በኋላ ያሰቡትና የሚሆነው አልገናኝ ብሏቸው አእምሯቸውን የሳቱትን ቤት ይቁጠራቸው:: ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ሄደው በደረሱበት ሀገር ያልተገባ እንግልት ላይ ከሚወድቁት በላይ የባህር ሲሳይ የሆኑትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: ወጣትነት ጉልበት ነው:: እድሜው በራሱ የሞከሩትን የሚያሳኩበት ባይሳካ እንኳን ተጨማሪ ተስፋዎች የሚታዩበት ነው::

በአፍላ የወጣትነት እድሜ፤ ሮጠው የማይጠግቡትን ያህል ጉልበት ሀገር ላይ አፍሶ ሀገርን ከማሳደግ ባለፈ ለምን አቅማችንን ላብ ወዛችንን ላልተመጣጠነ ክፍያ እናፈሳለን? ለምን አፍላውን እድሜያችንን አጠቃላይ ማንነታችንን ‹‹በህጋዊ ባርነት›› እናጣዋለን? የነገ ተስፋና ጸጋዎቻችንን በራሳችን እጅ ከማጨለማችን በፊት የነገ ራዕያችንን እንዴት በሀገራችን ማሳካት እንደምንችል ለማሰብ ከራሳችን ጋር እንማከር እላለሁ::

ምንጭ:- (አዲስ ዘመን ሐምሌ 25/2013፣ ለክፍሉ እንዲመጥን ተሻሽሎ የተወሰደ)

❖ አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ከሶስቱ ባለታሪኮች ውስጥ በስደት ህይወት ውስጥ ልጅ የወለደችው ነጃት ሱሌይማን ናት፡፡
2. <<እንደ ዝምታ መካሪ እንደ ስደት አስተማሪ የለም>>የምትለው ወይንሸት ረጋሳ ናት፡፡
3. ምንባቡ የስደትን ጠቀሜታ በደንብ ያብራራል፡፡
4. ሶስቱን ባለታሪኮች የሚያመሳስላቸው ከስደት ህይወታቸው ትምህርት መውሰዳቸውና ተስፋ አለመቁረጣቸው ነው፡፡
5. ነጃት በሱዳን ቆይታዋ የግል ሆቴል በመክፈት በርካታ ገንዘብ ሰብስባ ወደ ሀገሯ ተመልሳለች፡፡

ተግባር ሁለት፡-

ከታች ለተሰጡት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከምንባቡ ውስጥ ካሉት አንቀፆች ፈልጉ፡፡

1. አንድ ብላ (አንቀጽ 1 )
2. በረከት (አንቀጽ 5)
3. ህልም (አንቀጽ 9)
4. ሀብት (አንቀጽ 3)
5. ንቅንቅ (አንቀጽ 1)
6. ውጣ ውረድ (አንቀጽ 8)

ተግባር ሶስት፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማስታወሻ መሰረት "የሶስቱ እንስት የስደት ታሪክ" የሚለውን ምንባብ አቀላጥፋችሁ አንብቡ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታወሻ


**ገላጭ ጽሑፍ**

ገላጭ ጽሁፍ አንድ ነገር ምን ማለት እንደሆነ የሚያብራራና ብያኔ የሚሰጥ ወይም የአንድን ነገር የአሰራር ሂደት የሚገልፅ፤ እንዲሁም ሁነቶችንና ነገሮችን በተመለከተ ለሚነሱ ለምን፣ እንዴት፣ ምን ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ የድርሰት አይነት ነው፡፡ ገላጭ ድርሰት ሀተታውን የሚያቀርበው እንደ ተራኪ ድርሰት በጊዜ ቅደም ተከተል ተመስርቶ ሳይሆን በተጠየቅ አካሄድ ተመስርቶ ነው፡፡ ይህም ከቀላል ወደ ከባድ በመሄድ በምክንያትና ውጤት ተንተርሶ ነው፡፡

ምሳሌ፡- አልማዝ ጥልቀት ባለው የመሬት ከርሰ ምድርና እጅግ ከፍተኛ በሆነ የሙቀት ሀይል የተፈጠረ ብቻ ሳይሆን በጥንካሬው ተወዳዳሪ የሌለው ማዕድን ነው፡፡ አሁን የሰው ልጅ ከጥልቀት እየቆፈረ የሚያወጣው የአልማዝ ማዕድን ቢሆንም ከመሬት እምብርት በእሳተ ገሞራ አማካኝነት የወጣ ነው፡፡ አልማዝ እጅግ የከበረና ውድ ከመሆኑም በላይ በውስጡ ልዩና የእሳት ጨረር (ብርሃን) የሚያንፀባርቅ ግሩም ውበትና ግርማ የሚያጎናጽፍ ጌጥ ጭምር ነው፡፡ ስለሆነም ከውስጡ የሚያንፀባርቀው የእሳት ብርሃን ጥልቅ ፍቅርን፤ ጥንካሬው ደግሞ ዘላቂነት ያለው መዋደድን ያሳያል፡፡

### ተግባር አንድ፡-

ተማሪዎች ከላይ በቀረበው ማስታወሻ መሰረት ስለ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በተመለከተ ከታች የቀረበውን ቢጋር ተመርኩዛችሁ ሁለት አንቀፅ ገላጭ ጽሁፍ ጻፉ፡፡




### ተግባር ሁለት፡-

ጥንድ ጥንድ በመሆን የጻፋችሁትን ገላጭ ጽሁፍ ተቀያይራችሁ ስለ ሰዎች ዝውውር የሚያብራራ መሆኑንና ገላጭነቱን በተመለከተ ተገማገሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ፍካሬያዊ ቃላት

**ማስታወሻ**

**ፍካሬያዊ ፍቺ**

ባለፈው ምእራፍ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ እንዳላቸው በመገንዘብ ስለእማሬያዊ ፍቺ በዝርዝር አይተን ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ስለፍካሬያዊ ፍቺ እንመለከታለን፡፡

ፍካሬያዊ ፍቺ ማለት አንድ ቃል ከጥሬ ትርጉሙ ባሻገር ሊኖረው የሚችለው ሌላ ተደራቢ ፍቺ ነው፡፡ ፍካሬያዊ ፍቺ ብዙውን ጊዜ የሚመሰረተው በንጽጽር ላይ ነው፡፡ ንጽጽሩም ከአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ ልማድ፣ እምነት ጋር የሚቆራኝ ነው፡፡

| ምሳሌ፡- | ቃል | ፍካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|---|
| | ቀዳዳ | ነገር የማይቋጥር |
| | አልጋ | ዙፋን |
| | ድንጋይ | የማይሰማ |
| | ጎመን | አቅመ ቢስ |

ተግባር አንድ፡-

ከላይ በማስታወሻው በቀረበው ምሳሌ መሰረት ከታች ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ሙጫ
2. አልጫ

6. ንፋስ
7. አሳማ

3. መሰላል
4. መዥገር
5. አጎዛ
8. እሾህ
9. ጅማት
10. ቀጤማ

ተግባር ሁለት:-

ቀጥለው በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ።

1. ጠዋት የወጣሁ እንጀራ ፍለጋ ስንከራተት ዋልኩ።
2. ሁሌም የሚገርመኝ የኤርሚያስ አንበሳነት ነው።
3. ጩሉሌው ደላላ አባቴን አታሎ ቤታችንን በርካሽ ዋጋ አሸጠው።
4. የእሷን ክብሪትነት ብዙ ሰዎች ተረድተዋል።
5. ታናሽ ወንድሜ በትምህርቱ እሳት ሆነ።
6. እስስት የሆኑ ሰዎችን ባህሪ መረዳት አስቸጋሪ ነው።
7. ህፃኑ ዱባ ስለሆነ ለማንሳት ከበደኝ።
8. በጎጂ ሱሶች ምክንያት ቤቷን አፈረሰች።

ተግባር ሶስት:-

ከላይ ከተሰጡት ቃላት ውጪ አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸው አምስት ቃላት በመጻፍ በቡድን ሆናችሁ ፍቻቸውን ጻፉ።

## ክፍል ስድስት:- ሰዋስው

> **ማስታወሻ**
>
> **የዓረፍተ ነገር ስልቶች**
>
> ዓረፍተ ነገር የተሟላ መልዕክትን የሚያስተላልፍ በስርዓት የተቀናጁ የቃላት ስብስብ ነው። ማንኛውም ዓረፍተ ነገር በአወቃቀር ስርዓቱ አንድ ይሁን እንጂ በአገልግሎቱ ይለያያል። ሁሉም ዓረፍተ ነገሮች

አንድ ዓይነት ተግባር የላቸውም፡፡ በዚህም መሰረት ዓረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎታቸው አንጻር በአራት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

1. ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር ፡- ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር ስለአንድ ጉዳይ የሚያትትና የሚገልፅ የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር በአሉታ ወይም በአወንታ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡

ሀ. አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር አንድ ድርጊት በተወሰነ ጊዜና ቦታ፣ በተወሰነ ምክንያት የተፈፀመ ወይም የተከሰተ መሆኑን ይገልፃል፡፡

ምሳሌ፡- ነገ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ፡፡
አየለ ጠንቃቃ ሹፌር ነው፡፡

ለ. አሉታዊ ዓረፍተ ነገር የአፍራሽነት ባህሪ የሚታይበት የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር በተግባሩ አንድ ድርጊት አለመፈፀሙን ወይም አለመከሰቱን ጠቋሚ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ነገ ትምህርት ቤት አልሄድም፡፡
አየለ ጠንቃቃ ሹፌር አይደለም፡፡

2. መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር፡- አንድን መልዕክት በጥያቄ መልክ ለማስተላለፍ ወይም ለማቅረብ የሚያገለግል የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡ መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገሮችን ለመመስረት የሚረዱት ተዋቃሪዎች እንደ ምን፣ ማን፣ እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ወዴት፣ ለምን፣ ስንት ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ዓረፍተ ነገሮች መጠይቃዊ መሆናቸውን የምናውቀው በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ በሚመጣው የጥያቄ ምልክትና በድምጸቱ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ኤች አይቪ ኤድስን እንዴት መከላከል እንችላለን?
ለምን የቤት ስራህን አልሰራህም፡፡

3. ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር፡- ሀሳባችንን በትዕዛዝ መልክ ለመግለጽ የሚያገለግል የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኘው ግስ በትዕዛዝ አንቀፅ የተቀመጠ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፀጉርሽን አበጥሪ፡፡
መጽሐፉን አምጣ፡፡

4. አጋኗዊ ዓረፍተ ነገር፡- አንድን መልዕክት በመደነቅ፣ በመገረም እና በትዝብት ወዘተ. በመሳሰሉት ሀይለኛ ስሜቶች ለማስተላለፍ የሚያገለግል የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡
ምሳሌ፡- አ! እንዴት ያለች ቆንጆ ልጅ ናት፡፡
ይገርማል! ቡድናችን በሰፊ ውጤት አሸነፈ፡፡

ተግባር አንድ፡-

ተማሪዎች ከላይ በተሰጠው ማስታዎሻ ውስጥ የተሰጡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን የዓረፍተ ነገር ስልቶች ለዩ፡፡

1. ወደ ትምህርት ቤት ስትመጡ መታወቂያችሁን ያዙ፡፡
2. ጠንክሮ መማር ለምን ይጠቅማል?
3. አካል ጉዳተኛዋ እህቴ አንደኛ በመውጣቷ ተሸለመች፡፡
4. ፋጡማ ጧት ቁርሷን አልበላችም፡፡
5. አትሌት ጥሩነሽ ድንቅ ብቃቷን አስመሰከረች፡፡
6. ዋ! አበባውን እንዳትቆርጡ፡፡
7. ሙዘይን ለምን ትምህርት ቤት አልመጣም?
8. ወደ ቤታችሁ ስትሄዱ በሩን ዝጉት፡፡
9. ሀገርን መውደድ ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡
10. ጠንክሮ ባለማጥናቱ ዝቅተኛ ውጤት አመጣ፡፡

ተግባር ሁለት፡-

በተማራችሁበት የዓረፍተ ነገር ስልቶች መሰረት ሁለት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

**የምዕራፉ ማጠቃለያ**

- በዚህ ምዕራፍ ስለ አቀላጥፎ ማንበብ፣ ገላጭ ጽሁፍ፣ የቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሁም ስለ ዓረፍተ ነገር ስልቶች ተምረናል፡፡
- አቀላጥፎ ማንበብ ማለት ፊደላትን፣ ቃላትንና ሀረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልክት ሰጪ በሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ ነው፡፡
- ገላጭ ጽሁፍ አንድ ነገር ምን ማለት እንደሆነ የሚያብራራና ብያኔ የሚሰጥ ወይም የአንድን ነገር የአሰራር ሂደት የሚገልፅ፣ እንዲሁም ሁነቶችንና ነገሮችን በተመለከተ ለሚነሱ ለምን፣ እንዴት፣ ምን ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ የድርሰት አይነት ነው፡፡
- ፍካሬያዊፍቺ ማለት አንድ ቃል ከጥሬ ትርጉሙ ባሻገር ሊኖረው የሚችለው ሌላ ተደራቢ ትርጉም ነው፡፡ ፍካሬያዊ ፍቺ ብዙውን ጊዜ የሚመሰረተው በንጽጽር ላይ ነው፡፡ ንጽጽሩም ከአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ ልማድ፣ እምነት ጋር የሚቆራኝ ነው፡፡
    - የዓረፍተ ነገር ስልቶች ከአገልግሎታቸው አንፃር ሀተታዊ፣ መጠይቃዊ፣ ትዕዛዛዊና አጋኗዊ በመባል ይታወቃሉ፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ በመስጠት ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

ሀ. ድንክ  
መ. ወንፊት  
ለ. ዶማ  
ሠ. መጋዝ  
ሐ. ምሰሶ  
ረ. መንጠቆ

2. የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገር ቀይሩ፡፡

ሀ. አያንቱና አስቴር ነገ ይመጣሉ፡፡

ለ. ዘነበ ዛሬ ወደ ሀረር ይሄዳል፡፡

ሐ. ለዓመት በዓል በግ ገዛሁ፡፡

መ. ሶስና በማለዳ ተነስታ ቁርሷን በላች፡፡

3. ስለገላጭ ጽሁፍ ምንነትና ባህሪያት አብራሩ፡፡

4. ቀጥለው በቀረቡት ቃላት በትዕዛዛቸው መሰረት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ሀ. ሰበረ (መጠይቃዊ)

ለ. ጠመጠመ (አሉታዊ)

ሐ. አልገደለም (አዎንታዊ)

መ. ዘጋ (ትዕዛዛዊ)

ሠ. አሸነፈ (አጋኗዊ)

# ምዕራፍ ሰባት (፯)

## ማህበራዊ ግንኙነት

### ከምዕራፉየሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-

- በጥልቀት ታዳምጣላችሁ፡፡
- የማህበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት ትገልፃላችሁ፡፡
- በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ጽሁፍ ትፅፋላችሁ፡፡
- ውስብስብ ዐረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### “ጎፋ መስቃላ ዮ”





### ❖ ቅድመ ማዳመጥ

1. ማህበራዊ ግንኙነት ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ ሰዎች በህብረት በመሆን ምን ምን ስራዎችን ያከናውናሉ?
3. የጎፋ ማህበረሰብ በየትኛው የሀገራችን ክፍል ይገኛል?

### የማዳመጥ ሂደት

ተግባር፡-

"ጎፋ መስቃላ ዮ" የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ፈሊጣዊ ንግግሮች ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

ከታች ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በቃላችሁ አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. የጎፋ ማህበረሰብ የት አካባቢ ይገኛል? ከአዲስ አበባስ በስንት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል?
2. በጎፋዎች ቋንቋ መሰረት የመስከረም ወር ምን ተብሎ ይጠራል?
3. የሚለቀሙት የችቦ ጭራሮዎች ቀጥ ያሉ መሆናቸው የምን ተምሳሌት ነው?
4. የበዓሉ ዝግጅት የሚጀምረው ከመቼ ጀምሮ ነው?
5. የጎፋዎችን ማህበራዊ ግንኙነት ከበዓሉ አከባበር አንጻር በአጭሩ ግለፁ፡፡

ተግባር ሁለት፡-

"ጎፋ መስቃላ ዮ" በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ፡፡

1. በጎፋ ማህበረሰብ የበዓል አከባበር መሰረት <<ጎፋ መስቀላ ዮ >> -------- የሚወርድበት የበዓል ስነ-ስርዓት ነው፡፡
2. ---------------- በአካባቢው ባላባት፣ የዚያ ቀበሌ አስተዳዳሪ እና ባህላዊ መሪ እንዲሆን የተሾመ ሰው ነው፡፡
3. ንግስናውን የሚሰጡት ----------------- የሚባሉ አንጋሾች ሲሆኑ ንጉሱ ሲሞት በጊዜያዊነት በተዘጋጀ ---------------- ውስጥ የንግስና ስርዓቱን ይፈፅማሉ፡፡

4. የጎፋዎች ባህላዊ መጠጥ ----------- ይባላል፡፡
5. ችቦ የሚሰራባቸው ጭራሮዎች -------------ተብለው ይጠራሉ፡፡
6. የእድሜ ልክ ንግስና የሚሰጣቸው አናታቸው ላይ -------------- የሚባል ዘውድ ይደፋሉ፡፡

### ተግባር ሶስት፡-

ከታች በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

... ስነ-ጽሁፍ የሰው ልጅ ገጠመኝ ማንፀባረቂያ እንዲሁም ልዩ ልዩ የሕይወት መልኮች መገለጫ ነው፡፡ የሰው ገጠመኝና የህይወት መልክ ደግሞ ስፍር ቁጥር የለውም፡፡ ህይወት ባለ ብዙ ፈርጅና ባለብዙ ቀለም መሆኗ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የስነ-ጽሁፍ ክልል እዚህ ድረስ ነው ተብሎ ሊገደብ አይችልም ማለት ነው፡፡ ስነ-ፅሁፍ ማንኛውንም የሰው ልጅ ገጠመኝ፣ የተከሰተንና ሊከሰት የሚችልን ነገር እንዲሁም በሰው የምናብ አድማስ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብን ነገር ሁሉ ሊያካትት ይችላል፡፡ እይታውም እጅግ ሰፊ ብቻም ሳይሆን ገደብ አልባም ነው፡፡ የሰው ልጅ አያሌ ተግባራትም በስነ-ጽሁፍ ይንጸባረቃል፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር፡-

ከጓደኞቻችሁ ጋር በቡድን በመሆን ስለማህበራዊ ግንኙነት ምንነትና ጠቀሜታ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ውይይት አድርጋችሁ የደረሳችሁበትን የጋራ ሀሳብ በንግግር አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### “የሀገራችን ምርጥ ማህበራዊ እሴቶች”





❖ ቅድመ ንባብ

1. በፅሁፍ ውስጥ ፈሊጣዊ ንግግሮችን መጠቀም ምን ጥቅም ያለው ይመስላችኋል?
2. ማህበራዊ ግንኙነት ለምን የሚያስፈልግ ይመስላችኋል?
3. በአካባቢያችሁ ሰዎች በህብረት በመሆን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ዘርዝሩ፡፡

❖ የማንበብ ሂደት

ተግባር፡-

“የሀገራችን ምርጥ ማህበራዊ እሴቶች” የሚለውን ምንባብ ድምጽ በማሰማት ተራ በተራ አንብቡ፡፡ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍቺ እየሠጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

## “የሀገራችን ምርጥ ማህበራዊ እሴቶች”

“ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው” እንደሚባለው በሀገራችን ሰዎች ለአንድ ሰው አድካሚና እጅ እጅ የሚለውን ስራ በህብረት የመስራት ልማድ አላቸው፡፡ በደስታና በሀዘን ጊዜ በማህበረሰባችን ውስጥ መረዳዳትና መደጋገፍ የተለመደ ነው፡፡ በሀገራችን የተለያዩ ቦታዎች በርካታ ተባብሮ የመስራት እሴቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ የማህበረሰቡ ልማዶች መካከል ደቦና በሃ በግንባር ቀደምነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

**ደቦ ፡-**

ደቦ ጂጊ፣ ወንፈል እና ሌሎችንም ስያሜዎች የያዘ ማህበረሰቡ በህብረት ስራዎችን ለማከናወን የሚገለገልበት በተለይም በገጠራማው የሀገራችን ክፍል በጋራ በመተባበር ስራ የሚሰራበት ባህላዊ ስርዓት ነው፡፡ በእርሻ፣ በዘር፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ ወቅት የሀገሬ ሰው ጉልበቱንና መሳሪያውን በማዋጣት ደቦ የጠራውን ሰው ይረዳል፡፡ በአንድ ሰው ጉልበት ቢገፉት ቢገፉት ፈቀቅ የማይለው ስራ በተባበረ ክንድ በአጭር ጊዜ ይጠናቀቃል፡፡ ከእርሻ ስራ ወጪ ለቤት ግንባታ ለቀብርና ለሰርግ ደቦ ሊጠራ ይችላል፡፡

ደቦ ጠሪው ደቦ ለሚወጣው ሰው ምግብና መጠጥ ለማዘጋጀት ሽር ጉድ ይላል፡፡ ይህን ኃላፊነት ብዙውን ጊዜ የሚወስዱት የደቦ ጠሪው ሚስትና የጠሪው የቅርብ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የሚዘጋጀው ምግብና መጠጥ እንደየአካባቢው የሚለያይ ሲሆን ድግሱም ወቅቱን ያገናዘበ ይሆናል፡፡

በደቦ ስራ ወቅት የአካባቢው ሰው በነቂስ ይወጣሉ፤ ድምፀ መረዋ የሆኑ ሰዎች እየዘፈኑ የሰራተኛውን የስራ ተነሳሽነት ይቀሰቅሳሉ፤ አባቶች ይመርቃሉ፤ ጨዋታ አዋቂዎች በጨዋታ ሰውን ያዝናናሉ፡፡

ከብቶቹ፣ አዝመራው፣ መንደሩ እና ሳር ቅጠሉ ሳይቀር በዜማ ይወደሳል፤ ይመሰገናል፡፡ አልፎ አልፎ ቀራርቶና ፉከራ የተለመደ ነው፡፡ በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች ለተለያዩ ጉዳዮች ደቦ መጠራራት የተለመደ ነው፡፡ በደቦ ውስጥ ከሚዘፈኑ ዘፈኖች መካከል አንዱ ይሄን ይመስላል፡፡

እሽሩሩ በርዬ እሽሩሩ፣
አንተ በሰራኸው ይኖራል ሀገሩ፡፡
በሬና ገበሬ ቢጣሉም አይበጁ፣
እንዲያው ሰተት ብሎ ይጠመዳል እንጂ፡፡
በሬ የሌለው ሰው ማዕረግም አይደርሰው፣
ከሸንጎ ቢወጣ ሰው አይዋሰው፡፡
በሬ አንተን የጠላ ጎኔ እንተን የጠላ፣
የገና የጥምቀት ይለምናል ጠላ፡፡
በርዬ በርታልኝ ትንፋሽህ ምንድን ነው?፣
ምርቱ የኔ ቢሆን ገለባው ላንተ ነው፡፡
በርዬ ምርቁ በርዬ ምርቁ፣
አንተ ካልዞርክበት አይሰበር ምርቁ፣
በዱላ ቢመቱ በመንሽ ቢደልቁ፡፡
የበሬን ውለታ መጫወት ነው ማታ፣
በሰፊ ገበታ በዋንጫ ጋጋታ፡፡

*ተማሪዎች እጅ እጅ፣ ፈቀቅ የማይል፣ በተባበረ ክንድ ለሚሉት ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡ በሃ ምን አይነት ማህበራዊ ግንኙነት ይመስላችኋል?

በሃ፡-

በሃ የሀረር ሴቶች እርስ በርሳቸው ለመረዳዳት የሚያቋቁሙት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የመረዳጃ ማህበር ነው፡፡ ከበሃ በተጨማሪም አፎጫ የሚባል የሃረር ሴቶች የሚገለገሉበት ባህላዊ የመረዳጃ ማህበር አለ፡፡ አፎጫን ከበሃ የሚለየው ነገር ቢኖር የሀረር ሴቶች በበሃ ማህበር የሚሳተፉት በፈቃደኝነት ሲሆን የአፎጫ አባልነት ግን ባህላዊና ማህበራዊ ግዴታ ያለበት መሆኑ ነው፡፡ ሌላው የሁለቱ ባህላዊ ማህበራት ልዩነት ፆታን የተመለከተ ነው፡፡ በአፎጫ ማህበር ሴቶችም ወንዶችም የሚሳተፉ ሲሆን በሃ ግን ሴቶችን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡

በሃ የእቁብ አይነት ማህበር ሲሆን አባላቱ በየጊዜው ገንዘብ ይቆጥባሉ፡፡ የቆጠቡትን ገንዘብ በተለያዩ ሁነቶች (ደስታ ወይም ሃዘን) ሲያጋጥም ይጠቀሙበታል፡፡ ብዙውን ጊዜ የበሃ አባል የሚሆኑት ወጣት ሴቶች ናቸው፡፡ የዚህም ዋነኛው ምክንያት በሃ ከአፎጫ ይልቅ በአንፃሩ ለወጣቶቹ ሴቶች ለነፃነታቸው የሚያመች ማህበር መሆኑ ነው፡፡ የበሃ አባላት በየሳምንቱ ይገናኛሉ፡፡ በስብሰባቸውም ላይ ሻይ ተፈልቶ ግብዣ እየተካሄደ ፀሎት ያደርሳሉ፡፡ በዚሁ ስብሰባ ላይ መዋጮ በነፍስ ወከፍ የሚሰበሰብ ሲሆን እያንዳንዷ የበሃ አባል የአቅሟን ታዋጣለች፡፡ እርዳታ በሚያስፈልግበት ጊዜም የሚሰጣት የገንዘብ መጠን ያዋጣችው ተሰልቶ ነው፡፡

ብዙውን ጊዜ የአንድ በሃ አባላት ብዛት በቁጥር ከሃያ እስከ ሰላሳ አይዘሉም፡፡ ይህም የሚሆነው አባላቱ እንዳይበዙና ለአስተዳደር እንዲያመች እንዲሁም በአባላቱ መካከል የጠበቀ ቤተሰባዊ ትስስርን ለመፍጠር በማሰብ ነው፡፡ የበሃ ማህበር በተለይም በሰርግና በቀብር

ላይ ትልቁን ኃላፊነት በመወጣት በሃረር ሴቶች ማህበራዊ ህይወት ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

ምንጭ፡- (ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወለደ መስቀል ስብስብ ስራዎች ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

❖ አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ደቦ ምንድን ነው? ለማህበራዊ ግንኙነትስ ምን ጠቀሜታ ይሰጣል?
2. በደቦ ስራ ወቅት ምግብ የሚያዘጋጁት እነማን ናቸው?
3. ስራው በሚከናወንበት ሰዓት የሚዘፈኑ ዘፈኖች፣ ቀረርቶዎችና ሙገሳዎች አገልግሎታቸው ምንድን ነው?
4. “ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው” ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. የበሃ አባላት እስከ ስንት ይደርሳሉ?
6. ወጣት ሴቶች ከአፎጫ ይልቅ በሃን የሚመርጡበት ምክንያት ምንድ ነው?
7. በሃ ከአፎጫ ጋር የሚያመሳስለው ምንድን ነው? የሚያለያየውስ?

ተግባር ሁለት፡-

ከምንባቡ ለወጡ ፈሊጣዊ ንግግሮች ጥንድ ጥንድ በመሆን ፍቺ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ግንባር ቀደም - ቀዳሚ (ተጠቃሽ)

1. በነፍስ ወከፍ
2. ድምፀ መረዋ
3. ሳር ቅጠሉ
4. በነቂስ

**ተግባር ሶስት፡-**

ከላይ ፍቺ በሰጣችሁባቸው ፈሊጣዊ ንግግሮች ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

**ተግባር አንድ፡-**

ከታች የማህበራዊ ግንኙነትን በተመለከተ የቀረበውን ምሳሌ ጽሁፍ በማንበብ ከተሰጡት ርዕሶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ባለ ሁለት አንቀፅ ጽሁፍ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- የኢድ አልፈጥር በዓል የሚከበረው ሙስሊሙ ማህበረሰብ የረመዳንን ወር ፆሞ ሲጨርስ ነው፡፡ በዓሉ ሲከበር ምዕመናኑ በአንድ ቦታ ተሰብስበው በስግደት ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ፡፡ በዓሉ ከመከበሩ በፊት ሁሉም የእለት ጉርሱን መሸፈን የሚችል የሀይማኖቱ ተከታይ የሆነ ምዕመን በአካባቢው ለሚገኙ አቅመ ደካሞች<< ዘካተል ፈጥር>> ይሰጣል፡፡ የቤተሰቡ አስተዳዳሪ አባወራ በሀገሪቱ ከሚበቅሉና ከሚመገባቸው የእህል ዘሮች የተሻለውን በመምረጥ በቤተሰቡ ቁጥር ልክ ሁለት ኪሎ ተኩል ያዋጣል፡፡ይህም የሚሆነው አቅመ ደካሞች በዓሉን ካላቸው ጋር እኩል ተደስተው እንዲውሉ በማሰብ ነው፡፡ ይህም አንዱ የመተባበርና ጠንካራ የማህበራዊ እሴት ማሳያ ነው፡፡

ሀ. እድር    ለ. እቁብ    ሐ. የበዓል አከባበር

**ተግባር ሁለት፡-**

የፃፋችሁትን አንቀፅ ለጓደኞቻችሁ በማንበብ እርስ በርስ እርማት ተሰጣጡ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተመሳሳይ ቃላት

**ተግባር አንድ፡-**

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መዋጮ | ሀ. መደጋገፊያ |
| 2. መረዳጃ | ለ. መዋቢያ |
| 3. ገበታ | ሐ. የሚሰበሰብ |
| 4. ሚና | መ. አደባባይ |
| 5. ሽንጎ | ሠ. አስተዋፅኦ |
| 6. ጌጥ | ረ. ባህል |
| 7. ልማድ | ሰ. መጠጥ |
| 8. ሽክም | ሸ. ታስቦ |
| 9. ተሰልቶ | ቀ. ጫና |
| | በ. ምግብ |

**ተግባር ሁለት፡-**

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተቃራኒ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. በህብረት | ሀ. ዘመናዊ |
| 2. ግዴታ | ለ. ምርት |
| 3. ገለባ | ሐ. በተናጥል |
| 4. ነፃነት | መ. ማጠራቀም |
| 5. ባህላዊ | ሠ. እርግማን |
| 6. መቆጠብ | ረ. ባርነት |
| 7. ምርቃት | ሰ. ማባከን |
| | ሸ. መብት |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡-

ከታች በቀረበው ምሳሌ መሰረት የተሰጡትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን ወደ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ለውጡ።

ምሳሌ፡- ሀ. አባቴ መጣ። (ነጠላ ዓረፍተ ነገር)

ለ. እኔ ደስ አለኝ። (ነጠላ ዓረፍተ ነገር)

አባቴ ስለመጣ ደስ አለኝ። (ውስብስብ ዓረፍተ ነገር)

1. ሀ. በትምህርቴ አንደኛ ወጣሁ።
   ለ. ሽልማት ተሰጠኝ።
2. ሀ. ምስጋናው ጠዋት አርፍዶ ተነሳ።
   ለ. ምስጋናው ጠዋት ትምህርት ቤት ረፈደበት።
3. ሀ. ህፃናት በእንክብካቤ ያድጋሉ።
   ለ. ህፃናት ጤናማ ይሆናሉ።
4. ሀ. ዘምዘም የማጠቃለያ ፈተና ደረሰባት
   ለ. ዘምዘም ጠንክራ ታጠናለች።
5. ሀ. አንሻ የተማረች አርሶ አደር ናት።
   ለ. አንሻ በግብርና ስራዋ ውጤታማ ሆናለች ።
6. ሀ. ሰዎች ያለጥንቃቄ በመንገድ ላይ ይጓዛሉ።
   ለ. ሰዎች የትራፊክ አደጋ ይደርስባቸዋል።

## ተግባር ሁለት፡-

ከታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አዎንታዊ፣ አሉታዊ፣ ትእዛዛዊ፣ መጠይቃዊና አጋኗዊ መሆናቸውን ‹‹የራይት ምልክት›› በመጠቀም ለዩ፡፡

| ተ.ቁ | ዓረፍተ ነገር | የዓረፍተ ነገር ስልቶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎንታዊ | አሉታዊ | ትዕዛዛዊ | መጠይቃዊ | አጋኗዊ |
| 1 | ለምለም አስተዋይ ልጅ ናት፡፡ | | | | | |
| 2 | ወደ ወንዶ ገነት የምንሄደው መቼ ነው? | | | | | |
| 3 | ከበደ ዘፈን አይወድም፡፡ | | | | | |
| 4 | በጣም ይገርማል! ኳሷን ሰማይ አደረሳት! | | | | | |
| 5 | ሳትውል ሳታድር ወደ ክፍለ ሀገር መጓዝ አለብህ፡፡ | | | | | |
| 6 | አካል ጉዳተኞች እኩል የስራ እድል የማግኘት መብት አላቸው፡፡ | | | | | |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለፈሊጣዊ አነጋገር፣ውስብስብ ዓረፍተ ነገር፣ የቃላት ተመሳሳይና አውዳዊ ፍቺ ተምረናል፡፡
- ፈሊጦች የተናጋሪውን ቋንቋ ውበትና ለዛ በማላበስ የአድማጭን ስሜት የሚኮረኩሩ የአነጋገር ስልቶች ናቸው፡፡
- ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ሁለትና ከዚያ በላይ ግሶች ያሉት የዓርፍተ ነገር አይነት ነው፡፡
- የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የምንለው የቃላት መዝገበ ቃላዊና ቀጥተኛ ፍቺን ሲሆን አውዳዊ ፍቺ የምንለው ደግሞ አንድ ቃል በአንድ ዓረፍተ ነገር ወይም ምንባብ ውስጥ ሲገባ የሚኖረውን ፍቺ ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ከታች ለቀረቡት ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ባዶ ቤት　　　　ሐ. ሆደ ባሻ

ለ. ዓይን አውጣ　　　　መ. እግረ ደረቅ

2. ሶስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

3. ማህበራዊ ግንኙነት ከሚለው ርዕስ ምን ቁም ነገር ጨበጣችሁ?

# ምዕራፍ ስምንት (፰)

## ሱስ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-

- አዳምጣችሁ ተመሳሳይ ፅሁፍ ትጽፋላችሁ፡፡
- ሱስ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ትገልጻላችሁ፡፡
- የፅሁፉን ዋና ሀሳብ በተመለከተ ዘገባ ታቀርባላችሁ ፡፡
- ያዳመጣችሁትን ሀሳብ እንደገና ታዋቅራላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### “ትምባሆ”



❖ ቅድመ ማዳመጥ

1. ሱስ ምንድን ነው?
2. በጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የሱስ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
3. ሰዎች ትምባሆ ለምን የሚያጨሱ ይመስላችኋል?

❖ የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር፡-

“ትምባሆ” የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

ቀጥለው ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ትምባሆ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የአድሬናልን ዝውውር ይጨምራል፡፡
   ለ. የልብ ምትን ይቀንሳል፡፡
   ሐ. ሆርሞኖችን በብዛት ያመነጫል፡፡
   መ. የምግብ ፍላጎትን ይቀንሳል፡፡
2. በትምባሆ ውስጥ ከሚገኙ ጎጂ ንጥረ ነገሮች ውስጥ የሚመደበው የቱ ነው?
   ሀ. ታር ሐ. ኒኮቲን
   ለ. ካርቦን ሞኖ ኦክሳይድ መ. ሁሉም
3. ኢትዮጵያ የዓለም የጤና ድርጅት ትምባሆን ለመቆጣጠር ያወጣውን አዋጅ ያፀደቀችው መቼ ነው?
   ሀ. የካቲት ሃያ አምስት ሁለት ሺ አራት
   ለ. የካቲት አምስት ሁለት ሺ አራት
   ሐ. የካቲት አስራ ሁለት ሁለት ሺ አምስት
   መ. የካቲት ሃያ አንድ ሁለት ሺ አራት
4. በዓለም ላይ በትምባሆ ምክንያት በየዓመቱ ስንት ሚሊዮን ሰዎች ይሞታሉ?
   ሀ. አምስት መቶ ሚሊዮን ሐ. አራት ሚሊዮን
   ለ. ሃምሳ ሚሊዮን መ. አስራ አምስት ሚሊዮን
5. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?
   ሀ. ሰዎች ትምባሆ እንዲጠቀሙ ማበረታታት
   ለ. የትምባሆ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በዓለም ላይ እንዲጨምር ማበረታታት
   ሐ. የትምባሆ ጠቀሜታን ማብራራት
   መ. የትምባሆን ጉዳት ማብራራት

ተግባር ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ትንበያ | ሀ. ፋንታ |
| 2. ድርሻ | ለ. ተወሰነ |
| 3. ልውውጥ | ሐ. አዘጋጀ |
| 4. ፀደቀ | መ. ሽግግር |
| 5. ቀረፀ | ሠ. ቁጥር |
| 6. ያውካል | ረ. መረዳት |
| 7. አሃዝ | ሰ. ግምት |
| | ሸ. ይረብሻል |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

ተግባር፡-

ስለ ትምባሆ ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የምንባቡን መልዕክት ጠቅለል አድርጋችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### "እኔን ያየ ይቀጣ"

❖ ቅድመ ንባብ

1. ከታች በትይዩ ከቀረቡት ምስሎች ምን ተረዳችሁ?
2. በአካባቢያችሁ ወጣቶች በምን በምን ሱስ ውስጥ ተጠምደው አይታችኋል?
3. ሰዎች ወደሱስ እንዳይገቡ ምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?

❖ የማንበብ ሂደት

ተግባር አንድ፡-

“እኔን ያየ ይቀጣ” የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ምላሽ እየሠጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

**“እኔን ያየ ይቀጣ”**



በ2002 ዓ.ም በተሰጠው የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የወላጆቹን እና የትምህርት ቤቱን ስም ከፍ አድርጎ አስጠርቷል፡፡ በ2003 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሲቪል ምህንድስና ትምህርት ክፍል ተመድቦ ወደዚያው አቀና፡፡ ለቤተሰቡ የበኩር ልጅ ሲሆን በጥሩ በስነ ምግባር የታነፀና ትምህርቱም ጠንካራና ታታሪ ልጅ ነው፡፡

ተማሪ አንዷለም ተግባቢና አስተዋይ ልጅ በመሆኑ ከጓደኞቹ ለመግባባት ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ለግቢው አዲስ ቢሆንም ሰላምታ አሰጣጡ በስነ-ምግባር ተኮትኩቶ ያደገ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከአንዷለም ጋር በአንድ ዶርም የተመደቡት ስድስት ተማሪዎች ናቸው። ከሁሉም ተማሪዎች በበለጠ ከተማሪ ሙጂብ ጋር በጣም ተወዳጅተዋል፤ በግቢው ውስጥ እንዲሁም ወደ ክፍልና የመመገቢያ አዳራሹ ሲሄዱ ተለያይተው አያውቁም።
የትምህርት አሰጣጡ፣ የምግቡ ሁኔታ፣ የአየር ፀባዩና የቤተሰብ ናፍቆት ቢያስቸግራቸውም ሁለቱን ከመግባባት አላገዳቸውም። አንድ የትምህርት ክፍል ስለደረሳቸው በጋራ ያነባሉ፤ ይመገባሉ፤ እየተጋገዙ ጥሩ ውጤት ያመጣሉ። አንዷለም በክፍል ውስጥ በመሳተፉ መምህሮቹ ይወዱታል፤ በዚሁ ዓመት በትምህርቱ ከፍተኛ ውጤት አምጥቷል።

በአዲስ ዓመት የመስከረምን መጥባት ተከትሎ ዩኒቨርስቲያቸው የሁለተኛ ዓመት የቴክኖሎጂ ተማሪዎችን ጠራ። ተማሪ አንዷለም ለሁለት ወር ከቤተሰቡ ጋር እረፍቱን ካሳለፈ በኋላ እንደገና ወደ ግቢ ተመልሶ ከጓደኞቹ ጋር ተገናኝቷል። ምንም እንኳን ዩኒቨርስቲውን እየለመዱት ቢመጡም ዓመት እየጨመረ በመጣ ቁጥር የትምህርቱም ክብደት ጫን እያለ በመምጣቱ የማንበቢያ ሰአታቸውን ለማሻሻል ተስማሙ፤እንቅልፋቸውን እንዴት ማሸነፍ እንዳለባቸው ግራ በተጋቡበት ሰዓት መፍትሄ ነው ያሉትን ሀሳብ ጫት በመቃም ለመነቃቃት እና በደንብ ለማንበብ ወሰኑ።

ቀን ቀንን አየወለደ የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ተጠናቆ የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት አዳዲስ ኮርሶችን ተመዝግበው መውሰድ ጀምረዋል። እንደዋዛ እንቅልፍን አባሮ በማጥናት ሰበብ የተጀመረው ጫት አሁን ወደ ሱስ ደረጃ አድጎ ሲጋራን ወደማጨስም ተሸጋግሯል። ስነ-ምግባሩ፣ ትህትናው እና ጉብዝናው እንደጉም በኖ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የአንዷለም ሁለንተናዊ ባህሪ ተቀይሯል። ይባስ ብሎ የዶርም አባል ተማሪዎች ሲጋራ እያጨሰ አላስተኛ ብሎናል

ብለው ለዶርም ተቆጣጣሪው ከሰውታል፡፡

ያኔ በጉብዝናውና በስነ-ምግባሩ የሚወዱት መምህሮቹ በድርጊቱ ተበሳጭተው ደጋግመው መክረውታል፡፡ ቢሆንም ከዚህ ድርጊቱ ሊመለስ አልቻለም፡፡ ከጊዜ በኋላ ይህ አሳፋሪ ድረጊቱ ከዩኒቨርስቲው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ደረሰ፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከቀረበው ታሪክ ምን ተረዳችሁ? ባለታሪኩ ወደፊት ምን የሚገጥመው ይመስላችኋል?

በተደጋጋሚ ተመክሮ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ተመልሶ ላይወጣ ሰፊ የሱስ ባህር ውስጥ በመስመጡ ሊመለስ አልቻለም፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች ማስታወቂያ ቦርድ ላይ ውጤታቸውን ለማየት ቆመው ይተራመሳሉ፤ ከማስታወቂያ ቦርዱ በቀኝ በኩል ከፍ ብሎ የአንዷለምን ከዩኒቨርስቲ መባረር የሚያሳውቅ ወረቀት ተለጥፏል፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች ደነገጡ "አመት ባለሞላ ጊዜ ውስጥ የሰው ልጅ ባህሪ እንዲህ ሲቀያየር ያሳዝናል" አለች ከመካከላቸው አንዷ ሁሉም በመገርም ተመለከቷት፡፡

አንዷለም ወደ ቤተሰቦቹ መመለስ አልፈለገም፡፡ መባረሩ አላስጨነቀውም ግን ያኔ ስለ እሱ የመሰከሩ አንደበቶች፣ ስለ እሱ ስነ-ምግባርና ታታሪነት ያጨበጨቡ እጆች ታወሱት፡፡ አሁን ከትምህርት ተባረረ ሲባል ምን እንደሚፈጠር ሱስ ባደነዘዘው ጭንቅላቱ ማሰብ ጀመረ፡፡ ወደ ቤቱም አልተመለሰም በዚህም ምክንያት የደብዛው መጥፋት ያሳሰባቸው ቤተሰቦቹ እየተመላለሱ ቢፈልጉትም የውሀ ሽታ ሆኖባቸው እጅጉን ተጨንቀዋል፡፡

የቅርብ ጓደኛው የነበረው ሙጂብ እንደሱ ሱስ ውስጥ ገብቶ የነበረ ቢሆንም የሰውን ምክር በመስማቱ ከገባበት ሱስ ቶሎ ተመልሶ

በአሁኑ ጊዜ ተመርቆ እዚሁ አዲስ አበባ ላይ በኮንስትራክሽን ሙያ ውስጥ ተሰማርቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ የሰውን ምክር መስማት የተሳነው አንዷለም ግን መጨረሻው ሳያምር ብርድና ረሀብ እየተፈራረቁበት ኑሮውን በጎዳና ላይ አድርጓል፡፡ ሁሌም ጧት ጧት ለስራ የሚወጡ ሰዎች አንዷለም የቆሻሻ ገንዳ ውስጥ የጫት ገረባ ሲያገላብጥ ማየት የለመዱት ተግባር ሆኗል፡፡

በርካታ ወጣቶች ልክ እንደ አንዷለም ሳያስቡት ወደ ሱስ ውስጥ ይገቡና መውጣት ይሳናቸዋል፡፡ ቤተሰብና ሀገር ትልቅ ተስፋ ጥለውባቸው ሳለ እነሱ ግን ለቤተሰብና ለሀገር ይቅርና ለራሳቸውም መሆን አቅቷቸው አወዳደቃቸው ከፍቶ ይቀራል፡፡ ስለዚህ ወደ ሱስ ከገቡ በኋላ በቀላሉ ለመውጣት ስለሚያስቸግር ከእንደዚህ አይነት ድርጊት መቆጠብ ይገባል፡፡

❖ አንብቦ መረዳት

ተግባር አንድ

የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ ሀሳብ ከያዙ እውነት ትክክለኛ ሀሳብ ካልያዙ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡ ለመልሳችሁ ምክንያት ስጡ፡፡

1. አንዷለም ወደ ሱስ ውስጥ የገባው ከመጀመሪያውም ፍላጎት የነበረው በመሆኑ ነው፡፡
2. ባለታሪኩ አወዳደቁ የከፋው የሰው ምክር መስማት ባለመቻሉ ነው፡፡
3. ለጥናት ተብሎ የሚጀመር ጫት መቃም ወደ ለየለት ሱስ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡
4. ለአንዷለም ከዩኒቨርስቲ መባረር ምክንያት የውጤቱ መቀነስ ነው፡፡
5. በምንባቡ መሰረት ባለ ታሪኩ መጨረሻ ላይ ከሱስ ተመልሶ

ከዩኒቨርስቲ ተመረቋል፡፡

6. የአንዷለም የቅርብ ጓደኛ ሙጂብ የጓደኛው ግፊት ተጽዕኖ ቢያሳድርበትም ይህን ተቋቁሞ ለውጤት በቅቷል፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

ከታች ለቀረቡት ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት እና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የበኩር
2. ተኮትኩቶ
3. መጥባት
4. ጠነሰሱ
5. ነጎደ
6. ይተራመሳሉ
7. ደብዛው
8. የውሃ ሽታ
9. ይሳናቸዋል
10. ከፍቶ

### ተግባር ሶስት፡-

በምንባቡ መሰረት ወጣቱን ወደ ሱስ ውስጥ የሚያስገቡ ምክንያቶችን እና የሚያስከትሉትን ጉዳት በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በተወካያችሁ አማካኝነት በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

## ማስታወሻ

### ስርዓተ ነጥቦች

በወረቀት ላይ የሰፈረ ሀሳብ መልዕክቱ ግልፅ ሆኖ እንዲተላለፍ ስርዓተ ነጥቦች የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ በርካታ ስርዓተ ነጥቦች አሉ፡፡ ከነዚህም ውሰጥ ዋና ዋናዎቹን እንመልከት፡፡

1. አንድ ነጥብ (•) ፡- አንድ ነጥብ ይዘት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል፡፡
   - ቃላትን በምህፃረ ቃል አሳጥሮ ለመፃፍ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ተ.መ.ድ       የተባበሩት መንግስታት ድርጅት

   - ብርና ሳንቲሞችን እንዲሁም ሙሉና ክፍልፋይ ቁጥሮችን ለመለየት

ምሳሌ፡- 6.50       ስድስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም

2.9       ሁለት ነጥብ ዘጠኝ

2. ሁለት ነጥብ (፡)፡- ሁለት ነጥብ ከታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡
   - በቃላት መካከል በመግባት አንዱን ቃል ከሌላው ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ቶሎሳ፡ምሳውን፡በላ፡፡

   - ሰዓትና ደቂቃን ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- 2፡30       ሁለት ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ

3. ሁለት ነጥብ ከሰረዝ (፡-) ፡- ሁለት ነጥብ ከሰረዝ ቀጥለው የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡
   - መሪ ሃሳቡን ተከትለው ወደሚመጡ ዝርዝር ነገሮች ለማንደርደር ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ቋንቋ አራት ክሂሎች አሉት፡፡ እነሱም፡- ማንበብ፣ መፃፍ፣ መናገርና ማዳመጥ ናቸው፡፡

- ምሳሌ ለመጥቀስ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ኢትዮጵያ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ናት፡፡

4. ነጠላ ሰረዝ (፣) ፡- ነጠላ ሰረዝ ተመሳሳይ ሙያ ያላቸውን ተከታታይ ቃላት ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ድርጅታችን ጨው፣ ስኳር፣ ዘይት ወዘተ. ያከፋፍላል፡፡

5. ድርብ ሰረዝ (፤) ፡- ድርብ ሰረዝ አቻ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮች ለማያያዝ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- በጧት ተነሳ፤ ልብሱን ለበሰ፤ ቁርሱን በላ፤ ደብተሩን ይዞ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

6. ትዕምርተ-አንክሮ(!) ፡- ቃለ አጋኖ በመባልም ይጠራል፡፡ መገረምን፣ መደነቅን፣ ንዴትን፣ ትእዛዝን፣ ማሞካሸትን፣ ማድነቅን፣ ቁጣን፣ ጨኸትንና ለቅሶን የመሳሰሉትን ለማመልከት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ዛሬ መሄድ አለብህ! (ትእዛዝን ለመግለፅ)

7. ትዕምርተ-ስላቅ (¡)፡- ምፀትን፣ ቀልድና ተሳልቆን ያመለክታል፡፡
   ምሳሌ፡- አቤት ውፍረት¡ በር አያስገባትም እኮ (ቀጭን የሆነችን ልጅ)

8. ትምህርተ-ጥያቄ(?)፡- የጥያቄ ምልክት በመባልም ይታወቃል፡፡ ጥያቄያዊ ፅሁፎችን ለመፃፍ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- የቤት ስራህን ሰርተሃል ?

9. ቅንፍ ( )፡- ወይም የሚለውንም አማራጭ ቃል ተክቶ ይገባል፡፡
   ምሳሌ፡- ነገ ጠዋት ወላጅህን (አሳዳጊህን) ይዘህና፡፡

ተግባር አንድ፡-

ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ከታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ-ነጥብ አስገቡ፡፡

ምሳሌ፡- ከየት እየመጣህ ነው
ከየት እየመጣህ ነው?

1. በአዋሽ ፓርክ ውስጥ አንበሳ ቀበሮ ጅብ ሚዳቋ ዝንጀሮ እና ጦጣ የመሳሰሉት እንስሳት ይገኛሉ
2. በርቀት እንደተቀመጠ አያት እሷም አይታው ነበር
3. ወደዚህ ስፍራ ከዚህ ቀደም መጥቶ አያውቅም
4. ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው በማለት ቢኒያም በለጠ ተናገረ
5. የትምህርት ቤቱን ስርዓት ማክበር የሁሉም ተማሪ ግዴታ ነው
6. ጎሽ የኔ አንበሳ ከመቶው ሰላሳ አመጣህ
7. ተመድ የወባ በሽታ ወረርሽኝን ለመቀነስ ጠንክሮ እየሰራ ነው
8. ሀገርን የማልማት ኃላፊነት የማን ነው
9. የቀለም አባቴ መምህሬ ጎበዝ እንድሆን መከረኝ
10. ኢትዮጵያ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ናት እነሱም አባይ ባሮ ተከዜ ዋቢ ሸበሌ ወዘተ ናቸው፡፡

ተግባር ሁለት፡-

ከታች በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ አስገቡ፡፡

ግጥም 1 ልቦለድ 2 ተውኔት 3 እንዲሁም ሌሎች የስነ-ጽሁፍ ስራዎችን የሚፈጥርና የሚጽፍ አካል 4 ደራሲ 4 ይባላል 5 ፈጣሪ በገሃዱ ዓለም ሰውና ተፈጥሮን እንደፈጠረ ሁሉ ደራሲም በስነ-ጽሁፍ ዓለም የራሱን ሰዎች 6 ተፈጥሮ 7 ሀሳብና ሌሎች ነገሮችን ምናባዊ አድርጎ ይስላል 8 ነፍስ ይዘራባቸዋል 9 ቢፈልግ ይገድላቸዋል 10 ሲያሻውም እንደገና ሊያስነሳቸው ይችላል 11 ባጠቃላይ የተፃፈው ጽሁፍ ድርሰት ሲባል 12 ፀሀፊው ደግሞ ደራሲ ይባላል 13

## ክፍል አምስት:- ቃላት

### ተዘውታሪ ቃላት

ተግባር:-

በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ተዘውታሪ ቃላት ከታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛው ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ብልሀቶችን | ትልቅ | ክፍፍል |
| ውጤት | በለጋ | ለስቃይ |
| በፅኑ | ልማዳዊ | የውዴታ ግዴታ |

1. የተለያዩ የጥናት --------- በመጠቀም ውጤታማ መሆን አለብን፡፡
2. --------------- እድሜው በርካታ ኃላፊነቶችን ተቀብሏል፡፡
3. ግብር መክፈል የሁሉም ሰው ------------------- ነው፡፡
4. የወላጆቿንና የመምህሯን ምክር ባለመስማቷ ------- ተዳርጋለች፡፡
5. ሞሚና ----------- በመታመሟ ሆስፒታል ገባች፡፡
6. ጎጂ ----------- ድርጊቶችን መዋጋት የሁላችንም ኃላፊነት ነው፡፡
7. በቤተሰብ ውስጥ ትክክለኛ የስራ ---------------- መኖር አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት:- ሰዋስው

ተግባር:-

በምሳሌው መሰረጸጽትት አምስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ:- ገመችስ መጽሀፍ ማንበብ ስለሚወድ የተረት መጽሀፍ ገዛ፡፡

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለስርዓተ ነጥቦች፣ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር፣ አውዳዊ ፍቺና ተዘውታሪ ቃላት ተመልክተናል፡፡
- ስርዓተ ነጥቦች በወረቀት ላይ የሰፈረ ሀሳብ መልዕክቱ ግልፅ ሆኖ እንዲተላለፍ ለማድረግ የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ በፅሁፉ ላይ ስርዓተ ነጥቦችን አስተካክሎ ካለመጠቀም የተነሳ የዓረፍተ ነገሮቹ ትርጉም ሊያሻማ፣ ሊዛባ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊለወጥ ይችላል፡፡
- ተዘውታሪ ቃላት በእለት ተእለት ህይወታችን በብዛት የምንጠቀምባቸው (የማንገለገልባቸው) ቃላት ናቸው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ከታች በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ? | ፣ | ¡ | ፤ |
| ! | ፡፡ | “ ” | :- |

2. ቀጥለው ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አልማዝ ትምህርት ቤት መጣች፡፡

   ለ. ኢብራሂም ጠንክሮ ስላጠና ጥሩ ውጤት አመጣ፡፡

   ሐ. መምህሩ በመኪና ወደ መርካቶ ሄደ፡፡

   መ. የትምህርት ቤታችን ቤተ-መፃህፍት ግንባታ ተጠናቀቀ፡፡

3. ስለሱስ አስከፊነት የተገነዘባችሁትን በአጭሩ አብራሩ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ (፱)

## የሀገር ፍቅር

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-

- አዳምጣችሁ የጽሁፉን ፅንሰ ሀሳብ ከህይወታችሁ ጋር ታዛምዳላችሁ ፡፡
- የሀገር ፍቅርን ምንነት ትገልፃላችሁ፡፡
- ለተወሰነ ዓላማ ታነባላችሁ፡፡
- የሀገር ፍቅርን ታደንቃላችሁ፡፡
- ምስሎችን ትገልፃላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### “የአድዋ ድልና የሀገር ፍቅር ስሜት”




❖ ቅድመ ማዳመጥ

1. ርዕሱና የቀረበው ምስል ምን ግንኙነት ያለው ይመስላችኋል?
2. ሀገር ማለት ለእናንተ ምንድን ነው?
3. የሀገር ፍቅር ምንድን ነው? በምን በምን የሚገለፅ ይመስላችኋል?

❖ የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር፡-

“የአድዋ ድልና የሀገር ፍቅር ስሜት” የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

ተግባር አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. አስራ ሰባት አንቀፆች ያሉት የውጫሌ ውል የተደረገው ሚያዝያ 25/1880 ዓ.ም ነው፡፡
2. የአድዋ ጦርነት የተካሄደው በውጫሌ አካባቢ ነው፡፡
3. እቴጌ ጣይቱ ለአድዋ ጦርነት ድል መገኘት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡
4. ለመጀመሪያ ጊዜ የአድዋ ድል በዓል የተከበረው 1895 ዓ.ም ነው፡፡
5. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ጦር ሜዳ ሄዶ ያልተዋጋ ዜጋ አርበኛ ሊሆን አይችልም፡፡
6. አርበኝነት የሚለው ቃል ክብር፣ ማንነትና ተግባር የሚገለፅበት ቃል ነው፡፡

ተግባር ሁለት፡-

ከታች በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት ቀጥለው በቀረቡት ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛ አውዳቸው ውስጥ አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ገድል | ለመቀራመት | መና |
| የጋራ ክንዳቸውን | ሉዓላዊነት | የተከናነበበት |
| የአይበገሬነት | መናገሻ | አርነታቸውን |

1. በሀገር ---------------ላይ ከመጣ ጠላት ጋር ድርድር አያስፈልግም፡፡
2. አባቶቻችን ለሀገር ፍቅር ሲሉ የፈፀሙትን -------------እኛ ማስቀጠል አለብን፡፡

3. የሀገር ፍቅር ስሜት ከሰማይ የሚወርድ -------- ሳይሆን በጠንካራ ስራ የሚገለፅ ነው፡፡
4. አውሮፓዊያን የአፍሪካን አህጉር በቅኝ ግዛት ----------በርካታ ስልቶችን ተጠቅመዋል፡፡
5. የአፍሪካ ሀገራት ------------ ለማግኘት በርካታ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡
6. ዜጎች --------- አስተባብረው ሀገራቸው በምትፈልገው የስራ መስክ መሰማራት አለባቸው፡፡
7. የጀግና አባቶቻችን ----------ስሜት ሀገራችን ታፍራና ተከብራ እንድትኖር አድርጓል፡፡
8. አጼ ምኒልክ ወደ አድዋ የዘመቱት ከ------------ከተማቸው በመነሳት ነው፡፡
9. የአድዋ ጦርነት ወራሪው የኢጣሊያ ጦር የሽንፈትን ካባ -------- ነው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር

ከታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

1. የሐገር ፍቅር ለምን ያስፈልጋል? ምንስ ጥቅም አለው?
2. በአሁኑ ሰዓት ለሀገራችሁ ምን አስተዋፅኦ እያደረጋችሁ ትገኛላችሁ? ወደ ፊትስ ምን ለማድረግ አስባችኋል?

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### “የልብ ወጌሻው”



❖ ቅድመ ንባብ

1. ከላይ ከቀረበው ርዕስና ስዕል ምን ተረዳችሁ?
2. ለሀገራችን ትልቅ አስተዋፅኦ ካደረጉ ኢትዮጵያዊያን መካከል የምታውቋቸውን ተናገሩ፡፡
3. በሀገራችን ብቸኛ ስለሆነው የልብ ቀዶ ጥገና ማዕከል ምን ታውቃላችሁ?

❖ የማንበብ ሂደት

ተግባር አንድ

"የልብ ወጌሻው" የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ እየተነሳችሁ አንብቡ። መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ ስጡ።

## "የልብ ወጌሻው"

የዛሬ 43 ዓመት ገደማ በ1970 ዓ.ም በአሜሪካን ሀገር ነው በኢትዮጵያ የልብ ህክምና ማዕከል የማቋቋም ሀሳብ የተጠነሰሰው። በልብ ህክምና ሙያ ለመሰልጠን (ስፔሻላይዝድ ለማድረግ) በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቅኩበትን የትምህርት ማስረጃና የወደፊት ፍላጎቴን የሚገልጽ ሃሳብ ለኒዮርክ ዩኒቨርስቲ አቀረብኩ ።ቃለ መጠይቅ ያደረገችልኝ ፕሮፌሰር<< የምንቀበለው አስር ሰዎችን ነው ፤አንተ የተቀመጥከው አስረኛ ላይ ነው ፤ባቀረብከው ማመልከቻ ውስጥ ጥሩና ደስ የሚሉ ነገሮች አይቻለሁ ፤ስላቀድካቸው ነገሮች ከአንደበትህ መስማት እፈልጋለሁ ፤እውነት ትምህርቱን ስትጨርስ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰህ በልብ ህክምና ትሰራለህ?>> በማለት ስትጠይቀኝ አዎ! በማለት መለስኩላት።

ፕሮፌሰሯ<<ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰህ የልብ ህክምና ሆስፒታል በሌለበት ፣መስሪያ ቤት በሌለበት ፣ባለሙያ በሌለበት ፣እንዴት ነው የልብ ህክምና እሰራለሁ የምትለው?>>ሲሉ ደጋግመው ጠየቁኝ እኔም በመላ ልወጣው እንደምችል ነገርኳቸው?።

ወደ ቤቴ ስመለስ ፊቴ ላይ የመከፋትና የሀዘን ስሜት ያየችው ባለቤቴ <<ምነው ተከፋህ አልተቀበሉህም አንዴ?>>በማለት ጠየቀችኝ። መቀበሉንስ ተቀብለውኛል ነገር ግን አራት ነገሮች አርግዤ መጣሁ አልኳት፤ የልብ ሆስፒታል መገንባት፣ውድና

ልዩ የሆኑትን የህክምና መሳሪያዎች ማሟላት፣የልብ ሃኪም ማፍራትና ሆስፒታሉን በገንዘብ አቅም ዘላቂና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል የሚሉት በዶክተር በላይ አበጋዝ የተረገዙት ራዕይዎች መሆናቸውን ዘርዝረው አስረዷቸው፡፡

ተማሪዎች እስካሁን ከቀረቡት አንቀጾች ምን ተረዳችሁ?ባለ ታሪኩ ራዕያቸው የሚሳካ ይመስላችኋል?

ለዚህ ራዕያቸው ሳይታክቱ የወጡና የወረዱት ዶክተር በላይ አበጋዝ ሆስፒታሉን በኢትዮጵያ ህዝብና በሼህ መሃመድ ሁሴን አሊ አላሙዲ ትብብርና ድጋፍ አሰርተው በ2001 ዓ.ም አስመርቀዋል፡፡ ውድ የሆኑ ዘመናዊ የልብ ቀዶ ህክምና መሳሪያዎችንም በአጋር ድርጅቶች ደጋፍ አሟልተዋል፡፡የልብ ቀዶ ጥገና ሃኪሞችንም በሚኒያ ፖሊስ የልብ ቀዶ ሃኪም በሆኑት በዶክተር ቪብ ክሽንትና ታዋቂ በሆነው የህንድ ናርያና ሆስፒታል በሰለጠኑና ዛሬ ለተደረሰበት ደረጃ ማድረስ የቻሉ የአገር ባለ ውለታ ናቸው፡፡

እኚህ የአገር ባለውለታ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት የምስጋናና የእውቅና የክብር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡የተሰበረ ልብ ጠጋኙ ይህ ሽልማት ቢያንስባቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይደለም፡፡በኢትዮጵያ በየ አመቱ 50 ሺህ ህጻናት ከልብ በሽታ ጋር ይወለዳሉ፡፡በተጨማሪም ከ50 እስከ 60 ሺህ የሚሆኑት ደግሞ ከተወለዱ በኋላ የልብ በሽተኛ ይሆናሉ፤ህክምናውን ባለማግኘታቸው ይሞታሉ፡፡ ይህንን ታሪክ ለመቀየር ላለፉት 41 አመታት የደከሙትን ኢትዮጵያዊ ሁሉም ወገን ሊያመሰግንና አረዓያነታቸውን ሊከተል ይገባል፡፡ የዶክተር በላይን መንገድ ልብ ብሎ ላስተዋለ ልባም ሁሉ የሚናገረው ሀቅ ማንም ቢሆን በተሰማራበት የሙያ መስክ ሊደክምለትና ሊያሳካው የሚገባው የአገር ውለታ እንዳለበት ነው፡፡

ምንጭ፡- አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ቁጥር 285፣ሰኔ 15/2011ዓ.ም

❖ አንብቦ መረዳት

### ተግባር አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. በሀገራችን በየዓመቱ ስንት ህጻናት ከልብ በሽታ ጋር ይወለዳሉ?
2. የባለታሪኩ ራዕይ ምን ነበር? አብራርታችሁ ተናገሩ፡፡
3. ዶክተር በላይ አበጋዝ አራት ነገሮችን አርግዤ መጣሁ ካሉት ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡
4. ባለታሪኩ ለሀገርና ለወገን ላደረጉት አስተዋፅኦ የእውቅና ሽልማት የተበረከተላቸው ከማን ነው?
5. የልብ ህሙማን መርጃ ማዕከሉ መቼ ተመረቀ?
6. ከዶክተር በላይ አበጋዝ ታሪክ ምን ቁም ነገር አገኛችሁ?

### ተግባር ሁለት፡-

ቀጥለው ለቀረቡት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

1. መላ
2. አርግዤ
3. ሳይታክቱ
4. አጋር
5. ውለታ
6. ልባም
7. ሀቅ
8. ወጌሻ
9. እውቅና
10. መከፋት

### ተግባር ሶስት፡-

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን የንባብ ማስታወሻ በመውሰድ “መረጃን ለማግኘት ማንበብ” የሚለውን የንባብ ዓላማ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ በቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉትን የአሃዝ (የቁጥር) መረጃዎች ከታች በቀረበው ሰንጠረዝ ውስጥ ሙሉ፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከ2003 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና አገልግሎት የመድሀኒት ስርጭት መጠንን እንደሚከተለው ይገለፃል፡፡ በ2003 ዓ.ም መድሀኒቱን ከጀመሩ 333,434 ሰዎች መካከል 247,805 ያህሉ መድሀኒት በመውሰድ ላይ ያሉ ሲሆን ይህ በመቶኛ ሲሰላ 42.65 % ይሆናል፡፡ በ2004 ዓ.ም መድሀኒቱን ከጀመሩ 342,954 ሰዎች መካከል ደግሞ 270,543 ያህሉ መድሀኒቱን ወስደዋል፤ይህ በመቶኛ ሲሰላ 44.92% ነው፡፡

የ2005 ዓ.ም ስንመለከት ደግሞ መድሀኒቱን ከጀመሩ 439,301 ሰዎች መካከል 308,860 ያህሉ መድሀኒቱን የወሰዱ ሲሆን ስሌቱ 41.49 % ነው፡፡ በ2006 ዓ.ም ደግሞ ከ492,689 ሰዎች መካከል 344,344 ሰዎች መድሀኒቱን ተጠቅመዋል፡፡ ይህ ደግሞ በመቶኛ ሲሰላ 42.73% ነው፡፡ (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር)

| ከ2003-2006 ዓ.ም የፀረ ኤች አይ ቪ መድሀኒት ስርጭት መጠንን የሚያሣይ ሰንጠረዥ | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2003 ዓ.ም | | | 2004 ዓ.ም | | | 2005 ዓ.ም | | | 2006 ዓ.ም | | |
| የጀመሩ | የወሰዱ | በ% | የጀመሩ | የወሰዱ | በ% | የጀመሩ | የወሰዱ | በ% | የጀመሩ | የወሰዱ | በ% |
| 333,434 | 247,805 | 42.65 | | | | | | | | | |

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት



ተግባር አንድ፡-

ከላይ የቀረበውን ምስል መሰረት በማድረግ ስለ አድዋ ጦርነት ሁለት አንቀፅ ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ያልተዘወተሩ ቃላት

ተግባር፡-

ከታች በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ለተሰመረባቸው ያልተዘወተሩ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ወንደሰን ከባላጋራዎቹ ጋር ከረጅም ዓመታት በኂላ እርቅ ፈፀመ፡፡
2. ሸማኔው የሰራልኝ ቡልኮ ለአይን ያሳሳል፡፡
3. በእንሰት ቅጠል የተጋገረው ዳቦ ይጣፍጣል፡፡
4. ሁሉም ቤተሰብ ከሰፌው ማዕድ የአቅሙን ያህል ተቋደሰ፡፡
5. ሙክታር ጭራሮ ለመልቀም ወደ ጫካ ሄደ፡፡
6. ፈተና ሲደርስ ጉድ ጉድ ማለት መፍትሄ አይሆንም፡፡
7. ለሰርጉ በተጣለው ዳስ ውስጥ ጭፈራው ደርቷል፡፡
8. ንጉሱ የንግስናውን ዘውድ ደፋ፡፡
9. ለዓይን ያዝ ሲል ጉዞውን ጀመረ፡፡
10. ለጊዜያዊ ጥቅም ተብሎ ሀገርን የሚጎዳ ተግባር መፈፀም ተገቢ አይደለም፡፡

ተግባር ሁለት:-

ከታች የቀረቡት ቃላት ከግጥም ውስጥ የወጡ ናቸው ግጥሙን በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ለቃላቱ አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሁለት በሬ ሰዎች ሲያልፉ በጎዳና፣
እቃ መሬት ወድቆ ብልጭ ሲል አዩና፣
ተሽቀዳድመው ሄደው ከቦታው ሲደርሱ፣
ተፎካከሩበት ሁለቱም ሊያነሱ።

በኋላም ተማተው በጥፊ በጡጫ፣
አንደኛው ነጠቀ በጉልበቱ ብልጫ፣
አገላበጠና ቢመለከት ፈጥኖ፣
እቃውን አገኘው ማበጠሪያ ሆኖ ።

እስኪ ሁላችሁም በሉ ፍረዱት፣
እሱ ራሰ በራ ጠጉር የለበት፣
ሮጦ ተማቶ ቀምቶ ቢያመጣ፣
ምን ያድርግለታል ሚዶ ለመላጣ።

(ከበደ ሚካኤል)

1. ጎዳና
2. ተሽቀዳድመው
3. ተፎካከሩት
4. ተማተው
5. በጉልበቱ
6. አገላበጠ
7. ፍረዱት
8. ሚዶ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

ተግባር፡-

ቃላትን በትክክለኛ ቅደም ተከተላቸው አዋቅራችሁ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

1. ቤት ገባ ሀኪም ስለገጨው መኪና፡፡
2. ተዳረገች ስለማትጠብቅ ለጽኑ የግል ንፅህናዋን ህመም፡፡
3. ያስፈልጋል ከውጭ ለመጠበቅ ሀገርን ጠላት አንድነት ወራሪ ፡፡
4. ሰርተዋል ሁሉም ተማሪዎች የቤት ስራውን በጥሩ ሁኔታ፡፡
5. ስልጋል ንፅህናን መጠበቅ የአካባቢ መጠበቅ የውሃ ብክለትን ለመከላከል፡፡
6. ትናንት ማታ የገዛችልኝ ጠፋብኝ ቦርሳ አክስቴ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለንባብ አይነቶችና ዓላማ እንዲሁም ስለሀገር ፍቅር ምንነትና መገለጫዎች ተምረናል፡፡
- የንባብ ዓይነቶች (መረጃ ከማግኘት) አንፃር የዝግታ ንባብ፣ የፍጥነት ንባብ፣ የገረፍታ ንባብ ወዘተ. በማለት ይከፈላሉ፡፡
- ሰዎች ለተለያዩ ዓላማዎች ያነባሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡- ለጥንቃቄ፣ ለመዝናናት፣ አዲስ ነገር ለመማርና ለማወቅ እንዲሁም መረጃን ለማግኘት ወዘተ. የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- የሀገር ፍቅር ማለት ሀገርን የሚጠቅም ስራ መስራት፣ መስዋዕትነትን መክፈል ወዘተ. ማለት ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. አምስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡
2. የንባብ አይነቶችና ዓላማዎችን ዘርዝሩ፡፡
3. የሀገር ፍቅር ምንድን ነው? መገለጫዎቹንም ዘርዝሩ፡፡

# ምዕራፍ አስር (፲)

## ቃላዊ ግጥም

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ፡-**

- ዕሁፉን አዳምጣችሁ ትተረጉማላችሁ፡፡
- ለቃላዊ ግጥም ብያኔ ትሰጣላችሁ፡፡
- የቃላዊ ግጥም አይነቶችን ታብራራላችሁ፡፡
- የቅኔ ምንነትን ይለያሉ
- ዜማውን ጠብቃችሁ ግጥም ታነባላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### "ቃላዊ ግጥም"





❖ ቅድመ ማዳመጥ

"ቃላዊ ግጥም" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ የሰንጠረዡን ሁለት ረድፎች በደብተራችሁ ላይ በትክክል ሙሉ፡፡ ካዳመጣችሁ በኋላ ተመልሳችሁ ያወቃችሁት የሚለውን ክፍል በትክክል ሙሉ፡፡

| ቃላዊ ግጥም | | |
|---|---|---|
| ስለቃላዊ ግጥም የማውቀው | ስለቃላዊ ግጥም ማወቅ የምፈልገው | ስለቃላዊ ግጥም ተጨማሪ ያወቅሁት |
| - | - | - |
| - | - | - |
| - | - | - |
| - | - | - |

❖ የማዳመጥ ጊዜ

ተግባር ፡-

"ቃላዊ ግጥም" የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስታወሻ በመያዝ በንቃት አዳምጡ፡፡ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

❖ አድምጦ መረዳት

## ተግባር አንድ፡-

ከታች የቀረቡት ከማዳመጥ ምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ቃላዊ ግጥም ከትውልድ ወደ ትውልድ በጽሁፍ የሚተላለፍ የስነ-ቃል አይነት ነው፡፡
2. የቃላዊ ግጥም ባለቤት ማህበረሰቡ (ህዝቡ) ነው፡፡
3. የአንድ ማህበረሰብ ባህል በቃላዊ ግጥሞች አማካኝነት ጎልቶ ይወጣል፡፡
4. ቃላዊ ግጥሞች የቋንቋ አጠቃቀማቸው በዘፈቀደና ያልተቆጠበ ነው፡፡
5. የሰው ልጆች ሀሳባቸውን በጽሁፍ መግለጽ ከመጀመራቸው በፊት ቃላዊ ግጥምን ይጠቀሙ ነበር፡፡

## ተግባር ሁለት፡-

በ “ሀ” ስር ለቀረቡት ቃላት በ “ለ” ስር ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ክስተት | ሀ. መጀመሪያ |
| 2. ደራሲ | ለ. ያበለጽጋል |
| 3. ነጎደ | ሐ. ፀሀፊ |
| 4. ጎልቶ | መ. የማይዘረዝር |
| 5. መነሻ | ሠ. በፍጥነት ሄደ |
| 6. አስማምቶ | ረ. ግልጽ ሆኖ |
| 7. ያጎለብታል | ሰ. አሻራ |
| 8. ቁጥብ | ሸ. አጋጣሚ |
| | ቀ. መርማሪ |
| | በ. አስተካክሎ |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፡-

በአካባቢያችሁ እናንተ ወይም ሌሎች ሰዎች የሚያዜሟቸውን ቃላዊ ግጥሞች ሰብስባችሁ አምጡ፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

ከሰበሰባችኋቸው ቃላዊ ግሞች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በክዋኔ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### "ቃላዊ ሀብቶቻችን"

❖ ቅድመ ንባብ

1. ከታች የቀረበው ምስል ምንን የሚገልጽ ይመስላችኋል?
2. ቃላዊ ግጥም ከተፃፈ ግጥም በምን የሚለይ ይመስላችኋል?
3. የምታውቋቸውን የቃላዊ ግጥም አይነቶች ዘርዝሩ፡፡

❖ የማንበብ ሂደት

### ተግባር

"ቃላዊ ሀብቶቻችን" የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ እየተነሳችሁ አንብቡ፤ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

## “ቃላዊ ሀብቶቻችን”



ቃላዊ ግጥም በግጥም መልክ ከሚቀርቡ ወይም ከሚዜሙ የስነ-ቃል ዓይነቶች ውስጥ የሚመደብ ነው። የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች በጣም በርካታ ናቸው። እነሱም:- የባዕላት፣የፋከራ፣የልመና፣ የሙሾ፣የስራ ግጥሞች ወዘተ. በቃላዊ ግጥም ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። ቃላዊ ግጥሞች እንደየሁኔታው ሊዜሙ ወይም በእንጉርጉሮ ሊቀርቡ ይችላሉ። ቃላዊ በመሆናቸው በአብዛኛው አጫጭር ናቸው። እነዚህ ቃላዊ ግጥሞች ምጣኔ፣ ምትና ዜማ አላቸው። ግጥሞቹ በአብዛኛው በእኩል ጊዜ እንዲያልቁ ሆነው የተመጠኑ ሀረጋትን ይይዛሉ። የተመጠኑት ሀረጋት በተወሰነ ጊዜ ሲደጋገሙ ደግሞ ምትን ይፈጥራሉ፤ ሲነበቡም ዜማ አላቸው። ግጥሙ እንደሚገልፀው ስሜት ዜማው ይለያያል።

በአብዛኛው የገጠሩ ህዝብ በጋራም ሆነ በተናጥል አንድ ስራ በሚያከናውኑበት ጊዜ ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስራት ስለሚያግዘው ቃላዊ ግጥሞችን እየደረደረ ያንጎራጉራል፤ ይዘፍናል፤ ይጨፍራል። በተለያዩ ቡድናዊ የስራ አጋጣሚዎች ላይ ለምሳሌ በአጨዳ፣ በአረም፣ በቤት ስራ ጊዜ ወዘተ. ስራዎችን ሲያከናውን ያዜማል። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ለምሳሌ በሰርግ፣ በለቅሶ በጦርነት ወቅት ህዝቡን ለማነቃቃትና ስሜትን ለመግለፅ የሚቀርቡ እንደ እንጉርጉሮ፣ ፉከራና ቀረርቶ

የመሳሰሉት ቃላዊ ግጥሞች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከቀረበው ምንባብ ምን ተረዳችሁ? በቀጣዩ የምንባብ ክፍልስ ምን አይነት ቃላዊ ግጥሞች የሚቀርብ ይመስላችኋል?

ሀ. የስራ ላይ ግጥሞች

እኔስ አርሳለሁ አልመረርም፣
ችግር በወንጭፍ አይባረርም፡፡

ለ. በልጆች ጨዋታ የሚዜሙና የሚገጠሙ

እንቡሼ ገላ እንቡሼ ገላ፣
ሜዳ ነው ብዬ ገደል ልገባ፡፡
ገደል ገብቼ ልወጣ ስል፣
ጅቡ መጣብኝ ከእግሬ ስር፡፡

ሐ. የበዓል ጊዜ የሚዜሙና የሚገጠሙ

እዚያ ማዶ (ሆ) ጭስ ይጨሳል (ሆ)
አጋፋሪ (ሆ) ይደግሳል (ሆ) ...

መ. የሽለላ ቃላዊ ግጥም

አባይ ጥቁር ነበር ከሰል የመሰለ፣
እየቀላ መጣ ደም እየመሰለ፡፡

ሰ. የፉከራ ቃላዊ ግጥም

በል በለውና ጉልበት ጉልበቱን ፣
እያነከሰ ይውጣው ዳገቱን፡፡

በአጠቃላይ ቃላዊ ግጥሞች የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ ወዘተ. ልማዶችን የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው እንደሌሎች ቅርሶች ሁሉ እነዚህን ቃላዊ ሀብቶች ልንጠብቃቸው ይገባል፡፡

(አንተነህ ፣2001፣የአማርኛ ስነ- ቃል አጭር ቅኝት እና ዘሪሁን፣1992፡፡የስነ- ፅሁፍ መሰረታዊያን፡፡ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

❖ አንብቦ መረዳት

**ተግባር አንድ፡-**

**ቀጥለው የቀረቡትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. የቃላዊ ግጥም አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. ቃላዊ ግጥሞች በአብዛኛው የሚከወኑት በየት አካባቢ ነው?
3. ሰዎች በጋራም ሆነ በተናጥል ስራ ሲሰሩ ቃላዊ ግጥሞችን ለምን ያዜማሉ?
4. በአብዛኛው ቃላዊ ግጥሞ ቅርጻቸው ለምን አጭር ይሆናል?
5. በቃላዊ ግጥም የማህበረሰቡ ምን ምን ጉዳዮች ይዳሰሳሉ?

**ተግባር ሁለት፡-**

**ከታች የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች አይነት ለይታችሁ ተናገሩ፡፡**

ምሳሌ፡- እንኳን ጥሬውን ይብላው ዱቄቱን፤
በሬ አይደለም ወይ ያቀናው ቤቱን፡፡ (የስራ ቃላዊ ግጥም )

1. መታመን ነው እንጂ የሰው ቁም ነገሩ፤
   ሞትማ ግብሩ ነው ለሰው ልጅ ባገሩ፡፡
2. እንዳላይሽ እንዳላይሽ፤
   ወርቁን ጋረዱት ሚዜዎችሽ፡፡
3. ይህ አረም የሚሉት በጣም አደገኛ፤
   ጠዋት ማታ ቢነቅሉት አሁንም አፍለኛ፡፡
4. ገዳይ በየበሩ በየሸንተረሩ፤
   ይፈለግ የለም ወይ የአዳኙ ውሻ ዘሩ፡፡
5. በለው በጓንዴ ባፈ ድምድሙ፤
   የማታ ጮራ ሲመስል ደሙ፡፡
6. አይኔን ግንባር ያድርገው ብላችሁ አትማሉ፤
   ይቸግር የለም ወይ መሪ ማባበሉ፡፡
7. ኧረ አምሳለ
   ኧረ አምሳለ
   ኧረ ሆይ ኧረ ሆይ

ተግባር ሶስት፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ከማስታወሻው በታች የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች ዜማቸውን ጠብቃችሁ አንብቡ፡፡

## ማስታወሻ

### ግጥም እንዴት ይነበባል?

ግጥም የሚዋቀረው ሐረግ በሐረግ ነው፡፡ ሐረጎች ደግሞ ስንኝን ይመሰርታሉ ፡፡ ሐረግ በግጥም ውስጥ በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ ሲሆን ስንኝ ደግሞ አንድ የግጥም መስመር ነው፡፡ አንድን ግጥም ዜማውን ጠብቀን ለማንበብ የሚከተሉትን መመሪያዎች መተግበር ተገቢ ነው፡፡ እነሱም፡-

- በሐረጎችና በስንኞች መጨረሻ የተወሰነ የጊዜ ቆይታ ማድረግ
- ግጥሙን በተገቢ ዜማዊ ቃና ማንበብ
- የተለያዩ የግጥም አነባበብ ስልቶችን ከመምህራን፣ ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥንና ከስነ-ጽሁፋዊ መድረኮች ወዘተ. ማዳመጥ
- ግጥሙ የቅስቀሳ፣ የሀዘን፣ የግርምት፣ የትዝብት፣ የውደሳ… መሆኑን በማጤን የአነባበብ ለዛውን እንደየግጥሙ ዓይነት እየቀያየሩ ለማንበብ መሞከር የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

1. አንድ እንጀራ በእኔ እንዴት ትኮራለህ፣ ከባለጠጋ ቤት ትነባበራለህ፡፡
2. እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ፣ግራ እጄ ሲመክት ቀኝ እጄ ተመታ፡፡
3. አንበሳው ወይኖ የዋለበቱ፣አረገረገ ሸሸ መሬቱ፡፡
4. ተጉዞ ተጉዞ ሰው እንደ ደመና፣መመለሻው ጠፋ ያገሩ ጎዳና፡፡

ተግባር ፡-አራት

ቀጥሎ የቀረበውን ማስታዎሻ በጥሞና በማንበብ ከታች በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት አምስት ቅኔዎችን ከነፍችዎቻቸው ጽፋችሁ በመምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ማስታወሻ፡- ቅኔ

ቅኔ ‹‹ቀነየ›› ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም አመሰገነ፣አወሳሰበ፣ቀናውን በሌላ መንገድ ተናገረ ማለት ነው፡ ፡ ቅኔ በንግግር ሃሳብን አመስጥሮ ለማስተላለፍ የሚያስችል ጥበብ ነው፡፡ ሃሳብን መመስጠር፣ መቅበር፣ ነገሮችን የማራቅ ጥበብ የሚታይበትና እንደወርቅ ቆፍሮ ሚስጥሩን የማግኘት ክህሎትንና እውቀትን የሚጠይቅ ነው፡፡ በቅኔ ውስጥ ህብረቃል የምንለው ቃል/ሐረግአለ፤ ይህ ህብረ ቃል በውስጡ ሰምና ወርቅ አጣምሮ ይይዛል፡፡ ህብረቃል ማለት የጋራ ወይም የህበረት እንደማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በቅኔ ውስጥም ሰምና ወርቁን አስተባብሮ የሚይዝ ቃል/ሐረግ ማለት ነው፡፡

ሰም በቅኔ ውሰጥ ግልጽ መልዕክት የሚያስተላልፍና በፊት ለፊት ወይም በቀጥታ የምናገኘው የቃሉ/የሐረጉ ትርጉም ሲሆን ሚስጥራዊውን/ድብቁን ፍቺ በቀላሉ እንዳይታወቅ የሚያደርግ ነው፡፡ ጥልቅ የሆነ የቋንቋ ችሎታን የማይጠይቅ አስቀድሞ ወደ አእምሮአችን የሚደርሰው  የቅኔው ትርጉም ነው፡፡

ወርቅ በሰሙ ተሸፍኖ በቃላት ምርምር የሚገኝ የቅኔው ዓብይ ክፍል ሲሆን ቅኔው ለምን ተቀኘ? ውስጠ ሚስጥሩስ ምንድ ነው? በቅኔው ምን ድብቅ ሚስጢር መተላለፍ ተፈልጎ ነው ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡ ወርቁን ለመረዳት ጥልቅ የሆነ የቋንቋ ዕውቀት ፣የማሰብ፣የማሰላሰልና የማገናዘብ ችሎታ ይጠይቃል፡፡

ምሳሌ፡-  ንብረታችሁን ሁሉ ታስቆጥራላችሁ፣
አለቃችሁ እንጂ ማን ወሰደባችሁ፡፡ በሚለው ውስጥ

ህብረቃሉ--- አለቃችሁ የሚለው ሲሆን

ሰሙ---- አለቃ/ኃላፊ የሚለውን ፍች ሲሰጥ

ወርቁ --- ደግሞ ተፈጃችሁ/ተጨረሳችሁ የሚለውን ፍች ይሰጠናል፡፡

በዚህ መሰረት እናንተም ከወላጆቻችሁ በመጠየቅ አምስት ህብረቃሉን ሰሙንና ወርቁን የሚያሳዩ ቅኔዎች በማምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ያልተሟሉ ቃላዊ ግጥሞች አሟልታችሁ ፃፉ።

1. መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ፣
   የሴቱን አናውቅም ወንድ ------------።
2. ስራ እንደኮሶ እየመረረው፣
   ጠቅልሎ መጉረስ ማን --------።
3. ብነግድ አንድ ጨው ባርስ አንድ ቁና፣
   እንግዲህ ምን ልበል ----- ።
4. የኔማ እመቤት የፈተለችው፣
   የሸረሪት ድር ----------------።
5. ሲሰራው ዋለና ሲያንፀው ሲያንፀው፣
   እንደመፋቂያ እንጨት ----------።
6. የኔማ ጌታ የሰጠኝ ሙክት፣
   አንድ ዓመት ሞላኝ----------።

### ተግባር ሁለት፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥሞችን ጽፋችሁ በመምጣት በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

ዘይቤያዊ ቃላት

### ተግባር፡-

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ማስታወሻና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ።

1. ከሚከተሉት መካከል አነፃፃሪ ዘይቤ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. አይኑ የበርበሬ ማስቀመጫ መስሏል፡፡

ለ. ፊቱ የሀምሌ ሰማይ ነው፡፡

ሐ. ቁመቱ ዛፍ ያክላል፡፡

መ. ጥርሶቹ የዛገ ቆርቆሮ መስለዋል፡፡

2. እሱማ ጨዋ ነው ባህሉን አክባሪ፣

እርቃኑ ቢታይም ለብሶ ትልትል ሱሪ፡፡

በአመሉስ ቢሆን ከቶ ማን ያማዋል፣

ቁማር መጠጥ እንጂ ምን ተገኝቶበታል፡፡ ይህ ግጥም የቀረበው በምን አይነት ዘይቤ ነው?

ሀ. ምፀት ሐ. ለዋጭ

ለ. ተምሳሌት መ. ግነት

3. አንቺ ፀሀይ ያየሽውን መስክሪ? ፡፡ ይህ ሀሳብ የቀረበው በምን አይነት ዘይቤ ነው?

ሀ. እንቶኔ ሐ. ምፀት

ለ. ግነት መ. አያዎ

4. ሆዴ ረመጥ ነው፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተገለፀው የዘይቤ አይነት ----ነው፡፡

ሀ. ግነት ሐ. ተለዋጭ

ለ. ሰውኛ መ. አነፃፃሪ

5. ከሚከተሉት መካከል በሰውኛ ዘይቤ የቀረበው የቱ ነው?

ሀ. ዐባይ የሀገር ኩራት ነው ሐ. ሀገር ትጣራለች

ለ. እናት ኢትዮጵያ መ. አልማዝ ተኮራምታ ቁጭ አለች

6. የገዛሁት እንጀራ እፍ ቢሉት ወንዝ ይሻገራል፡፡ ይህ ሀሳብ የቀረበበት የዘይቤ ይነት ከሚከተሉት መካከል የቱ ነው?

ሀ. ሰውኛ ሐ. ተምሳሌት

ለ. እንቶኔ መ. ግነት

7. ሰውዬው የቀን ጅብ ነው። ይህ ግጥም በየትኛው ዘይቤ የተገለፀ ነው?

ሀ. በምፀት ሐ. በእንቶኔ

ለ. በግነት መ. በተለዋጭ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ፡-

ቀጥለው በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቢሆንም | እንደ | በ |
| ይሁን እንጂ | ስለ | በተጨማሪም |

1. ትዕግስት ከትምህርት ቤት ----------- ተመለሰች እጇን ታጠበች፡፡
2. የእንቦጭ አረምን ለማጥፋት ህዝቡ ርብርብ እያደረገ ------ የተፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም፡፡
3. አሁን የጥናት ሰዓት ----- ደረሰ ቴሌቪዥን መዘጋት አለበት፡፡
4. ያሲን ጠንክሮ አንብቦ ነበር፤ --------------- ጥሩ ውጤት አላመጣም፡፡
5. ኳስ መጫወት ብወድም --- ኮሮና ምክንያት አልተሳካልኝም፡፡
6. ጓደኛዬ ከትምህርቱ ---------- የቀን ስራ ይሰራል፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

እስካሁን ስለውስብስብ ዓረፍተ ነገር በተማራችሁት መሰረት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አምስት ውስብስብ አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ ቃላዊ ግጥም ምንነትና አይነቶች፣ የግጥም አነባበብ ዘዴ፣ የግጥም ቃላት እንዲሁም ስለዘይቤና የዘይቤ አይነቶች ተምረናል።
- ቃላዊ ግጥም ሰዎች ጽህፈትን መጠቀም ከመጀመራቸው በፊት ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን ሲያንፀባርቁበት የኖረ አሁንም በማገልገል ላይ የሚገኝ ቃላዊ የህዝብ ሀብት ነው። የቃላዊ ግጥም አይነቶች በርካታ ቢሆኑም የሰርግ፣ የስራ፣ የሀዘን ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው።
- አንድን ግጥም ዜማውን ጠብቀን ለማንበብ በሐረጎችና በስንኞች መጨረሻ የተወሰነ የጊዜ ቆይታ ማድረግ፤ ግጥሙን በተገቢ ዜማዊ ቃና ማንበብ፤ የተለያዩ የግጥም አነባበብ ስልቶችን ከመምህራን፣ ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥንና ከስነ-ጽሁፋዊ መድረኮች ወዘተ. ማዳመጥ፤ ግጥሙ የቅስቀሳ፣ የሀዘን፣ የግርምት፣ የትዝብት፣ የውደሳ... መሆኑን በማጤን የአነባበብ ለዛውን እንደየግጥሙ ዓይነት እየቀያየሩ ለማንበብ መሞከር የሚሉ መመሪያዎችን መከተል አስፈላጊ ናቸው።
- ዘይቤ (ዘይቤያዊ ንግግር) የምናስተላልፈው መልዕክት ምስል በመፍጠር መልዕክቱ ጎልቶ፣ አምሮና ደምቆ እንዲታይ የምንጠቀምበት የቋንቋ አጠቃቀም አይነት ነው።

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ከታች የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች አይነት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. አይዞሽ ሙሽሪት አይበልሽ ከፋ፣

ሁሉም ያገባል በየወረፋ፡፡

ለ. በጠፍጣፋ ድንጋይ ከተዘጋ በሩ፣

እናት አትገኝም እንደወፍ ቢበሩ፡፡

ሐ. ፎጣ መጠምጠም ራስ ይመልጣል፣

ሽንጥን ገትሮ ማረስ ይበልጣል፡፡

መ. ዱብ ዱብ ይላል እንደ በረዶ፣

በልጅነቱ በረሃ ለምዶ፡፡

2. ቀጥለው በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የዘይቤ አይነቶች ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. <<ከቸኮልክ አትደርስም>> ብሎ መከረኝ፡፡

ለ. ጠይባ እንደ ንብ ታታሪ ናት፡፡

ሐ. <<ለሰው ሞት አነሰው አለች ቀበሮ፡፡>>

መ. የአባቴ ፈረስ ከመኪና ይፈጥናል፡፡

ሠ. ዘነበ አንበሳ ነው፡፡

## ሙዳየ ቃላት

| ቃላት | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሃቅ | እውነታ |
| ህልም | በእንቅልፍ የሚታይ፣ራዕይ፣ የማይሳካ ምኞት |
| መና | ከንቱ፣ብልሹ (ሲላላ) ፣ ህብስት ፣ ምግብ (ሲጠብቅ) |
| መዛመት | መሰራጨት |
| መዥገር | የከብቶችን ደም የሚመጥ ተባይ |
| መደለያ | ማባበያ |
| ሙግት | ክርክር፣ንትርክ፣ጭቅጭቅ |
| ሰለባ | ተጠቂ፣ተጎጂ |
| ሰርክ | ዘወትር (ሁልጊዜ) |
| ሰናይ | መልካም |
| ስራ ፈት | ስራ የሌለው |
| ረባዳ | ጎድጓዳ (ዝቅተኛ) ቦታ |

| | |
|---|---|
| ራዕይ | ወደ ፊት ሊሰራ የታሰበ እቅድ |
| ሸንጎ | ጉበኤ፣ስብሰባ፣ዳኝነት የሚሰጥበት ቦታ |
| በነቂስ | በሙሉ፣አንድም ሳይቀር |
| ባል እንጀራ | ጓደኛ |
| ባል ደረባ | አብሮ የሚሰራ ፣የስራ ጓደኛ |
| ብሂል | አባባል፣ መርህ |
| ነፍስ ወከፍ | እያንዳንዱ፣በየራሱ |
| አሉባልታ | የውሸት ወሬ |
| አመርቂ | አጥጋቢ |
| አምባ | መንደር፣ተራራ |
| አሪ | የአፋር ህዝብ ባህላዊ የቤት አሰራር |
| አርነት | ነፃነት |
| አዘቦት | የስራ ቀን |
| አፍላ | ወጣት |

| | |
|---|---|
| እምብርት | መሃል |
| እንቅፋት | መሰናክል፣እግርን የሚያደናቅፍ |
| ወጌሻ | ስብራትን ፣ውልቃትን የሚጠግን ባለሙያ |
| ዋዜማ | ከበዓል በፊት ያለው ቀን |
| ውለታ | አንዱ ለሌላው የሚያደርገው መልካም ስራ |
| በኩር | የመጀመሪያ |
| ገድል | የአንድ ግለሰብ ስራ፣ጀብዱ |
| ገፀ-በረከት | ስጦታ |
| ፈርጅ | ክፍል ወይም ረድፍ |

## ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሃሞቱ ፈሰሰ | ሰነፈ |
| ሆደ ባሻ | ቶሎ የሚከፋው |
| ልባም | ብልህ፣አስተዋይ |
| ልብ አቁስል | ጨቅጫቃ፣ነዝናዛ |
| ሳር ቅጠሉ | ሁሉም |
| ቂም አረገዘች | ተቀየመች |
| አመድ አፋሽ | በደግነቱ የማይመሰገን |
| አቅመ ቢስ | ደካማ |
| አይኑ ቀላ | ተናደደ |
| አይን አውጣ | ደፋር፣ ባለጌ |
| እግረ ደረቅ | እድለ ቢስ |
| አፈ ቅቤ | ክፉ ነገር የማይናገር፣አታላይ |
| የውሃ ሽታ | አድራሻው የማይታወቅ |
| ጮቤ ረገጠ | ተደሰተ |

## ዋቢ ፅሁፎች

መስፍን ሀብተማሪያም:: 1983 :: አውደ ዓመት :: አዲስ አበባ ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

ማርታ እሸቱ :: 2007 :: ኩራዝ አማርኛ :: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ ኢንተርሽናል አሳታሚ ድርጅት፡

ሞላ ኀብስቱ::2013:: ባዶ ምጥ የስነ ግጥንም መድብል::

ሪፖርተር ጋዜጣ፣ ጥር 18 ቀን፣ ቅፅ 19 ቁጥር 1434፣2006 ዓ.ም::

ሪፖርተር ጋዜጣ፣ መስከረም 18 ቀን ፣ቅጽ 25 ቁጥር 2026፣2012 ዓ.ም::

ሰለሞን ሐለፎም ::1997:: የድርሰት አፃፃፍ:: አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት::

ሰለሞን ጥላሁን እና ስምረት ገብረ ማሪያም:: 2000:: ደማቆቹ የአንዳንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊያን የሕይወት ውልብታ:: ፖፕሌሽን ሚዲያ ኢትዮጵያ::

ባየ ይማም:: 2002:: አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው:: አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች::

ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወልደ መስቀል:: (2007) ስብስብ ስራዎች:: አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት:: (ሁለተኛ እትም)

ተምሳሌት እፁብ ድንቅ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት:: 2007:: አዲስ አበባ፣ ፀሀይ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት::

ታለጌታ ይመር :: 2007 :: ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ አጋዥ መፅሀፍ ከ7ኛ-10ኛ ክፍል :: አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት::

አለም እሸቱ:: 1999:: ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ ከ7ኛ- 10ኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት::

አለምፀሀይ ወዳጆ :: 2009 ::የማታ እንጀራ የግጥም መድብል :: አዲስ አበባ፣ ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል

ማህበር፡፡

አብዱ ራህመቶና ንጉሴ አየለ ፡፡1979፡፡ ሙሽራው ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ሐምሌ 25/2013 ዓ.ም፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ቁጥር 285፣ሰኔ 15/2011 ዓ.ም፡፡

ኢካሽ 25ኛ ዙር የጋዜጠኝነት ሰልጣኞች መጽሄት፡፡ የካቲት 2013 ዓ.ም፣ ኖቫ ማተሚያ ቤት፡፡

ኤ.ሲ.ፒ. ኤሲ የትምህርት ቦርድ የት/ቤት የበጎ ፍቃደኞች መመሪያ ማኑዋል፡፡

ከበደ ሚካኤል፡፡1961፡፡ ብርሃነ ህሊና ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ወይ አዲስ አበባ መፅሄት፣ቅፅ 1፣ቁጥር8፣2013ዓ.ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ 1992፡፡ የሥነጽሑፍ መሠረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዝክረ ህዳሴ አዲስ አበባ መጽሄት፣2013 ዓ.ም፡፡

የሻው ተሰማ ፡፡1996፡፡ ልሳነ-ብዕር ከመልሳነ ሰብእ ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት የታተመ፡፡

የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፡፡ የ2006 ዓ.ም በጀት ዓመት ሪፖርት፡፡

ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ ፡፡1999፡፡ አማርኛ አጋዥ መጽሀፍ ፡፡ አዲስ አበባ፣አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት

ጂ አይ ዜድ (GIZ) የጀርመን የተራዶ ድርጅት፣ 2020 እ.ኤ.አ የታተመ፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ 2008፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ጠና ደዎ፡፡ 2008፡፡ ሰው፣ ግብረገብና ስነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፡፡

## የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | 1 | ፪ | 2 | ፫ | 3 | ፬ | 4 | ፭ | 5 | ፮ | 6 | ፯ | 7 | ፰ | 8 | ፱ | 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | | ፲፪ | | ፲፫ | | ፲፬ | | ፲፭ | | ፲፮ | | ፲፯ | | ፲፰ | | ፲፱ | | ፳ | 20 |
| ፳፩ | | ፳፪ | | ፳፫ | | ፳፬ | | ፳፭ | | ፳፮ | | ፳፯ | | ፳፰ | | ፳፱ | | ፴ | 30 |
| ፴፩ | | ፴፪ | | ፴፫ | | ፴፬ | | ፴፭ | | ፴፮ | | ፴፯ | | ፴፰ | | ፴፱ | | ፵ | 40 |
| ፵፩ | | ፵፪ | | ፵፫ | | ፵፬ | | ፵፭ | | ፵፮ | | ፵፯ | | ፵፰ | | ፵፱ | | ፶ | 50 |
| ፶፩ | | ፶፪ | | ፶፫ | | ፶፬ | | ፶፭ | | ፶፮ | | ፶፯ | | ፶፰ | | ፶፱ | | ፷ | 60 |
| ፷፩ | | ፷፪ | | ፷፫ | | ፷፬ | | ፷፭ | | ፷፮ | | ፷፯ | | ፷፰ | | ፷፱ | | ፸ | 70 |
| ፸፩ | | ፸፪ | | ፸፫ | | ፸፬ | | ፸፭ | | ፸፮ | | ፸፯ | | ፸፰ | | ፸፱ | | ፹ | 80 |
| ፹፩ | | ፹፪ | | ፹፫ | | ፹፬ | | ፹፭ | | ፹፮ | | ፹፯ | | ፹፰ | | ፹፱ | | ፺ | 90 |
| ፺፩ | | ፺፪ | | ፺፫ | | ፺፬ | | ፺፭ | | ፺፮ | | ፺፯ | | ፺፰ | | ፺፱ | | ፻ | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 |
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | |

# አማርኛ

# እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# ፯ኛ(7) ክፍል


አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIRO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU